# በውስጥ ገጾች


ዐብይ ርዕስ

"በሃገራዊ የምክክር መድረኩ አጀንዳዎች በመገናኛ ብዙኃን ይተቻሉ፤ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ይሳተፋሉ"

ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ
የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር

3



ፖለቲካዊ ትኩረት



አቶ አመሃ መኮንን



ዶክተር ራሔል ባፌ

አገር የሚበላው ነቀዝ

11


ፍትህና መልካም አስተዳደር




የሕትመቶቹ ጥሪ

17

ባህልና ቱሪዝም



25

የገዳሙ ትንሳኤ

ለጡረተኛው የቆመው የአዋጅ ማሻሻያ

14

ከደስታ ባሻገር

20

ትኩረት የሚሻው የመድሃኒት አቅርቦት

21

ደምሴ ፅጌና ተመሳጣሪ ታሪኮች

36

# ርዕሰ አንቀጽ

## መመካከር እያለ መነካከስ አይበጅም!

አገራዊ ውይይቶች የአንዲት ሃገር ህልውና በአንድ ወይም በሌላ መንገድ አደጋ ላይ ሲወድቅ አሊያም ዜጎችና ይመለከተናል የሚሉ አካላት የሃገሪቱ ቀጣይነትና የዜጎች የወደፊት ኑሮ ሲያሳስባቸው የሆነ አይነት የመውጫ ብልሃት ለመሻት የአኗኗር ዘይቤያቸውን፣ የፖለቲካና ኢኮኖሚ አወቃቀራቸውን ያሉበትን ክፍለአለም ታሳቢ ያደረገ አካታች የንግግር የውይይት ወይም የድርድር መንገዶች ስለመፈለጋቸው የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ።ለኢትዮጵያ ሁሉንተናዊ ሰላም ሲባል የተመሰረተው አገራዊ የምክክር መድረኩ ቀደምሲል የነበሩና አሁንም ፈተና ሆነው የተገኙ የአገራችንን ችግሮችን ተነጋግሮ ከመፍታት አካያ የሚኖረው ሚና ጉልህ ነው፡፡

ምንም እንኳን ብዙ የሚያግባቡ ነገሮች ቢኖሩንም ከጊዜ ወደጊዜ ግን አንዳንድ መሰረታዊ የሆኑ የማያግባቡን ነገሮች በመኖራቸውና እነኚያም ለግጭትና አልፎም ለጦርነት ስለዳረጉን ህዝቦቻችን በማያግባቡን ነገሮች ላይ ተወያይተው ወደፊት ሀገራችን ሰላማዊ የምትሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ተገቢ ነው፡፡ ውይይት ተወያዮችን መግባባት ላይ ያደርሳል፡፡ መግባባት ላይ እንኳን ባይደረስ ከነ አለመግባባታችን ተግባብተን እንድንቀጥል ያስችላል፡፡ ከነ አለመግባባታችን ተግባብተን እንቀጥል ማለት አንድ ቀን ያላግባቡን ነገሮች ይፈታሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ውይይት እንጂ ጦርነት እና መሳሪያ ጥቅም የለውም፡፡

ማንኛውም ችግር የተፈጠረው ሰዎች በሃሳብ ባለመግባባታቸው በመሆኑ ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች ችግራቸው እንዲወገድ በቅድሚያ መነጋገር አለባቸው፡፡ ውይይት መግባባትን ያመጣል፡፡ በብዛትና በሀይል ልዩነቶቻችን ላይ ስለሰራን አሁን የደረስንበት ላይ ደርሰናል፡ የጦርነትን አስከፊነት አይተናል፡፡ በጦርነት ሰላም አይመጣም፡፡ ዘላቂ የሆነ ወንድማማችነትና እህትማማችነት ሊመጣ የሚችለው ቁጭ ብሎ መሳሪያን አስቀምጦ መወያየት ሲቻል ነው፡ ፡ ወደ ውይይት ሲመጣ መጀመሪያ መቀመጥ ያለበት መሳሪያ ነው፡፡ ውይይት ሁላችንም የምናሸንፍበት እስከሆነ ድረስ ሁላችንም መሳሪያችንን አስቀምጠን ሰላምን አንግበን መምጣት አለብን፡፡ ስለሰላም እስከተመጣ ድረስ ለሰላም የማይከፈል መስዋዕትነት የለም፡ ፡ ለሰላም በሚከፈል መስዋዕትነት ውስጥ ደግሞ ህይወት አይጠፋም፡፡

በጦርነት ያየነው አሳርና መከራ ነው፡ ፡ መመካከር እያለ መነካከስ አይበጅም። ሰላም በአገራችን በመኖሩ የሚቀኑ አሉ። እርስ በእርሳችን እንድንቀያየም፣ እንዳንረዳዳ፣ እንዳንተማመን ሠላም የሌለባት ረብሻና መከራ የሰፈነባት ኢትዮጵያ እንድትሆን ሌት ከቀን የሚሰሩ አካላት እንዳሉ መረዳት ያሥፈልጋል። ወንድም ከወንድሙ ስለምን ብሎ ይናከሳል?

# መኀ እንጠይቅልዎ!

ጤና ይስጥልን፣ ለአገራችን ብሎም ለምስራቅ አፍሪካ ዋነኛ የቃጠሎ፣ የድንገተኛና የአደጋ ህክምና አገልግሎት መስጫ ሆስፒታል በሚል ዓላማ ሐምሌ 2007 ዓ.ም ሥራ የጀመረው አቤት ሆስፒታል፣ "የተቋቋመበት ዓላማና እየሰጠ ያለውም አገልግሎት ትልቅና ሰፊ ሆኖ ሳለ በዚህ ልክ ትኩረት እየተሰጠው አይደለም፣ አሁን ካለበት ኪራይ ቤት ወጥቶ በራሱ ህንጻ አገልግሎት እንዲሰጥ ከታሰበ ዓመታት ቢቆጠሩም፣ ዛሬም፣ ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር ጠባብ በሆነ ህንጻ፣ በርካታ ገንዘብ እየከፈለ አገልግሎት እየሰጠ ነው፤ ሆስፒታሉን እንዲያስተዳድር ኃላፊነት የተሰጠው የቅ/ጳ/ሆ/ሚ/ሜ/ኮሌጅም ሆስፒታሉን በተገቢው ልክ እያገዘው፤ ለህንጻው ስኬትም በቁርጠኝነት እየሰራ አይደለም" በሚል ከሆስፒታሉ ማህበረሰብ ቅሬታ ደርሶናል፤ ይህንን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ኃላፊዎች አነጋገረን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውናል፡፡

**የቅ/ጳ/ሆ/ሚ/ሜ/ኮ ምክትል ፕሮቮስት አቶ ተመስገን መኮንን፡-** የአቤት ሆስፒታል አገልግሎት ሲታሰብ፣ በጊዜው፣ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦታ ፈልገው እንዲሰጡ፣ የቅ/ጳ/ሆ/ሚ/ሜ/ኮ ደግሞ በጀቱን አስፈቅዶ ግንባታውንና የስራ ሂደቱን እንዲመራ በሚል ዓላማ ነበር፡፡ ቦታውም ተገኝቶ ሆስፒታሉም ተገንብቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ አገልግሎቱ መጀመር ስለነበረበት ሆስፒታሉ አሁን ባለበት ቦታ ኪራይ እየከፈለ ሥራ እንዲጀምር ተደርጓል፡፡

ሆስፒታሉ መሬት አጥቶ እስካሁን በኪራይ መቆየቱ እንደ መንግሥት ጎድቶናል፤ ኪራዩ ብዙ ነው የሚለውና ከአከራይ ጋር ያለው ጭቅጭቅም ከፍተኛ ጫና ፈጥሮብናል፤ ቢሆንም ግን ገንዘቡን ብቻ ሳይሆን የበርካቶችን ሕይወት መዳን እንደተቻለም ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ሆስፒታሉ የራሱን ህንጻ ለመገንባት በተደረገው ጥረት ፈተና የነበረው ቦታ ማግኘት ሲሆን፣ ምን ያህል ገንዘብ ለኪራይ እየወጣ እንዳለና የሆስፒታሉ ግንባታ ለከተማዋም ለአገርም የሚያበረክተውን አስተዋጽኦንም ስናስረዳ ቆይተናል፤ በመጨረሻም፣ ሆስፒታሉ የኮቪድ ማዕከል ሆኖ በሚያገለግልበት ወቅት ያገኘውን በከተማ አስተዳደሩ የመኀብኘት አጋጣሚ ተጠቅመን የቦታ ጉዳይ ችግር እንደሆነብንና በየጊዜው ጥያቄ ብናቀርብም መፍትሔ እንዳላገኘን ባስረዳነው መሠረት፣ ሆስፒታሉ በሚገኝበት ጉለሌ ክፍለ ከተማ ውስጥ ያሉ ክፍት ቦታዎች እንዲጣሩ ተደርጎ፣ በክ/ከተማው ወረዳ ስምንት፣ 8 ሺህ 618 ካሬ ቦታ አግኝተን የካርታ ስራውም ተጠናቆ በዚህ ዓመት ግንባታ ለመጀመር እየተንቀሳቀስን ነው፡፡

**የአቤት ሆስፒታል ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶ/ር ሃናኒያ ጀንባይ፡-** "በምስራቅ አፍሪካ የድንገተኛ አደጋ ህክምና ላይ ብቻ የሚሰሩ ሆስፒታሎች የሉንም፣ አዲስ አበባም እንደ አፍሪካ ህብረት መቀመጫነቷ ይህ ሆስፒታል ያስፈልጋታል" በሚል መነሻ አቤት ሆስፒታል ከ 7 ዓመታት በፊት ስራ ሲጀምር፣ የአደጋ ፍሰትና የአገልግሎቱን አስፈላጊነት ታሳቢ በማድረግ፣ የራሱን መሬት አግኝቶ ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ በኪራይ ቤት አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ ነው፡፡ ሆስፒታሉ ለተከራየው ህንጻ፣ ከቫት ውጪ በአመት 52 ሚሊዮን 600 ሺ ብር ለኪራይ የሚከፍል ሲሆን፣ በራስ ቤት አገልግሎት ከመስጠት ጋር ሲነጻጸር የኪራይ ወጪው የዋዛ ባይሆንም፤ በዚህ ብር በተከራየነው ህንጻ የበርካቶችን ሕይወት መታደግ መቻሉን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

አቤት ሆስፒታል የራሱ ህንጻ እንዲኖረው ለማስቻል ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል፤ ረጅም ጊዜ የወሰደውም ይሄ ሂደት ነበረ፤ ይህ ጥረት ስላልተቋረጠም የግንባታ በጀት ሳይመለስብን እየተንከባለለ እዚህ ሲደርስ ሶስት ዓመት ሆኖታል፡፡ መሬቱ ተገኝቶ ካርታ ከተሰራ በኋላ ደግሞ ብዙ ቴክኒካል ችግሮች ገጥመውን ነበር፤ አሁን ላይ የካርታ ሥራው አልቆ፣ ጨረታ የማውጣትና ግንባታ የመጀመር ሂደት ላይ ነው ያለነው፡፡

**በቅ/ጳ/ሆ/ሚ/ሜ/ኮ የምህንድስናና ግንባታ ዳይሬክቶሬት ተጠባባቂ ዳይሬክተር ኢንጂነር አማኑኤል ህይወት፡-** ለሆስፒታሉ ማሰሪያ የሚሆነውን ካርታ ያገኘነው ሐምሌ 2013 ዓ.ም ቢሆንም፣ በካርታ ያለው መሬት ሲወርድ ወደ አስፋልት ስለወጣ፣ እንዲስተካከል ጠይቀን ህዳር 28/2015 የተስተካከለ ካርታ ተሰጥቶናል፡፡ አጠቃላይ ካሬው 8618 ካሬ ሲሆን፣ ከ1300 በላይ አልጋ መያዝ የሚችል፣ አቤት አሁን እየሰጠ ያለውን አገልግሎት በተሻለ መልኩ መስጠት እንዲያስችለው ሆኖ ዲዛይን የተሰራለት የራሱ ሄሊኮፕተር ማረፊያ ያለው ትልቅ ሆስፒታል ለመገንባት በዝግጅት ላይ ነን፤ ቀሪ ሥራዎችና የጨረታ ሂደቱ ሁለት ወራት ቢፈጅ ከሶስት ወራት በኋላ ግንባታውን ለመጀመር ዝግጁ ነን፤ ግንባታውም እስከ 5 ቢሊዮን ብር ድረስ፣ በሁለት ዓመት ይጠናቀቃል የሚል ግምት አለን፡፡


በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እየታተመ የሚወጣ

እፕድ

ዋና አዘጋጅ፡– ሳሙኤል ይትባረክ
ፖ.ሳ.ቁ፡– 30145
ስልክ፡– 011-1264207
Sammes.zellek@gmail.com
zemenpress@gmail.com

ከፍተኛ አዘጋጆች፡– ንጉሴ ተስፋዬ, ስሜነህ ደስታ

አዘጋጆች፡– ተስፋ ፈሩ, ዮርዳኖስ ፍቅሩ

ማስታወቂያና ደንበኞች አገልግሎት
ስልክ፡- 011 1 56 98 73
ፋክስ፡- 011 1 57 44 40

ማከፋፈያ፡–
ስልክ፡- 011 1 57 02 70

ግራፊክስ ዲዛይን
ትዕግስት ሰይፉ

ፎቶግራፍ፡–
አሸናፊ ጉደታ

# “በሃገራዊ የምክክር መድረኩ አጀንዳዎች በመገናኛ ብዙኃን ይተቻሉ፤ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ይሳተፋሉ”

*ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ*
*የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር*

ተስፋ ፈሩ

የጥር ወር የዘመን መጽሔት ዐቢይ ርዕስ ዓምድ እንግዳችን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ ናቸው። ዘመን መጽሔት ከዋና ኮሚሽነሩ ጋር ባደረገችው ቆይታ ከተቋቋመ ዘጠኝ ወራት ያስቆጠረው ኮሚሽን እስካለንበት ጊዜ ድረስ ያከናወናቸውን ዓበይት ተግባራት፣ ያጋጠሙትን ችግሮች፣ ቀጣይ ሥራዎቹን፣ ስሀገራዊ ምክክሩ መሳካት ከተለያዩ አካላት ጋር እያደረገ ያለውን ግንኙነት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የተመለከቱ ጥያቄዎች አንስታለች፣ መልካም ቆይታ።



ኢትዮጵያ 86 እና 87 ወይም ከዚያም በላይና በታች ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦችና ብሔሮች ያሉባት ሀገር ነች። ስለዚህ እያንዳንዱ ወገናችን መወከል አለበት።

**ዘመን፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ፣ በቅድሚያ ከዘመን መጽሔት ጋር ቆይታ ለማድረግ ስለፈቀዱ በዝግጅት ክፍላችን ስም ምስጋና አቀርባለሁ።**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** እኔም እናንተ ወደ ኮሚሽናችን ጽሕፈት ቤት ስለመጣችሁ አመሰግናለሁ።

**ዘመን፡- ሀገራዊ ምክክር ከሚያልፍባቸው ቅድመ ዝግጅት ፣ ዝግጅት፣ ምክክር እና ትግበራ ከሚባሉት አራት ሂደቶች ሁለቱ ደረጃዎች ተጠናቀው ወደ ሦስተኛው ለመሸጋገር ጫፍ የተደረሰበት ጊዜ ላይ ነን። ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ያከናወናቸው ዐበይት ተግባራት ምንድን ናቸው?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** እንዳልከው የዚህ ሀገራዊ ምክክሩ የሥራ ሂደት አራት ደረጃዎች አሉት። የመጀመሪያው የቅድመ ዝግጅት የምንለው ነበር። በቅድመ ዝግጅት ወቅት አዲስ ተቋም እንደመሆናችን መጠን ቢሮችንን በሰው ኃይል ማደራጀት ነበረብን። ምክክሩን ለማሳለጥ የተመረጥነው 11 ኮሚሽነሮች ከተለያየ ቦታ ነው የመጣነው። የምክክርን ጽንሰ ሀሳብ በሚገባ ተረድተን አንድ ወለል ላይ እንድንሆን የማስቻል ራሱን የቻለ ሥራ ነበር። ከዚያ ጋር ደግሞ ሀገራዊ ምክክሩ የተቋቋመበትን አዋጅ ዓላማና ተግባራትን እንዲሁም ያሉትን 33 ገደማ አንቀጾች በሚገባ መረዳት ተያያዥ ጉዳይ ነው። ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር የሚሠሩ ብዙ ተቋማት አሉ፣ እነዚህን ተቋማት የመለየትና ራሳችንን እና ሥራችንን የማስተዋወቅ ሥራ ሠርተናል። በዚህ ረገድ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፤ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የአካል ጉዳተኛ ማኅበራት፣ የሴቶች ማኅበራት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም እዚህ ሀገር ያሉትን የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ተወካይ አምባሳደሮችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን የሚመሩ ኃላፊዎች የመሳሰሉትን

ሁሉ አግኝተናል። በዚህ ቅድመ ዝግጅት ወቅት በተለያዩ ሀገሮች የተካሄዱ ውይይቶች ምን ያህሉ ተሳካላቸው፤ ምን ያህሉ ደግሞ ከሸፉ፤ እንዴት ተዋጣላቸው እንዲሁም ለምን ከሸፉ የሚለውን መጽሐፍቶችንና መጣጥፎችን በማሰባሰብ ስንፈትሽ ነበር። በሀገራችን በዚህ ግዝፈት ደረጃ በአዋጅ ተቋቁሞ የምክክር ሥራ ሲሠራ ለመጀመሪያ ጊዜ በመሆኑ በቅድመ ዝግጅት ጊዜ ውስጥ ብዙ የሠራናቸው ሥራዎች ነበሩ። በተጨማሪም አዋጁን በመንተራስ ለሥራዎቻችን የሚሆኑ የኮሚሽነሮችና የጽሕፈት ቤት የሥነ ምግባር መመሪያዎችን እና የተለያዩ ድንጋጌዎችን አዘጋጅተናል።

ከቅድመ ዝግጅት ተቀጥላው ወደ ሆነው ዝግጅት ስንመጣ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማግኘት ወደፊት ምን አይነት ሥራዎችን በጋራ መሥራት እንደምንችል በተለያዩ ጊዜዎች በመወያየት ከአንዳንዶቹ ጋር የስምምነት ማዕቀፍ መፈራረም ደረጃ ደርሰናል። የሦስት ዓመት ስልታዊ (ስትራቴጂ) ዕቅዳችን ተነድፎ ውይይት ተደርጎበት ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ጸድቆ ወደ ሥራ ገብተንበታል። የ2015 ዓ.ም. የበጀት መርሐ ግብራችንን አውጥተን አጸድቀን በዚያ መሠረት እየሄድን ነው ያለነው። በእነዚህ ሁሉ የሥራ ሂደቶች ውስጥ የሰው ኃይል ስለሚያስፈልግ በአሁኑ ሰዓት በፊት ከሁለቱ ኮሚሽኖች የተረከብናቸውን ሠራተኞች መደበኛ አድርገን ከወጭ ባገኘነው እርዳታ ከፍተኛ እውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች ቀጥረን ሥራ ለማስጀመር በመንደርደር ላይ ነን። ምናልባት በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ የቀጠርናቸው 17 ከፍተኛ ባለሙያዎች ሥራ ይጀምራሉ። በዚህ በዝግጅት ምዕራፍ ውስጥ ከሄድንባቸው ዋና ዋና ዓበይት ጉዳዮች አንዱ አስራ አንዳችንም ኮሚሽነሮች በዘርፍ በዘርፍ ተከፋፍለን ሥራ እንድንሠራ ማድረግ ነው።

ዘርፎቹ አራት ናቸው። አንዱ የሚዲያ ኮሙኒኬሽን እና አጋርነት ዘርፍ ነው። ብዙ ጊዜ ኮሙኒኬሽን ተግባቦት ይባላል። ነገር ግን በኮሙኒኬሽን ተግባቦት ብቻ አይደለም ያለው የዛ ተቃራኒም እዛው ኮሙዩኒኬሽን ውስጥ ስላለ ዘርፉ አለን። ሁለተኛ የሥርዓት ድንጋጌና የስልጠና ዘርፍ አለን። ሦስተኛ የውይይት /ዲያሎግ/ የምንለው ዘርፍ አለ። እንዲሁም የአመራር ዘርፍም አለን። እነዚህ አራት ዘርፎች በተለያዩ ኮሚሽነሮች ነው የሚመሩት። የሚዲያ ኮሙኒኬሽን እና አጋርነት ዘርፉ በአራት ኮሚሽነሮች ሲመራ ሁለቱ በሦስት ሦስት ኮሚሽነሮች ይመራሉ። የአመራሩ ደግሞ በእኔ እና በምክትል ኮሚሽነሯ ይመራል። በዚህ መንገድ የየራሳችንን ሥራዎች ተከፋፍለን ሂደቱን በየጊዜው እያስገመገምን ነው በዚህ በዝግጅት ወቅት በመሥራት ላይ ያለነው።

የኮሚሽኑ አወቃቀር አስራ አንዱም ኮሚሽነሮች አባላት የሆኑበትና ዋና ኮሚሽነሩ የሚሰበስቡት ካውንስል አለው። በዚያ ስር ደግሞ ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነር እና ጽሕፈት ቤቶች አሉ። ስለዚህ የሚሰበሰበው አጀንዳ አንድ ሺህም ይሁን አንድ ሚሊዮን ወደዚህ ምክር ቤት ይመጣና እጅግ መሠረታዊ የሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ተለቅመው ወጥተው ወደ ሀገራዊ ውይይት ይቀርባሉ።

**ዘመን፡- በሀገራዊ ምክክሩ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል እንዲወከል የዜጎች ተሳትፎ በገዢው ፓርቲ የመጠለፍ ዕድል ባላቸው ነባር መዋቅሮች ብቻ የተገደበ እንዳይሆን በሚል ስጋታቸውን የሚገልጹ ወገኖች አሉ። የተሳታፊዎች መረጣው በምን መልኩ እየተከወነ ነው?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** አጀንዳ የሚሰበሰበው ከሕዝብ ነው ብዬሃለሁ። ሕዝብ ያለው ወረዳና ቀበሌ ውስጥ ነው። የትኛው ሕዝብ ስንል አዋጁ አሳታፊ በሆነ መልኩ ማንንም ወደኋላ ሳይተው ይላል። ኢትዮጵያ 86 እና 87 ወይም ከዚያም በላይና በታች ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦችና ብሔሮች ያሉባት ሀገር ነች። ስለዚህ እያንዳንዱ ወገናችን መወከል አለበት። በብሔር ብሔረሰብ እና በሕዝቦች መወከል ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ደግሞ ይኖራሉ። በእነዚህ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የአካልና አዕምሮ ጉዳተኞች እንዲሁም እጅግ በጣም የተረሱ ሩቅ ያሉ ሕዝቦቻችን አሉ። ብዙ ጊዜ እንዲህ አይነት ነገር ሲካሄድ ከማዕከል ወይም ከላይ ነው የሚጀምረው። ለምሳሌ ሕገ መንግሥት ሲረቀቅ ካለቀለት በኋላ ወደ ሕዝብ ይወርዳል። ሕዝብ ተወያየበት ይባልና ተወያየም ምንም አለም አላለም ሕገ መንግሥቱ ይጸድቃል። በእኛ ሂደት ግን ዋናው የዚህ ውይይት ባለቤት ሕዝባችን ነው። ስለዚህ አጀንዳውን ራሱ ማምጣት አለበት። አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር፣ ቅጠል ሻጭ ወይም ሸማኔ ሳይባል ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ስለሀገሩ የመናገር የመወያየትና የመወሰን ኃላፊነት አለበት።

በዚህ መሠረት ስናደርግ የከረምነው በየክልሎች እየሄድን ከአካባቢ መንግሥታት መስተዳድሮችና ካቢኔዎቻቸው ጋር መነጋገር ብቻ ሳይሆን በየአካባቢው ያሉትን የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች እና ሌሎችንም በመንግሥታዊ መዋቅር ውስጥና ውጪ ያሉትን የኅብረተሰብ ክፍሎች ማግኘት ጭምር ነው። ብዙ ጊዜ በመንግሥታዊ መዋቅር ሲኬድ ከመንግሥታዊ መዋቅር ውጪ ያሉት ይረሳሉ። በመንግሥታዊ መዋቅር ብቻ ከሆነ የምንሄደው ገዢውን ፓርቲ ብቻ የሚያውቁና የመንግሥትን አጀንዳ ይዘው የሚሄዱ ብቻ ሊሆኑብን ይችላሉ። ከመንግሥት መዋቅር ውጭስ ያሉትስ ? እነሱም ኢትዮጵያውያን ናቸው። እነሱም በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የመናገርና በዕጣ ፈንታዋ ላይ የመወሰን መብት አላቸው።

ብዙ ጊዜ ውይይት የሚመስል ነገር ስናካሂድ የምንሰባሰበው ፊደል የቆጠርን ነን። ምሑራን ተሰባሰቡ፤ ልሂቃን ተሰባሰቡ፤ ሀሳብ አፍላቂዎች እንዲህ አደረጉ የሚል ቋንቋ ሁሉ አለን። እኔ የአዕምሮ ሐኪም ነኝ፣ በተፈጥሮ የሰው ልጅ



አዕምሮ የተስተካከለ እስከሆነ ድረስ ሀሳብ ያፈልቃል። እኛ ሰዎች የምንለየው እሳቤና እይታችን ከሌሎቹ እንስሳት የላቀ በመሆኑና ንቃተ ሕሊና /ኮንሺየስነስ/ የሚለው እሳቤ ያለን ብቸኛ ፍጡሮች በመሆናችን ነው። ስለዚህ ሁላችንም እናስባለን። ልዩነቱ አንተ በተሻለ አንደበት ወይም በተባ ብዕርህ ታወጣዋለህ እኔ በጎለደፈ አንደበት እለዋለሁ ወይም ላወጣው አልችልም። ከዚህ በስተቀር አርሶ አደሩም ሆነ አርብቶ አደሩ ሀሳብ አለው። አንዳንድ ጊዜ በትምክት የምንናገራቸው ነገሮች አሉ። አርብቶ አደርና አርሶ አደር ከአስተዳደር ጥያቄ ውጭ ምን ጥያቄ ይኖሯቸዋል ይባላል። ይሄ ትክክል አይደለም። አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች ናቸው ብዙ ሺህ ዓመታት አኑረው እዚህ ያደረሱን። ስለዚህ ሁላችንም ሀሳብ እናፈልቃለን። ሁላችንም ሀሳብ እስካፈለቅን ድረስ ደግሞ ሁላችንም ተሰሚ መሆን አለብን። ብሔረሰብ እንኳን ብለን የማንጠራቸው ሕገ መንግሥቱ ሕዝቦች የሚላቸው፤ እኔ ብሔር ነው የምላቸው፣ እነኚያ ጠረፍ ላይ ያሉ የተረሱና የተገፉ ትንንሽ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ስለ ሀገራቸው መናገር መቻል አለባቸው፤ ድምጽ ሊኖራቸው ይገባል። ያንን ስናደርግ ነው አንተ የእንደዚህ አይነት ልጅ እኔ የእንደዚህ አይነት ልጅ ተባብለን ሳንገፋፋ የምንኖረው።

**ዘመን፡- አጀንዳ የምትሰበስቡት እንዴት ባለ መንገድ ነው ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** ዋናዎቹ ተዋንያን ሕዝቦች ስለሆኑ አጀንዳ አሰባሰባችን ከታች



**የዝግጅት ምዕራፉ አለቀ የምንለው አጀንዳዎቹ ተሰብስበው ለምክር ቤታችን ሲቀርቡና ምክር ቤታችን ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሕዝብ ተወካዮች ባሉበት አጀንዳዎቹን አጣርቶ በመምረጥ የኢትዮጵያ ሀገራዊ አጀንዳዎች እነዚህ ናቸው ብሎ ለሕዝብ ሲያሳውቅ ነው።**

ወደላይ ነው። አጀንዳ ከሕዝብ ተሰብስቦ ወደ ኮሚሽኑ ምክር ቤት ይመጣል። ይሄ ማለት ግን ከታች ወደ ጎን አንሄድም ማለት አይደለም። የክልል ፓርቲዎች እንዳሉ ሁሉ በፌዴራል ደረጃ የተደራጁ ፓርቲዎች ይኖራሉ። የክልል የተለያዩ የሲቪል ማኅበራት እንዳሉ ሁሉ በሀገር ደረጃ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህኅበራት ኮንፌደሬሽን አለ። ስለዚህ በሀገር ደረጃ የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌደሬሽን ምንድን ነው ማቅረብ የሚፈልገው አጀንዳ የሚለውን እናያለን ምክንያቱም በአካባቢ ደረጃና በሀገር ደረጃ የሚነሱ አጀንዳዎች ሊለያዩ ይችላሉ።

በሀገራችን በአሁኑ ሰዓት 11 ክልሎች አሉ፤ የክልሎች ቁጥር እየጨመረ ነው። በተጨማሪም ሁለት ትልልቅ ከተማዎች አሉ። አዲስ አበባ 11 ክፍለ ከተሞች አሉ፣ በዚያ ውስጥ ደግሞ 125 ወረዳዎች አሉ። እነዚህ ሁሉ ይካተታሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ 1 ሺህ 300 ገደማ ወረዳዎች ስላሉ ሁሉም ይካተታሉ። ነገር ግን 1 ሺህ 300 ወረዳዎች እንሂድ ካልንና እያንዳንዱን ቀበሌና ጎጥ እናሳትፍ ካልን ምናልባት 10 እና 15 ዓመታት ሊፈጅብን ይችላል።

1 ሺህ 300 ወረዳዎች ብንሄድ ከፍተኛ የሰው ኃይልና ብዙ ገንዘብ ይጠይቀናል። እኛ ደግሞ ድሆች ነን። ስለዚህ ባነሰ ዋጋ በተቻለ መጠን ሁሉንም ሕዝባችንን ተደራሽ መሆን እንዳለብን ስለምናምን 1 ሺህ 300 ወረዳዎቹን እያመቻቸን እያጣመርን ክላስተር እያደረግን ጨርሰናል። የቀረን የመጨረሻው አዲስ አበባ ነው። የአዲስ አበባን አመራርና እስከታች ድረስ ያለውን ሕዝባችንን ከጥምቀት ማግስት ጀምሮ እናገኛለን ያንን ከጨረስን በኋላ ሁኔታዎቹ በተመቻቹባቸው ቦታዎች ላይ አጀንዳዎችን መሰብሰብ እንጀምራለን። ተስፋ የምናደርገው በድሬዳዋ እና በሐረር እንጀምራለን ብለን ነው፣ ወዲያው ደግሞ ሶማሌ እንቀጥላለን እንዲያ እያልን እንሄዳለን።

በጎንዮሽ ሂደት ውስጥ ከሕዝቦቻችን ጋር በውጭ ሀገራት የሚኖሩት በተለምዶ ትውልደ ኢትዮጵያውያን (ዲያስፖራ) በመባል የሚታወቁት ወገኖቻችን ይካተታሉ። ከሀገራችን ውጭ ከአምስት ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን ይኖራሉ። ለእነኚያ ኢትዮጵያውያንም ኢትዮጵያ ሀገራቸው ነች። እነሱም የሀገራቸው ዕጣ ፈንታ ይመለከታቸዋል። ስለሚመለከታቸው ነው በስደት ውስጥ ሆነው መከራቸውን እያዩ በሚያጠራቅሙት ገንዘብ በቀጥታ በኢትዮጵያ ልማት የሚሳተፉት። ወገኖቻቸውን ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት ወደ ሀገራቸው የሚልኩት ገንዘብም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለሀገር ልማት የሚውል ነው። ስለዚህ እነሱንም ማቅረብና አጀንዳቸውን ሰብስቦ ለውይይት ማቅረብና በውይይቱ እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ ስራ ነው።

አጀንዳዎችን ስንሰበስብ በጣም ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ ግን ተመርጠው ተመርጠው መጨረሻው ላይ ጥቂት ይሆናሉ። ይሄ እንዳለ ሆኖ ከየአካባቢው ከታች የመጡት አጀንዳዎች ይጣላሉ ማለት አይደለም። በየአካባቢያቸው ችግራቸውን ለመፍታት የሚወያዩባቸው ይሆናሉ። ለምሳሌ አንዳንዶቹ በዚያው በሁለት ወረዳዎች መሐል ፤ ሌሎቹ ደግሞ በሁለት ዞኖች መሐል ፤ የተቀሩት ደግሞ በሁለት ክልሎች መሐል የሚፈቱና ወደ ፌዴራል የማያመጧቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በየወረዳው ሕዝብ የመረጣቸው ተወካዮች ተሰባስበው ወደ ዞን ይመጡና ከታች ይዘዋቸው የመጡትን አጀንዳዎች እያሰባሰቡ በክልል ላይ መርጠው የመጨረሻውን ወደ ምክር ቤታችን ይላካሉ ማለት ነው።

ይሄ ሁሉ ሂደት በዝግጅት ምዕራፉ የሚጠናቀቅ ነው። የዝግጅት ምዕራፉ አለቀ የምንለው አጀንዳዎቹ ተሰብስበው ለምክር ቤታችን ሲቀርቡና ምክር ቤታችን ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሕዝብ ተወካዮች ባሉበት አጀንዳዎቹን አጣርቶ በመምረጥ የኢትዮጵያ ሀገራዊ አጀንዳዎች እነዚህ ናቸው ብሎ ለሕዝብ ሲያሳውቅ ነው። ይሄ ሂደት ሁሉ ወደፊት ለሕዝብ ግልጽ የሚሆን ነው። በማኅበራዊ እና በዋና መገናኛ ብዙኃን /ሜንስትሪሚንግ ሚዲያዎች/ ለሕዝብ ቀርቦ እንዲተች የሚደረግ ይሆናል። በተጨማሪም እነኚህ አጀንዳዎች በፖስታ፣ በስልክ ወይም ደግሞ በሌሎች አማራጮች ለሕዝብ ሊቀርቡ ይችላሉ።

**ዘመን፡- አጀንዳዎች ከተመረጡ በኋላ በተቀሩት ምዕራፎች በሚቀጥለው ሂደት የምትሠሯቸው ሥራዎች ምን ይሆናሉ ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** አጀንዳዎች

ከተመረጡ በኋላ የሚቀጥለው ምዕራፍ የሚሆነው የውይይቱ ሂደት ነው። አጀንዳ መሰብሰብ ምናልባት ጥቂት ቀናት የሚወስድ ሥራ ሊሆን ይችላል። ውይይቱ ግን ሰፋ ያለ ጊዜ የሚወስድና በደምብ የሚካሄድ ነው። በውይይት ሂደት ውስጥ ሦስት ተዋንያን አሉ። የመጀመሪያዎቹ ተዋንያኖች ሕዝብና የተደራጁ ተቋማት ናቸው። ሁለተኛዎቹ አወያዮች ናቸው። ውይይት ማለት ክርክር አይደለም። በክርክር አሸናፊና ተሸናፊ አለ፣ በውይይት ግን አሸናፊ ብቻ ነው የሚኖረው። እኔና አንተ ወደ ውይይት ስንመጣ መጀመሪያ አዕምሯችን ውስጥ የሚመጣው ሰላም ነው። ቁጭ ብለን ስንወያይ ግን ሥርዓት ባለው መንገድ መወያየት መቻል አለብን። ምክንያቱም መሐላችን ለግጭት የዳረጉን ብዙ ነገሮች ስላሉና እኔም አንተም የለመድነው ጉልበትና ማሸነፍን ስለሆነ አወያይ ያስፈልገናል። ያ አወያያችን አንተንም እኔንም በእኩል የሚያይ ገለልተኛ እና እውቀት ያለው መሆን አለበት። በውይይታችን መሐል የድሮ ባሕሪያችን መጥቶ አንዳችን ጉልበተኛ ብንሆን አወያያችን ያቀዘቅዝናል እየበረድን ውይይታችንን እንቀጥላለን። ስለዚህ በእኔና በአንተ መካከል የሚንሸራሸሩት ሀሳቦች ይሆናሉ።

መጨረሻ ላይ ስናየው እኔም አንተም የአንድ እናት ልጆች ነን ዝም ብለን ነው መከራችንን ስናይ የከረምነው ብለን ውስጣችን ያለውን መርዝ ካወጣን በኋላ እርቅ እንፈጽማለን። እኔና አንተ እርቅ ስንፈጽም የአንተም ልጆችና ቤተሰቦች አብረው ካንተ ጋር ያቁሙ ሁሉ፣ አብረው ከእኔ ጋር ያቁሙ ሁሉ በነገሩ ያምኑበትና በጋራ ወደፊት እንቀጥላለን። አንተ ከበደልከኝ ለካ ይሄ ሁሉ ነገር ደርሷል ብለህ አንተም ጋር ጸጸት ይመጣል እኔም ጋር ጸጸት ይመጣል፣ ስለዚህ እርቃችን የተሟላ ይሆናል። አንተ አቅም ካለህ እኔን ትክሰኛለህ፤ እኔ የተሻልኩ ከሆንኩ ተበዳይ እንኳን ብሆን አንተን አግዝሃለሁ። ውይይት የሚባለው ይሄ ነው።

በውይይቱ መጠናቀቂያ ላይ የተግባባንባቸውም ሆኑ ያልተግባባንባቸው ነጥቦች በደምብ ይሰበሰቡና ተቀምረው ወደ ትግበራ ይላካሉ። የሚተገበረው አካል ማን ነው ? ብዙ ጊዜ መንግሥት ነው። ስለ ሕገ መንግሥት ከሆነ ሕግ አውጪው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው። የፍትሕ መጓደል ከሆነ ደግሞ ሕግ አስከባሪው ወይም ሕግ ተርጓሚው ነው። ለዚህ ሕዝብ የሰጠው ሀሳብ ተሰንዶ ወደ ሚመለከታቸው አካላት ይላካል። እስከዚህ ድረስ አዋጁ መብት ይሰጠናል። እንዲተገብር የላክንለት ፈጻሚው አካል የሚፈጽም ከሆነ ይኸው ፈጽሟል ብለን ለሕዝባችን እናሳውቃለን። ፈጻሚው አካል አልፈጽምም ካለም አልፈጽምም ብሏል ብለን ለሕዝባችን እናሳውቃለን። ያን ጊዜ የትግበራና የክትትል ምዕራፍ ሥራችን ይጠናቀቃል ማለት ነው።



**ዘመን፡- ሥራችሁን የምታከናውኑት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚመደብላችሁ በጀት ብቻ ነው ወይስ ከሌሎች አካላት የምታገኙት እገዛ አለ ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** መንግሥት አዋጅ አስቀምጧል። እኔ ጣልቃ አልገባባችሁም ሥራችሁን የምትሠሩበት ሕንጻ ሰጥቼያችኋለሁ፤ የሚያስፈልገውን ነገር አቀርባለሁ፤ የምትጠይቁትን በጀት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርባችሁ ማስፈቀድ ትችላላችሁ ባለው መሠረት እንዲሁም እኛ በቀጥታ ተጠሪነታችን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለሆነ የሚያስፈልገንን በጀት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርበን አጸድቀናል። አብዛኛው ሥራ 2015 ላይ የሚከናወን ነው ብለን ስላሰብን ወደ ሦስት ቢሊዮን ብር ገደማ ነበር የጠየቅነው። ይህን ገንዘብ እንደ ድህነታችን እንደጊዜው ሁኔታ በጥንቃቄ የተወሰነ ገንዘብ ከገንዘብ ሚኒስቴር እየወሰደን በመጠቀም ላይ ነን።

ሥራችንን እንደጀመርን ብዙ የውጭ ድርጅቶች ገንዘብ እንርዳችሁና ኤክስፐርት እንስጣችሁ አይነት ጥያቄዎች አቅርበውልን ነበር፣ አይሆንም ነው ያልነው። ይሄ ኢትዮጵያዊ ፕሮግራም ስለሆነ ከሀገራችን በምናገኘው በጀት መወሰን መቻል አለብን። ገንዘብም ከፈለግን ከሀገራችን ውስጥ ማግኘት አለብን። እናንተ ገንዘብ የምትሰጡንም ከሆነ ቋት ገንዘብ ሚኒስቴር

ውስጥ አስቀምጠንላችኋል እዚያ ክተቱ በገንዘብ ሚኒስቴር ሕግና ደምብ መሠረት ከዚያ እያወጣን እንጠቀምበታለን እንጂ ገንዘብ ወደ እኛ ቤት መምጣት አይገባውም ብለን ነው ለፈረንጆቹ የነገርናቸው። ምክንያቱም ፈረንጆቹ እጆቻቸው በጣም የረዘሙ ናቸው። የረዘሙ እጆቻቸው ምን እንደሚሠሩ አስተውለናል።

በተለየ ሁኔታ ግን የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም ላለፈው ዓመት ወደ 80 ሚሊዮን ብር ገደማ መድቦልን ለሥራችን የሚያስፈልጉንን መኪኖች፣ ኮምፒዩተሮችና የመሳሰሉትን ነገሮች ገዝተን የእኛን የገንዘብ ሚኒስቴርን በጀት ሳንጠቀም እዚህ ደርሰናል። ወደፊትም እናግዛችሁ የሚሉን ዓለም አቀፍ ተቋማት ካሉ በዚህ መሠረት ብቻ ነው የምንቀበለው። ይሄ ሁሉ ጥንቃቄ የእኛን ተዓማኒነት እና ገለልተኝነት መጠበቅ ስላለብን ነው።

**ዘመን፡- ኮሚሽኑ ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ ምን አይነት ትምህርት ወስዷል ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** ባነበብናቸውና ባደረግናቸው ጥናቶች ብዙ ሀገሮች ውስጥ ውይይቶች ተካሂደዋል። የእኛ ግን ለየት ይላል። ለየት የሚልበት ምክንያት በተለያዩ ሀገራት የተደረጉት ውይይቶች በዓላማ የተደረጉ ናቸው። ዓላማ ምን ማለት ነው ለምሳሌ ኬንያ ውስጥ ምርጫ ተካሄደና በምርጫው ውጤት ባለመስማማት ብዙ ሕዝብ አለቀ። ስለዚህ ምን እናድርግ በሚል አጀንዳ ከላይ ወረደና በዚያ ላይ ተወያዩ። አጀንዳው ከላይ ከመውረዱ በተጨማሪ አወያያቸው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስር ይሠሩ የነበሩት ኮፊ አናን ስለነበሩ ውይይቱ የተመራው በጉልበተኛ ነው። እንደዚህ ዓይነት ውይይት የውጭ ተጽዕኖ ያለበት ነው። የውጭ ተጽእኖ ያለው ውይይት ደግሞ ዕድሜ አይኖረውም።

የሀገር ውስጥ ጉልበተኛ ተፅዕኖ ያለበት ውይይትም ወደ አሸናፊነት ብቻ የሚሄድ በመሆኑ ዕድሜ አይኖረውም። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በሱዳን ውስጥ የተካሄደው ውይይት ነው። አጀንዳዎች ተቀረጹ ሕዝቦች ተሰባሰቡ ውይይቶች ተጀመሩና በመሐሉ በወቅቱ የነበሩት ፕሬዚዳንት እጃቸው ረዝሞ ስለገቡበት ውይይቱ ከሸፈ። የመን ብዙ ዓመት ጦርነት ላይ ከቆየች በኋላ ውይይት እናድርግ ብለው ሴቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና ሌሎችም የተሳተፉበት በጣም ጥሩ የሚባል አካሄድ ተከትለው ነበር። የገልፍ ሀገሮች እጃቸውን አስረዝመው ውይይቱ ውስጥ በመግባት እኛ እንምራና ባልናችሁ መንገድ ሂዱ ማለት በመጀመራቸው ውይይቱ ከሸፈ። አሁን እንደሚታየው ዛሬም የመን ጦርነት ውስጥ ነው ያለችው። ሱዳንም እየተገራገጨች እዚህ ደርሳለች። ስለዚህ የብዙ ሀገሮች ውይይቶችን ስናይ አጀንዳ ከላይ ወደታች ይወርዳል ወይም የሀገሩ መንግሥት ጉልበተኛ ሆኖ ጣልቃ ይገባል አለበለዚያ ደግሞ የውጭ ሀገራት እጃቸው ረዝሞ ውይይቱ ውስጥ

## የእኛ ሥራ መገዳደል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲበቃ ተወያይተን አንድ መፍትሔ ላይ እንድንደርስ ማስቻል ነው።

ገብተው እኛ ካልመራነው በማለታቸው ምክንያት ይፈርሳል። ከእነዚህ አካሄዶች እኛ ብዙ እየተማርን ነው። በዚህ ምክንያት ለውይይቱ ሂደት ጥበቃ እናደርጋለን። የውጭ ጣልቃ ገብነት እንዳይኖርም በጥብቅ እንጠብቀዋለን።

የእኛ ውይይት የሚይዛቸው ሥራዎች በጣም ሰፊ ናቸው። ሌላ ሀገር እንደዚህ ተሄዶበታል ? በንባባችን አላገኘንም። ብዙ ጊዜ በቀሎ የሚያልቁ ትናንሽ አጀንዳዎች ናቸው የሚሆኑት። የተሳካላቸውን ሀገሮችን እንኳን ብንመለከት ቱኒዚያ ምስቅልቅል ብላ በነበረችብት በአንድ ወቅት የሆነው ምንድን ነው፣ ተሰባሰቡና የሠራተኛ ማኅበሩና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው በሙሉ አብረው ተወያይተው መንግሥት መሠረቱ። ያ መንግሥት በአሁኑ ሰዓት ቢያንስ በሥርዓት እየሄደ ነው ያለው። ቱኒዚያ ትንሽ ሀገር ነች እንደ እኛ ከ80 በላይ ቋንቋ እና ከ200 በላይ ከእነዚህ ቋንቋዎች የወጡ ዘዬዎች የሚነገርባት ሀገር አይደለችም። የሕዝቦቿ ቁጥር አነስተኛ መሆን ጠቅሟታል።

**ዘመን፡- በእስካሁኑ ጉዟችሁ ያጋጠሟችሁ ችግሮች እና የወሰዳችኋቸው የመፍትሔ እርምጃዎች አሉ ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** የእኛ ኮሚሽን የሥራ ዕድሜ ሦስት ዓመት ነው። ከሦስት ዓመቱ ላይ ዘጠኝ ወሩን እያነሳንለት ነው። ይሄ ዘጠኝ ወር ዝም ብሎ አይደለም ያለፈው። ከላይ እንደገለጽኩልህ እጅግ በጣም በርካታ መሠረታዊ ሥራዎች ሲሠሩበት ነው የከረመው። ብዙ ጊዜ ወገኖቻችን ከስሜት የተነሳ ለምን ዝም አሉ ወይም ድምጻቸው አይሰማም ወይም ደግሞ ቀን ቆጥረው ሦስት ዓመት ሲሞላቸው እንደቀደሙት ኮሚሽኖች ሊከስሙ ይችላሉ የሚል ፍራቻ አላቸው። በተለይ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የነበረው ጦርነት እና በየቦታው ያለው ግጭት ሕዝባችንን ስላሰለቸው፣ ብዙዎቹ እኛ የእርቀ ሰላም ኮሚሽን ሁሉ እንመስላቸዋለን። እርቅ የምናመጣ የምናደራድር ሁሉ ይመስላቸዋል። እርቅ የሚቀጥለው ውጤት ነው የሚሆነው። ወይም ደግሞ እርቀ ሰላም አይደለም ሥራችን። እርቀሰላም የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና የእናቶች ሥራ ነው። የእኛ ሥራ መጨረሻ ላይ ወደ ሀገራዊ እርቅ ማምጣት ነው። ቀደም ብሎ ከመጣም እሰየው፤ ይረዳናል። ምክንያቱም ሁለት በአካባቢ ጉዳይ የተጣሉ ወገኖች ቢታረቁ የታረቁበት ሁኔታ ዘላቂ ይሁን ከተባለ ውይይት ያስፈልጋቸዋል። አለበለዚያ በየአካባቢው ይጋጫሉ በሬ ያርዳሉ ይታረቃሉ በሚቀጥለው ቀን ደግሞ በግጦሽ መሬት መገዳደል ይጀምራሉ። የእኛ ሥራ መገዳደል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲበቃ ተወያይተን አንድ መፍትሔ ላይ እንድረስ ማስቻል ነው።

እንደምታውቀው ተፎካካሪዎቹን እና ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ በሀገራችን የተመዘገቡ 53 የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ። በተፎካካሪ ፓርቲዎች ዘንድ በመጀመሪያዎቹ ቀናት ጭምር የአዋጁን ሂደት አለመቀበል፤ እኛ የተመረጥንበትን ሂደት አለመቀበል አልፎ ተርፎም እኛን ይሄ ሰውዬ ወይም ያቺ ሴትዮ ከዚያ ነች ወይም ከዚህ ነች በማለት የነበሩ ጥርጣሬዎች ነበሩ። እነዚህን ሁሉ ነገሮች በየደረጃው ማጥራት ነበረብን። ከፖለቲካ ፓርቲዎች አመራር ጥምረታቸው ጋር መገናኘት ነበረብን። በሂደት ባደረግነው ክትትልና ሥራ ከ 53ቱ ውስጥ ከ40 በላይ የሚሆኑት ከእኛ ጋር አብረው ለመሥራት ተስማምተዋል። በቅርብ ጊዜ ውስጥ የስምምነት ማዕቀፍ እንፈራረማለን። ከተቀሩት ጋርም አብረን እንሠራለን ብዬ ነው የማስበው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አካላትም የተለያዩ ብዥታዎች እና ስሜቶች ነበሯቸው። አንዳንዶቹ አምባሳደሮች ለምሳሌ ሰሜን ውስጥ ሰላም ሳይሰፍን ወይም ጦርነት ሳይቆም ውይይት ማካሄድ ትችላላችሁ ወይ ይሉን ነበር። እኛ ደግሞ ሁለት ነገር ነበር የምንነግራቸው። አንደኛ እኛ ሕዝብ ጠቁሞን በአዋጅ ነው የተቋቋምነው። ተወዳድረን እዚህ ቦታ ካልገባን ብለን የመጣን ኮሚሽነሮች አይደለንም። እንዲህ ያለ ኃላፊነት ሲሰጠን ለሀገራችን የተወሰነች እንኳን ድርሻችንን እንወጣ ብለን ነው የመጣነው። እዚህ በመግባታችን ኃላፊነትን ከመሸከም ውጭ የምናገኘው ጥቅም የለም። አንዳንድ ኮሚሽነሮቻችን እንደውም ትልልቅ ሥራዎቻቸውንና የሚያገኟቸውን ከፍተኛ ክፍያዎች ትተው ነው ወደዚህ የመጡት፣ ብለን ያለውን ነገር በትክክል በማስረዳት አካሄዱ ሁለት ነገር ሊሆን እንደሚችል እንነግራቸዋለን።

አንዱ መንገድ በየቦታው ያለው የሰላም መደፈረስ እስኪቆም እጃችንን አጣጥፈን መቀመጥና መረጋጋት ሲኖር ሥራችንን መጀመር ነው። ሌላው ግን እየተዘጋጀን እና ሌሎች የሰላም ሂደቱን የሚጠርጉት እያመቻቹልን እኛም

ሁኔታዎችን እያመቻቸን ሰላም ባለበት ቦታ የውይይቱን ወይም የምክክሩን ሂደት እያጠናከርን ሌሎች ደግሞ ወደ ሰላም ሲመጡ ያንኑ አጠናክረን መሄድ ነው። ሁለተኛው አማራጭ የተሻለና ተገቢ መሆኑን መጀመሪያ በመላ ሀገሪቱ ሰላም መስፈን የለበትም ወይ ለሚሉን የሀገር ውስጥና የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አካላት እያስረዳን ቆይተናል። እንደ ዕድል ሆኖ የእግዚአብሔርም ፈቃድ ሆኖ ልክ እኛ እንዳልነውና እንደተመኘነው በአሁኑ ሰዓት ቢያንስ የሰሜኑ የሰላም ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል።

**ዘመን፡- አሁንም ድረስ ውይይቱ መፍትሔ አያመጣም የሚል አቋም በመያዝ ራሳቸውን ከሀገራዊ ምክክሩ ሊያገሉ እንደሚችሉ እየገለጹ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። እነዚህን ወገኖች ለማግባባት እያደረጋችሁ ያላችሁት ጥረት አለ ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** ከእኛ ጋር ለመሥራት ፍላጎት ካላሳዩት 10 እና ከዚያ በላይ ከሆኑት ፓርቲዎች ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እየተገናኘን እኛ ማን እንደሆን እንዲሁም ሥራችን የት ድረስ እንደሚሄድና የሥራ ኃላፊነታችን ምን ምን እንደሆነ በማስረዳት ላይ እንገኛለን። እኛ የውይይትን ሥራ የምናመቻችና የምናሳልጥ እንጂ ወሳኞች ስላልሆንን ይህንን እያሳወቅናቸው ነው።

ብዙ ሕዝብ ተቀብሎናል ያልሰሙንና ያልፈለጉን ጥቂት የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው ብለን እነሱን ወደ ኋላ መተው የለብንም። ምክንያቱም ለእነሱም ኢትዮጵያ ሀገራቸው ነች። ልዩነታችን እነሱ ሀገራችን ልትጓዝበት ይገባል ብለው የሚያምኑት ሌላ መንገድ በመሆኑ ነው ብዬ ነው የማስበው፤ ያ ደግሞ መብታቸው ነው። ነገር ግን እነሱም የመጨረሻ ግባቸው ሀገራቸው ኢትዮጵያ እስከሆነች ድረስ፣ እኛም የመጨረሻ ግባችን ሀገራችን ኢትዮጵያ እስከሆነች ድረስ እና የእኛ ሥራ የእነሱንም አጀንዳ ጭምር አካቶ ወደ ውይይት ማምጣት ስለሆነ ለእነሱም ጭምር ነው እየሠራን ያለነው። እነዚህ ያልተቀበሉን ወይም የተቃወሙን የፖለቲካ ፓርቲዎች ነገ ጠዋት ሁኔታዎች ከተመቻቹ ሀገር የሚመሩና የሚያስተዳድሩ ስለሆኑ ሕዝብ የተዋደደበትንና የተፋቀረበትን ጠንካራ ሀገርን መምራት ለፖለቲካ ፓርቲዎችም ትልቅ ዕድልና ጸጋ ይመስለኛል።

ከ40 በላይ ከሆኑት የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋርም አብረን ለመሥራት ስምምነት ላይ እስክንደርስ ድረስ የራሳቸው ጥርጣሬ ነበራቸው። አንዳንዶቹ በአዋጁ አቀራረጽ ሂደት ላይ ነው ችግራችን ያሉን አሉ። ሌሎች በኮሚሽኑ ስም ላይ ጥያቄ አንስተው የውይይትና የእርቀ ሰላም ኮሚሽን መሆን አለበት ያሉን አሉ። እናንተስ ምን ያህል ተዓማኒ ናችሁ? ከመንግሥት ጋር ወይም ከዚኛው ጋር ከዚያኛው ጋር ትወግናላችሁ ያሉን ነበሩ። እኛ የሰጠናቸው መልስ አዋጅ ጸድቆ እኛ እንዴት እንደተጠቆምን ባላወቅንበት ሁኔታ ለዚህ ሥራ ተሰይመናል።

**"ከጥቂት ጊዜ በኋላ በየክልሉ ጽሕፈት ቤቶችን እንከፍታለን። የምንከፍታቸው ጽሕፈት ቤቶች በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንዲሆኑ ነው የወሰንነው"**

አብራችሁን በመሥራት እዩን፣ እንደምትሉት ሳይሆን ገለልተኝነታችንና ተዓማኒነታችን የሚታይ ነው የሚሆነው። ተዓማኒነታችን ብዙም የሚያስደነግጥ አይደለም፣ ምክንያቱም ሕዝብን ነው የምናወያየው፤ የሚወስነውም ሕዝብ ነው። ራሱ ተወያዩ እንጂ እኛ ሀገር እንዲህ ትሁን ብለን አቅጣጫ አንሰጥም ስለዚህ አብረን እንሥራ የሚል ነው።

የእኛ ትልቁ ኃላፊነት ሂደቱን በሥርዓት መርተን ውጤቱን በትክክል ጠምረን ተከታትለን እስከ መጨረሻው ድረስ ሄደን መሠራትና አለመሠራቱን ማረጋገጥ ነው። ተስፋ እማደርገው ቅቡልነቱ እየሰፋ እንደሚሄድ ነው፤ እየሆነም ያለው እንደዛ ነው።

**ዘመን፡- ከመንግሥት የምትፈልጉት ድጋፍ እያገኛችሁ ነው ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** መንግሥት ሀገራዊ ምክክሩ ትልቅ ፕሮግራም መሆኑን አምኖበት አዋጅም እንዲወጣ አመቻችቶ እዚህ አድርሶናል። የሚሰጠን ገንዘብ ሁልጊዜም እንደምለው የሕዝብ ገንዘብ ነው። እኔም አንተም ታክስ የምንከፍለውን ገንዘብ ነው መልሶ የሚያደላድለን። በየክልሎች ስንሄድም የክልል መንግሥታት ሁኔታዎችን አመቻችተውልናል፣ በሚችሉት እረድተውናል አግዘውናል።

ከጥቂት ጊዜያት በኋላ በየክልሉ ጽሕፈት ቤቶችን እንከፍታለን። የምንከፍታቸው ጽሕፈት ቤቶች በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንዲሆኑ ነው የወሰንነው። ስለዚህ ከፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች ስብስብ ጋር የስምምነት ማዕቀፍ ተፈራርመናል። በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንዲሆን የፈለግነው ኢትዮጵያን የሚወክሉ በመሆናቸው ነው። ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ከሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሄዱ የሁላችንም ልጆች ናቸው። ወጣቶች የሀገራቸው ጉዳይ ስለሚመለከታቸው በዚህ በእኛ ሥራ ሂደት ውስጥ መሳተፍ አለባቸው። አወያይ ሊሆኑ ይችላሉ። አስተማሪዎቻቸው ይሳተፉበታል በመጨረሻም ሁሉንም ባይሆን እንኳን የተወሰነውን ሥራችንን ሠርተን እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መግባባት ላይ ደርሰን ቢያንስ ለዴሞክራሲ መሠረት ጥለን ስንወጣ በየዩኒቨርስቲው ያሉት ልጆቻችን የጀመርነውን ነገር ያስቀጥሉታል።


ቢያንስ ቢያንስ የሚኖረንን ነገር እዚያው ትተንላቸው ስለምንወጣ ተቋማቱ የሰላም ግንባታ እና የምርምር ማዕከላት ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ተስፋ ነው ያለኝ። ምክንያቱም የጸብ መነሻም ሆነ የሰላም ግንባታ ቦታ ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው። ዩኒቨርሲቲዎች ሳይንስ ላይ ብቻ አይደለም ማተኮር ያለባቸው አብሮ መኖር ላይ እና አብሮ መሥራት ላይም ማተኮር አለባቸው። ያንን እያዳበሩ ሲሄዱ ነው ትልቅ ሀገር ሊገነቡ የሚችሉት።

**ዘመን፡- በአንድ ወቅት ከአንድ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቆይታ መንግሥት ጣልቃ የሚገባ ከሆነ ሥራዎን እንደሚለቁ ገልጸው ነበር። እስካሁን ከመንግሥት በኩል የገጠማችሁ ጣልቃ ገብነት አለ ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** ምንም ነገር የለም። አንደኛ እኔ ቀጥታ ሪፖርት የማደርገው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ነው። አፈ ጉባኤው ከመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ከቃለ መሐላችን ስንወጣ ያሉን ነገር ቢኖር እናንተ በተቻለ መጠን ገለልተኛና ተዓማኒ ሆናችሁ መሥራት ነው ያለባችሁ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በጭራሽ ወደ እናንተ ውስጥ አይመጣም ነው ያሉት። ያንን ጥያቄ እንደዛ የመለስኩት ለምንድን ነው ጥያቄው በእንደዛ አይነት መልኩ ተቃኝቶ ስለመጣ ነው። መንግሥት መጀመሪያውኑ እንዳይቋቋም ማድረግ ሲችል ለምን ጣልቃ ይገባል? በነገራችን ላይ ልክ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሊጠቀሙ እንደሚችሉት ሁሉ መንግሥትም ተጠቃሚ ነው የሚሆነው። አሁን አስተውለህ ከሆነ ብዙ ሥራዎች ወደ ሀገራዊ ምክክር እየመጡ ነው። ምክንያቱ ምንድን ነው፣ የመጨረሻው ወሳኝ ሕዝብ ስለሚሆን መንግሥትም ታጋዥ ነው የሚሆነው። ይሄ ሥራ የተሳካለት ቢሆን ተምሳሌታዊ ሥራ ሠራ የሚባለው ወገናችን፣ ሕዝባችንና ሀገራችን ስለሆነ ተጠቃሚ ነው የሚሆነው።

**ዘመን፡- ሁለተኛው ምዕራፍ ተገባዶ ምክክሩ ሊጀመር ጥቂት ጊዜ ነው የቀረው። ትግራይ ክልል በነበረው ሁኔታ ምክንያት እንደሌሎች አካባቢዎች የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች አልተሠሩም። በቀረው አጭር ጊዜ ክልሉን በውይይቱ ለማሳተፍ ምን ታስቧል?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** በአጋጣሚ እኔ አልነበርኩበትም እንጂ በቅርቡ ኮሚሽነሮቻችን ወደ ትግራይ ሄደው ነበር። እኔ በኢትዮጵያ የሀገር ሽማግሌዎች ካውንስል ውስጥ ሰብሳቢ ሆኜ ሰላምን በሚመለከት በተደጋጋሚ ወደ ትግራይም ወደ አማራም ወደ ብዙ ክልሎች ሄጄ ነበር። እንደ ዕድል ሆኖ ጦርነቱ ከመከሰቱ በፊት ሁሉ በመጨረሻ ሰዓት መቀሌ ሄጃለሁ። በኋላም ላይ ጊዜያዊ አስተዳደር በተጀመረበትም



**ወደ ውይይት ሲመጣ መጀመሪያ መቀመጥ ያለበት መሣሪያ ነው። መጀመሪያ እኔና አንተ ወደ ውይይት የምንመጣው አንተም ፈልገህ እኔም ፈልጌ ነው። አንተ ሳትፈልግ እኔ በግድ ባመጣህ የጉልበት ክርክርና ጭቅጭቅ እንጂ ውይይት አይሆንም።**

ጊዜ ጭምር ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር የመሄድ ዕድል ነበረኝ። ይሄ ብቻ ሳይሆን ወጣት ሐኪም ሆኜ ትግራይ ስለሠራሁ ለሕዝቡ በጣም ከፍተኛ ፍቅር አለኝ። ችግር ውስጥ በነበረበት በቀይ ኮከብ ዘመቻ ጊዜ ነው ያንን ሕዝብ የማውቀው። ምን አይነት ኢትዮጵያዊ ሕዝብና ወገን ወዳድ እንደሆነ አውቃለሁ። ዋናው ነገር አሁን ሰላሙ እየመጣና እየተጠናከረ ከሄደ በሌሎች ክልሎች በሚገኙ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች እንደምናደርገው ሁሉ በትግራይ ክልልም ጽሕፈት ቤታችንን በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ እንከፍታለን ብዬ ነው ተስፋ የማደርገው። ያ ማለት በክልሉ ውስጥ ባሉት ዞኖች ሁሉ በሌሎች ቦታዎች ስንሠራቸው የነበሩትን ሥራዎች እንቀጥላለን።

ለዚህ ውይይት የዚያ አካባቢ ሕዝብ የበለጠ የሚዘጋጅበት ይሆናል ብዬ ነው የማምነው። ምክንያቱም ጦርነትን የአካባቢው ሕዝብ ላለፉት 50 ዓመታት በሚገባ ያውቀዋል። በታሪክ ወደኋላ ከሄድን ምናልባት ብዙ መቶ ዓመታትም ወደ ኋላ ሊወስድ ይችላል። አካባቢው የሀገር በር በመሆኑ ብዙዎቹ ጦርነቶች በዚያ ስለሚያልፉ የአካባቢው ሕዝብ ለብዙ መቶ ዓመታት ለችግርና ለጦርነት ተጋላጭ ነው። ያለፉት 50 ዓመታት ደግሞ ከተመለከትን ብዙ የተፈተነ ሕዝብ ስለሆነ በእርግጠኝነት ከነፍጥ ይለቅ ቁጭ ብሎ መወያየት እንደሚቻል ከማንኛውም አካባቢ ባላነሰ ግንዛቤ ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ።

**ዘመን፡- ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም አካታች ከሆነ በተለያየ የሀገሪቱ ክፍል የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ቡድኖች ወደ መድረኩ ሊጋበዙ ይገባል የሚሉ ወገኖች አሉ። በዚህ ላይ የኮሚሽኑ አቋም ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** ወደ ውይይት ሲመጣ መጀመሪያ መቀመጥ ያለበት መሣሪያ ነው። መጀመሪያ እኔና አንተ ወደ ውይይት የምንመጣው አንተም ፈልገህ እኔም ፈልጌ ነው። አንተ ሳትፈልግ እኔ በግድ ባመጣህ የጉልበት ክርክርና ጭቅጭቅ እንጂ ውይይት አይሆንም። ውይይት ሁለታችንም የምናሸንፍበት እስከሆነ ድረስ ሁለታችንም መሣሪያችንን አስቀምጠን ሰላምን አንግበን ነው የምንመጣው። ለሰላም ፍላጎቱ እስካለና ጥያቄው ከዛ እስከመጣ ድረስ እኛ ሽብርተኝነትን እስከማስነሳትና ለዚህ ውይይት የሚመጡትን ደህንነት እስከማስጠበቅ ድረስ እንሄዳለን። ለምሳሌ ሽብርተኛ ተብሎ በውይይት ላይ መቀመጥ አይችልም። ስለዚህ እኛ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ይሄ አካል ለውይይት ስለመጣ የሽብርተኝነት ስያሜው ይነሳለት ብለን የመጠየቅ መብት አለን። በእርግጥ የሀገሩ ሕግና አካሄድ ምን እንደሚልና ምን ሊል እንደሚችል ባላውቅም ያንን እስከመጠየቅ ድረስ መብት እንዳለን ግን ከጅምሩ ጀምሮ አፈጉባኤው አረጋግጠውልናል።

ስለሰላም እስከተመጣ ድረስ ለሰላም የማይከፈል አቋም የለም። ለሰላም በሚከፈል መስዋዕትነት ውስጥ ደግሞ ሕይወት አይጠፉም። ለምን ? ጠብመንጃ ቁጭ ብሏል። ይሄንን ነው እኔ ሁልጊዜ የምናገረው። ይሄ የግል አቋሜ ነው በእርግጠኝነት ሌሎቹም ባልደረቦቼ ኮሚሽነሮች ከዚህ ብዙ የወጣ አቋም ይኖራቸዋል ብዬ አላስብም።

**ዘመን፡- በምዕራብ ኢትዮጵያ በሚንቀሳቀሱት ኃይሎች በኩል በሀገራዊ ውይይቱ ለመሳተፍ ፍላጎት የሚኖር ከሆነ ኮሚሽኑ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄ ያቀርባል ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** ግዴታችንም ነው እንጂ። ምዕራብ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሕዝባችን ከየትኛውም አካባቢ በላይ ሰላም የጠማው ነው። ምክንያቱም የደረሰውን ችግር እናውቃለን። እዛ ያሉ ኃይሎች የለም በቃ ያተረፍነውን ነገር አየነው፣ እኛ በሀሳብ ለማሸነፍ ወደ ውይይቱ እንመጣለን ካሉ እነኚህ አካላት በአጀንዳ ቀረጻው ሂደት ውስጥ ለመወያየት ዝግጁ ናቸው ብለን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄ እናቀርባለን። ሄደን እናንተን አያገባችሁም የሚል መልስ የሚሰጠን ከሆነ ደግሞ ያንንም ለሕዝባችን እንነግራለን። እኛን እዚህ አስቀምጦናል ብለን የምናምነው

ሕዝባችንን ነው፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቃለ መሐላ የፈጸምነው ለዛ ነው። ስለዚህ የጠየቅነው ነገር ሲፈጸምም ሆነ ሳይፈጸም ሲቀር ለሕዝባችን እንነግራለን።

**ዘመን፡- ኮሚሽኑ ለእነዚህ ኃይሎች በቀጥታ ጥያቄ ያቀርባል ወይስ በራሳቸው ወደ መድረኩ ለመምጣት ፍላጎት ማሳየት ይጠበቅባቸዋል?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** እኛ እንግዲህ በቀጥታ መንገዱ የለንም። ለምሳሌ ባለፉት ሁለት ዓመታት ፍላጎቱ ቢኖረንም ትግራይ አልሄድንም። መንገዱ መመቻቸትና ፈቃዱ ከዚህም ከዚያም መገኘት መቻል አለበት። ከምታነሳቸው ኃይሎች በኩል ጥያቄው ከመጣ ግን ያንን ጥያቄ የማስተናገድ ኃላፊነት አለብን። አሁን የት ሄዳችሁ ከማን ጋር ነው የምትነጋገሩት ብትለኝ የት ጋርና ማን ምን እንደሆነ በማላውቅበት ይሄ ነው ልልህ የምችለው ሁኔታ ግን የለም።

**ዘመን፡- ሥራችሁ እጅግ በጣም ሰፊ ነው። ኮሚሽኑ የተጣለበትን ኃላፊነት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ይወጣል ብለው ያምናሉ ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** አላምንም። የተሰጠን ኃላፊነት በጣም ብዙ ነው። ነገር ግን መሠረታዊ ሥራዎችን እንሠራለን ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም የኢትዮጵያ እጅግ መሠረታዊ ችግሮች ጥቂት ልሂቃን እንደምናምነው አንድ ሁለት ሦስት ብቻ ናቸው ብዬ አላስብም። የሀገራችንን ችግር በሚገባ እንመልከተውና እንሂድበት ሙሉ ለሙሉ ወደ መግባባት እንምጣ ከተባለ በጣም በርካታ ይሆናሉ ብዬ አምናለሁ። ያ ሁሉ በዚህች በቀረችው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልቃል የሚል የዋህ አመለካከት የለኝም። እኔ የማምነው ግን በተወሰኑ እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መወያየት ምን እንደሚመስል በማሳየት ለሕዝባችን አካሄዱን በሚገባ አስቀምጠን እናስተላልፋለን ብዬ ነው። ይህ ትልቅ ነገር ነው። ለዴሞክራሲም መደላድል በር ይከፍታል።

ብዙ ጊዜ እዚህ ሀገር ሲነገር የምሰማው ውይይት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን አዲስ አይደለም የሚባል ነገር አለ። አላውቅም፣ እሱን ለመሞገት ፈልጋለሁ። ለምን እኛ የተዋረድ ማኅበረሰብ ነን። በአንድ ቤት ውስጥ አባትና እናት አሉ። አባት ወይም እናት የበላይ ነን የሚሉበት ልጆች ደግሞ ከታች የሆኑበት ኅብረተሰብ ነው ያለን። በእኛ ኅብረተሰብ ውስጥ ሥልጣኑ ትልቁ የሀገር ሽማግሌ ወይም ትልቁ የሃይማኖት አባት ዘንድ ነው የሚሆነው። በዚህ መልኩ የተዋረደ ኅብረተሰብ መሆናችን ጥሩ ነገር ነው፤ እሱም ነው ለብዙ ሺህ ዓመታት የጠበቀን ብዬ አምናለሁ። አሁን ግን ስለውይይት በምንነጋገርበት ጊዜ የ 18 አመት ወጣትም ሆነ የ80 አመት አረጋዊ ወይም እናት ቁጭ ብለው እነኚህ ናቸው አጀንዳዎቻችን ብለው ይወያያሉ።

አዋጁ ለሦስት ዓመታት ነው ይሄን ኮሚሽን ያቋቋመው እንደአስፈላጊነቱ ይራዘማል ይላል። እንደአስፈላጊነቱ ሲራዘም አንዳንዶቻችን በጡረታ ዕድሜ እያገለገልን ስላለን ሊረዝምብን ይችላል። ስለዚህ በዚህ የሥራ ሂደት ውስጥ በትክክል መተካካት ሊኖር ይገባል ብዬ አምናለሁ። ከላይ እንደጠቀስኩልህ ሁሉ ነገር ላይ የግድ መግባባት ላይ እንደርሳለን ማለት አይደለም። ባለመግባባትም ተግባብቶ መቀጠል ቀላል ነገር አይደለም። ስለዚህ ያልጨረስናቸውን አጀንዳዎች ሕዝብ እስካመነበት ድረስ በቀጣይ ይሄው ተቋም ተረክቦ ሊያስኬዳቸው ይችላል።

**ዘመን፡- ከተለያዩ አካላት ጋር በጋራ ለመሥራት የመግባቢያ ስምምነቶችን ተፈራርማችኋል። ስምምነቶቹ ምን እያስገኙ ነው ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** የሁለትዮሽ ስምምነቶች ከሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማት ጋር ተፈራርመናል። እነዚህ የሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማት የሚሠሩልን በተለይ ግንዛቤ ማስጨበጡ ሂደት ላይ ታች ድረስ ሄደው ስለሆነ የሚሠሩት ብዙ እገዛዎችን ያደርጉልናል ብዬ አምናለሁ። ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ስንፈራረም ዋናው ዓላማ ፓርቲዎቹ ተከታዮቻቸው በትክክል በውይይቱ ሂደት ላይ እንዲሳተፉ እንዲያስችሉ ነው። ስለዚህ ከአካል ጉዳተኞችም ማኅበር ሆነ ከሌሎች ማኅበራትም ጋር የምንፈራረማቸው ስምምነቶች ዓላማቸው የራሳቸውን ተከታዮች እንዲያነቁልን ማስቻል ነው። ያ ማለት የእኛ ሥራ ወደ ኅብረተሰቡ በቀላሉ እንዲሰርጽ ያስችላል። ምክንያቱም ኅብረተሰቡ ጋር ያሉት እነሱ እንጂ እኛ እዚህ ማዕከል ያለነው አይደለንም። በነገራችን ላይ ይሄ ሚዲያና ተግባቦት ማዕከላትንም ይመለከታል። ለምሳሌ በቅርቡ ከሶሻል ሚዲያው ማኅበረሰብ ጋር አንድ ስብሰባ አካሂደናል፤ ወደፊትም የሚቀጥል ይሆናል።

**ዘመን፡- በቅርቡ ፍትሕ ሚኒስቴር የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮችን አርቅቆ ለባለድርሻ አካላት ለውይይት አቅርቧል። እርስዎ የሚመሩት ኮሚሽን ሥራ ውጤታማ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የሽግግር ፖሊሲው የሚኖረውን ሚና እንዴት ይገልጹታል ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** ውይይት መግባባትን ያመጣል። ከመግባባት ቀጥሎ ደግሞ የሚመጡ አሉ። ሀገራዊ እርቅ ወይም የሽግግር ፍትሕ ሊሆን ይችላል። ብዙ በደሎች በሀገራችን ላይ ደርሰዋል። ባለፉት 50፣ 60፣ 100 የፈለገውን መቁጠር እንችላለን፣ በቅርብ ጊዜም የደረሱ አሉ። እነኚህ በደሎች ፍትሕ ይፈልጋሉ። ፍትሕ ማለት የግድ እሰረው ቁረጠው ግደለው ስቀለው ማለት አይደለም። ቢያንስ አንዳችን በአንዳችን ላይ በደል ማድረሳችንን ተማምነን ወደፊት ይሄ እንዳይደገም ተስማምተን፣ በደል ያደረስን ጸጸታችንን ገልጸን ይቅርታችንን ጠይቀን፤ በደል የደረሰባቸው በደል ያደረሱትን ጸጸትና ይቅርታ ተቀብለው ተክሰው ወደፊት መቀጠል መቻል አለብን። ስለዚህ የሽግግር ፍትሕ ብዙ ነገሮችን ነው የሚያካትተው። ቀጥታ ፍርድ ቤት መሄዱ እና እዚያ የሚተላለፈው ቅጣት እንዳለ ሆኖ ሕዝቦች ይቅር ባይ ናቸውና፣ እስካሁንም ድረስ ያስተዋልነው ይሄ ስለሆነ ወደፊት የሚቀጥሉበትን መንገድ የሚያመቻቹት እነሱ ናቸው። ስለዚህ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው በኋላ ላይ የሚደረስበት ውጤት ነው የሚሆነው። ከእኛ ሥራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የለውም ነገር ግን በውይይቱ የሚደረስበት የጋራ መግባባት ወደዚያ ስለሚያመጣን ከፍትሕ ሚኒስቴር ጋር ተነጋግረንበታል።

**ዘመን፡- በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር እንዲሳካ ከማን ምን ይጠበቃል ይላሉ ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑን ሥራና ኃላፊነቶች አዋጁንም በሚገባ በጥንቃቄ ተረድቶና አውቆ አብሮ በጋራ መሥራት የበለጠ ይጠቅመናል ብዬ አስባለሁ። በብዛትና በኃይል ልዩነቶቻችን ላይ ስለሠራን አሁን የደረስንበት ላይ ደርሰናል። ምናልባት ሀገራዊ ውይይቱ ወደ አንድ ምዕራፍ ያመጣናል ብዬ አምናለሁ። ስለዚህ እኔ በራሴ የማምነው የጦርነትን አስከፊነት አይተናል። በጦርነት ሰላም አይመጣም። በጦርነት ሰላም የሚመስል ነገር ማምጣት ይቻል ካልሆነ በስተቀር ዘላቂ የሆነ ወንድማማችነትና እህትማማችነት ሊመጣ የሚችለው ቁጭ ብሎ መሣሪያን አስቀምጦ መወያየት ሲቻል እንደሆነ በየጊዜው እንናገራለን። ይሄ የምንለው ነገር አሁን እየመጣ ነው ያለው። የሰሜኑ ሰላም ለምዕራብ ኢትዮጵያም ሰላም መምጣት በር ይከፍታል የሚል እምነት አለኝ። ምክንያቱም በዚህ በጦርነት ያየነው አሳርና መከራ ነው። ወጣቶቻችንን አጣን፤ ብዙ ጉዳት ደረሰ፤ ንብረቶች ወደሙ፤ በድህነታችን ላይ ተጨማሪ ድህነቶችን ነው ስንጭምር የከረምነው። መጠራጠርን ነው ስንጨምር የከረምነው። ለብዙ ሺህ ዓመታት አብረው የኖሩ ወገኖቻችንና ሕዝቦቻችን ላይ ነው ሰቆቃ ስንደርብባቸው የከረምነው።

ኮሚሽናችን የተቋቋመበት አዋጅ የሚለው ምንም እንኳን ብዙ የሚያግባቡ ነገሮች ቢኖሩንም ከጊዜ ወደጊዜ ግን አንዳንድ እጅግ መሠረታዊ የሆኑ የማያግባቡን ነገሮች በመኖራቸውና እነኚያም ለግጭትና አልፎም ለጦርነት ስለዳረጉን ሕዝቦቻችን በማያግባቡን ነገሮች ላይ ተወያይተው ወደፊት ሀገራችን ኢትዮጵያ ሰላማዊ የምትሆንበትን መንገድ ይመቻች ነው። ስለዚህ ውይይት በሚባልበት ጊዜ ተወያዮቹን መግባባት ላይ ማድረስ ነው። መግባባት ላይ እንኳን ባንደርስ ከነአለመግባባታችን ተግባብተን እንድንቀጥል ማስቻል ማለት ነው። ከነአለመግባባታችን ተግባብተን እንቀጥል ማለት አንድ ቀን ያላግባቡን ነገሮች ይፈታሉ ማለት ነው። ስለዚህ ውይይት እንጂ ጦርነት እና መሳሪያ ጥቅም የለውም።

**ዘመን፡- ለጥያቄዎቻችን የተብራራ ምላሽ ስለሰጡን እናመሰግናለን።**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# አገር የማብላው ነቀዝ



አቶ አመሃ መኮንን

> ሙስና በተባለው ደረጃ ምናልባትም ከተባለው ደረጃ በከፋ ሁኔታ በአገራችን ተንሰራፍቷል።

> የአገልግሎት አሰጣጡ ሙስና የነገሰበት በመሆኑ ስርዓቱን መፈተሽና መሰረታዊ ምንጩን በማግኘት መሰረታዊ ለውጥ ማድረግ እስካልተቻለ ድረስ እንዲሁ በቀላሉ የሚቆም አይደለም።



ዶክተር ራሔል ባፌ

**ተስፋ ፈሩ**

በአማርኛ ቋንቋ “ሙስና” የሚለው ቃል “corruption” ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል አቻ ትርጉም የሚሰጥ ሆኖ ግልጋሎት እየሰጠ ነው። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር ማዕከል በ1993 ዓ.ም ያሳተመው አማርኛ መዝገበ ቃላት ገጽ 67 ላይ “ሙስና” የሚለውን ቃል በስልጣን ወይም በስራ ድርሻ አላግባብ የመገልገል፣ የመጠቀም ወይም የመጥቀም ድርጊት ነው ሲል ይበይነዋል። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 404 ንዑስ አንቀጽ ሦስት ‹ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በተሰጠው ኃላፊነት ወይም ተግባር ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት የተሰጠውን ስልጣን ወይም የሕዝብ አደራ ያላግባብ የተገለገለበት እንደሆነ ወይም ማንኛውም ሰው ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማሰብ፣ ለመንግስት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለመስጠት ቃል የገባ፣ ያቀረበ፣ የሰጠ፣ ወይም ለማቅረብ የተስማማ እንደሆነ› ሲል የሙስናን ምንነት ይገልጻል።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ አደረጃጀቶች ሙስናን ለመከላከል ስትታገል ቆይታ በ1993 ዓ.ም የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን ተቋቁሞ የፀረ-ሙስና ትግሉን በፌዴራል ደረጃ እንዲያስተባብርና እንዲመራ ተደርጓል። በተዋረድም በክልሎችም ተመሳሳይ ስልጣንና ተግባር ያላቸው ኮሚሽኖች ተቋቁመው የጸረ ሙስና ትግሉን በክልል ደረጃ የመምራትና የማስተባበር ስራ ሲሰሩ ቆይተዋል። በኋላም በአዋጅ ቁጥር 1236 /2013 የፌዴራል የስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ለማሻሻል አዲስ አዋጅ ወጥቷል።

በአዲሱ አዋጅ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ ሙስና እና ብልሹ አሰራር የአገራችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት የሚገታ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ የህግ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤ በአገራችን የተጀመረውን የልማት፣ የሰላም እና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል በመልካም ስነ ምግባር የተገነባ፣ ሙስናን የሚፀየፍ፣ በፅናት የሚታገል ህብረተሰብ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤ የኮሚሽኑ አሠራር የግልጽነት እና የተጠያቂነት መርሆዎችን የተከተለ እንዲሆን በማድረግ ኮሚሽኑ ተቋማዊ እና የአሰራር ነፃነት እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤ ለኮሚሽኑ በተለያዩ አዋጆች የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በአንድ ላይ ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እና ኮሚሽኑ በአገር ደረጃ የፀረ ሙስና ትግሉን የመምራት እና የማስተባበር ሚናውን ለመወጣት የሚያስፈልገውን የኃላፊነት ወሰን በህግ መደንገግ በማስፈለጉ፤ የሙስና መከላከል ተግባር በአንድ ተቋም ተጀምሮ የሚጠናቀቅ ባለመሆኑ ኮሚሽኑ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት የህግ ድጋፍ እንዲኖረው በማድረግ ከፀረ ሙስና ትግል አኳያ በዓለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃ አገሪቱን በብቃት እንዲወከል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው ማሻሻያው ያስፈለገው።

የጸረ ሙስና ትግሉን የሚያግዙ የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ተቋማዊ ስራዎች ሲከናወኑ ቢቆዩም የሚወሰዱት እርምጃዎች የዘመቻ መልክ የነበራቸው ነበሩ። ይህ ደግሞ፣ ሙስና እና ሙሰኞች ጉልበት እንዲያገኙና ለአገር ፈተና የሆኑበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ አድርጓቸዋል። በየዓመቱ የአገራትን የሙስና ተጋላጭነት ይፋ የሚያደርገው ዓለምአቀፉ ፀረ-ሙስና ጥምረት ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ2022 ባወጣው መረጃ መሰረት ኢትዮጵያ ከ180 አገራት 87ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ይሄው ተቋም ከ10 ዓመታት በፊት በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር የ2012 ባወጣው የአገሮች የሙስና ደረጃ ከተፈተሹት ከ174 አገሮች ኢትዮጵያን 113ኛ ላይ አስፍሯት ነበር። ዛሬ የኢትዮጵያ መንግስት ሙስና የአገር የደኅንነት ሥጋት መሆን ደረጃ ላይ እንደደረሰ እየገለጸ ባለበትና የተፈታሽ አገራት ቁጥር ከ174 ወደ 180 ከፍ ባለበት ሁኔታ ኢትዮጵያ 26 ደረጃዎችን ማሻሻሏ በሌሎች አገራት ሙስና ፍጹም ያየለበት ሁኔታ ካልኖረ በቀር አጠያያቂ ይመስላል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በቅርቡ የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋሙን ይፋ ሲያደርጉ ሙስና ዛሬ የአገራችን የደኅንነት ሥጋት ሆኗል። ኢትዮጵያ ወደ ብልጽግና የምታደርገውን ጉዞ እጅ ተወርች አሥሮ ለመያዝ ከጠላቶቻችን እኩል ሙሰኛው እየታገለን ነው። የተስተካከለ ቢሮክራሲ፣ የተቀናጀ መዋቅርና ዘመናዊ አሠራር ለሙስና ተጋላጭነትን ስለሚቀንሱ፣ እነዚህን ለማጥፋት ወይም ለማሰናከል ሙሰኛው ቀን ከሌት እየሠራ

ነው። ሕዝባችን በአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከመሬት ጋር በተያያዙ አሠራሮች፣ በፋይናንስ ዘርፍ፣ በሽያጭና ግዥ ሂደቶች፣ በፍትሕ አደባባዮች፣ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች፣ የህዝብ ተቋማት ወዘተ. በሚያጋጥመው ሙስና እየተማረረ ነው። በተለያዩ ጊዜያት ከሕዝብ ጋር በተደረጉ ውይይቶች ከጸጥታ ሥጋቶች እኩል ሙስና የብልጽግና ጉዟችን ዋናው ዕንቅፋት መሆኑን አንሥቷል በማለት ሙስና የደረሰበትን ደረጃ ገልጸዋል።

የህግ ባለሙያው አቶ አመሃ መኮንን ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደ መንግስት ኃላፊነታቸው እንዲህ አይነት መግለጫ ሲሰጡ የአሁኑ የመጀመሪያ አለመሆኑን ይገልጻሉ። ሙስና በተባለው ደረጃ ምናልባትም ከተባለው ደረጃ በከፋ ሁኔታ በአገራችን ተንሰራፍቷል። በተለይም በመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና በፍርድ ቤቶች አካባቢ ህዝቡን ያማረረ እንደነበረና አሁንም እንደሆነ የሚታወቅ ሀቅ ነው። ህዝቡም በብዛት በምሬት የሚናገረው ጉዳይ ነው። አሁን መንግስት የሚታገሰው አይደለም የአገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ አደጋ ደቅኗል ብሎ ከመምጣቱ በስተቀር በበርካታ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አካባቢ ያለጉቦ አገልግሎት መስጠት የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ሲሉም ያክላሉ።

ሙስናን ለመታገል በሚል ቀደም ሲልም የጸረ ሙስና ኮሚሽን ተቋቁሞ እንደነበር በማስታወስም፣ ይሄ ተቋም በአንድ ወቅት ከማስተማርና ከመከታተል ባለፈ በሙስና የሚጠረጠሩ የመንግስት አካላትን የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ሁሉ ነበረው በኋላ ይህ ስልጣን ከእጁ ወጥቶ ወደ ፌዴራል አቃቢ ህግ የዞረበትን ሁኔታ እናውቃለን። ይሄ ተቋም ያደረገው አስተዋጽኦ ነበረ፣ ነገር ግን የሙስና ወንጀልን የመመርመርና የመክሰስ ስልጣኑን ካጣ በኋላ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እየተወጣ ነበር ለማለት ያስቸግራል። መንግስት አሁን ይህንን ተቋም በሚያጠናክርና በሚያግዝ ሁኔታ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀጥታ የሚከታተሉት ራሱን የቻለ ኮሚቴ እንዳቋቋመ ነው የገለጸው። መንግስት "ችግሩን ተረድቼዋለው፤ ህዝብ ተማሯል፤ በአጠቃላይ የመንግስትን አሰራር በማሽመድመድ ህዝብ በመንግስት ላይ እምነት እንዳይኖረው እያደረገ ነው በሚል የተነሳበት አግባብ ጥሩ ነው" የሚል ግምገማ እንዳላቸው ይናገራሉ።

አያይዘውም፣ የኮሚቴው ዝርዝር ኃላፊነት እና አሰራሩን የተመለከቱ መረጃዎች እስካሁን ይፋ ባለመደረጋቸው እንዴት ታች ድረስ ወርዶ ሊሰራ እንደተዘጋጀ የሚያሳይ ነገር የለም። ምናልባት፣ በአገራችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ እንደሚታወቀው አንዳንድ ጊዜ ሙስና ላይ የሚደረግ ዘመቻ የፖለቲካ መሳሪያ የሆነበት አጋጣሚ እንደነበረ ስናስብ አዲስ የተቋቋመው ኮሚቴ ዝርዝር ኃላፊነቱ ብዙም ካለመታወቁ ጋር ተደምሮ የሚነሱ አንዳንድ ጥርጣሬዎች አሉ። መጀመሪያም የፌዴራል ጸረሙስና ኮሚሽን ሲቋቋም፣ ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው። እንደሚታወቀው ሙስና በባህሪው የመንግስት ባለስልጣናት ስልጣናቸውን ተጠቅመው ከሚፈጽሙት ወንጀል ነው። ከመንግስት መዋቅር ውጭ ያሉ ሰዎች በተባባሪነት ሊሳተፉ ይችላሉ። ከዚህ አንጻር ጥርጣሬ መኖሩና የገለልተኛነት ጥያቄ መነሳቱ አግባብ ነው ብለው እንደሚያምኑ ይገልጻሉ።

ነገር ግን፣ በአስፈጻሚው አካል መቋቋሙ ብቻ በቀጥታ ገለልተኛ አይሆንም ለማለት ላያስደፍር ይችላል የሚሉት የህግ ባለሙያው፣ ገለልተኛ ነው ወይም አይደለም የሚያሰኙት በተግባር የሚወስዳቸው እርምጃዎች ናቸው። ስለዚህ በተግባር ገለልተኛነቱን የሚያሳዩ እርምጃዎችን ሲወስድ መታየት መቻል አለበት። ይህ ካልሆነ ግን፣ የፖለቲካ ፍላጎትን ለማሳካት የተወሰደ እርምጃ ተደርጎ ስለሚወሰድ ማህበረሰቡ እምነት ሊያጣበት ይችላል። የተቋቋመው ኮሚቴ በተነገረው መጠን ወደስራ ገብቶ ውጤት ማየት መቻል አለብን። በርግጥ ኮሚቴው እንደተቋቋመ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ በተወሰዱ እርምጃዎች የታሰሩ ሰዎች እንዳሉ አውቀናል። የተነገረውና የተወሰዱ እርምጃዎች መጠን እና አይነት ሲታይ እውነት ለመናገር ብዙ የሚያኩራራ ሆኖ አላገኘውትም። ብዙ ስራ ስለሚጠይቅ ምናልባትም ከዚህ በኋላ በተከታታይ የምንሰማቸው ነገሮች ይኖራሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ይላሉ።

መሰል አደረጃጀቶችን ማቋቋም በሌሎች አገራትም የሚሰራበት መንገድ ነው። ሙስናን በመክሰስና በማስቀጣት ብቻ ሙሉ ለሙሉ መከላከል አይቻልም። ከአስተሳሰብ፣ ከባህልና ከማህበረሰብ እድገት ጋር ይያያዛል። የመንግስትን ንብረት እንደ ራሱ ንብረት አድርጎ የሚቆጥር ማህበረሰብ መፈጠር አለበት። ስለዚህ መጠነ ሰፊና ዘርፈ ብዙ ትግል የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። በአዋጅ የተቋቋመው የጸረ ሙስና ተቋም ዋነኛ ግቡ የህብረተሰቡን ንቃተ ህሊና በማሳደግ ሙስናን የሚጠየፍ ትውልድ ለመፍጠር ተከታታይነት ያለው ስራ መስራት ያሉን አቶ አመሃ፣ በአንድ መልኩ ይሄ ስራ እየተሰራ በተለያየ ምክንያት የሙስና ደረጃው ጠቅላይ ሚኒስትሩ በገለጹት መጠን እጅግ ከፍተኛ ሁኔታ ላይ የሚደርስና የአገርን ኢኮኖሚ በእጅጉ የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ እንዲህ አይነት ጊዜያዊ ኮሚቴ በማቋቋም ጠንካራ እርምጃ መውሰዱ ተገቢ መሆኑንም ይገልጻሉ።

የኮሚቴው የቤት ስራዎች ሊሆኑ የሚችሉትን ጉዳዮች በተመለከተ ግምታቸውን ሲያስቀምጡ፣ ዋነኛ አይነኬ በተባሉት አካባቢዎች ላይ ቆራጥ የሚባሉ እርምጃዎን በመውሰድ የሙስና ወንጀሎችን በመመርመር ተጠርጣሪዎች በህግ እንዲጠየቁ ውሳኔዎችን ማሳለፍና አቅጣጫ ማስቀመጥ ይሆናል ብዬ እጠብቃለሁ። እንዲሁም፣ በአዋጅ የተቋቋመው የጸረሙስና ኮሚሽን ከስራ አስፈጻሚው አካል ተፅእኖ ውጪ ስራውን ያለችግር እንዲሰራ ማስቻል ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ህብረተሰቡንም በጸረሙስና ትግል ላይ በማንቀሳቀስ ረገድም ትልቅ ሚና ይኖረዋል የሚል ግምት አለኝ ብለዋል።

ሙስናን መታገል የመንግስት ብቻ ኃላፊነት አለመሆኑ ሊሰመርበት እንደሚገባ የሚናገሩት አቶ አመሃ፣ አንድ ማህበረሰብ ላይ የሞራል ውድቀት እና የስነምግባር ብልሽት ካለ የተቀረው የሃይማኖትም ሆነ የፍትህ ተቋም ከዚህ ችግር ከገጠመው ማህበረሰብ

**አሁን ጉቦ እየተሰጠ ያለው ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ሳይሆን የተገባውንም መብት ለማስከበር ነው።**

ስለሚመነጭ የተሟሉ ተቋማትን መጠበቅ በጣም አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት የሚመረጠው አካሄድ ሁለትዮሽ መሆን አለበት ብዬ ነው የማምነው። ሙስና አሁን የመጣ ቋንቋ ከመሆኑ ውጭ ስርቆት ማለት ነው። ስርቆት (ሌብነት) ደግሞ፣ በሁሉም እምነቶች የተወገዘና የተኮነነ ነው። ነገር ግን፣ ይኸው ችግር መልሶ በእምነት ተቋማት ውስጥም ጎልቶ የሚታይበት ሁኔታ አለ። የእምነት ተቋማት በአንድ በኩል ቤታቸውን በማጽዳት ራሳቸውን ምሳሌ በማድረግ መስራት አለባቸው። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ህዝብ በአብዛኛው በተለያዩ ቤተእምነቶች ውስጥ የሚሳተፍ ሃይማኖተኛ ነው ማለት ይቻላል። በክርስትናው በኩል በየበአላቱ የሚታየው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ይታወቃል፤ እንደዚሁ በእስልምና በኩልም በሶላት ጊዜ የታየው ህዝብ ይታወቃል። ከፍተኛ ቁጥር ያለው ለመማር ተዘጋጅቶ የመጣን ህዘብ ማግኘት ትልቅ ዕድል ስለሆነ የሃይማኖት ተቋማት ሊጠቀሙበት ይገባል። አትስረቁ የሚል መልዕክት ከማስተላለፍ በዘለለ ቤተ እምነቶች ምሳሌ መሆን አለባቸው በማለት መክረዋል።

ሙስና ሊኖር የሚችለው ሰጪ ሲኖር ነው። ህብረተሰቡ ለምን በሙስና ውስጥ ይሳተፋል ብለን ስንጠይቅ የሚፈልገውን አገልግሎት በሚፈልገው ፍጥነትና ጥራት የማያገኝ በመሆኑ ነው። በዚህ ሁኔታ ማህበረሰቡ ላይ መፍረድ በጣም አስቸጋሪ ነው ነገር ግን፣ አንድ ትውልድ ተጎድቶም ቢሆን፣ ሙስናን የሚጠየፍ ማህበረሰብ መፍጠር መቻል አለብን። ዜጎች በተቻላቸው መጠን አገልግሎትን ከሙስና በጸዳ መንገድ ለማግኘት በየደረጃው የተዘረጉ የአቤቱታ መስመሮችን ተከትሎ በህጋዊ መንገድ ብቻ ለማግኘት ጥረት ማድረግ መቻል አለባቸው። የተቋቋመው ኮሚቴም ህብረተሰቡ አገልግሎት ለማግኘት በተቸገረ ጊዜ ወዲያውኑ አቤቱታ የሚያቀርብበትና መፍትሄ የሚያገኝበት ስርዓት መዘርጋት አለበት። ይሄ በሌለበት ሁኔታ ህብረተሰቡ ላይ የምንጥለው ኃላፊነት በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አንድ ሰው የቀበሌ መታወቂያ ማግኘት በሆነ አጋጣሚ በጣም አንገብጋቢ ጉዳይ ሊሆንበት ይችላል። እንዲህ ባሉ አጋጣሚዎች ያ ሰው በአጭር ጊዜ ውስጥ መታወቂያ ሊያገኝ የሚችልበት መንገድ መዘርጋት አለበት። ምክንያቱም መታወቂያ ህክምና

ከማግኘት፣ ጉዞ ከማድረግ፣ ከባንክ አገልግሎት ጋር ይቆራኛል። ይህን ማድረግ የመንግስት ኃላፊነት ነው። አማራጭ ከሌለ ግን ያሰው መታወቂያውን ለማግኘት ያልተገባ መንገድ ለመሄድ ሊገፋፋና ሊደፋፈር ይችላል። ሲደመር አገልግሎት ሊሰጥ ከተመደበው ኃላፊ ስነ ምግባር ጋር ተያይዞ የሙስና ሂደት ውስጥ የመግባት ነገር ሊኖር ይችላል። ስለዚህ በመንግስት በኩል አገልግሎቶቹ የተፋጠኑ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉም ይመክራሉ።

ብሔራዊ የሙስና ኮሚቴው ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ የወረደ አወቃቀር ሊበጅለት እንደሚገባ በመጠቆም የሙስና ተግባር ህብረተሰቡ ካልተሳተፈበት በአንድ አካል ብቻ የሚፈጸም አይደለም። ህብረተሰቡ ደግሞ፣ በአብዛኛው በሲቪክ ማህበራት የሚወከል ስለሆነ የተቋቋመው ኮሚቴ ማህበራቱ የሚጠበቅባቸውን ትልቅ ሚና እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት። ሁለተኛ ሙስና በሁለት ደረጃዎች የሚፈጸም ነው። ከፍተኛ የገንዘብ መጠን የሚንቀሳቀስበትና በከፍተኛ የመንግስት የኃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ ባለስልጣናት የሚሳተፉበት ሙስና አለ። በሌላ በኩል የህብረተሰቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ገትቶ ያለው በአነስተኛ ደረጃ ነገር ግን እጅግ በብዛት የሚፈጸመው ሙስና አለ። በዚህኛው የሙስና አይነት ላይ የሲቪክ ማህበራት ትልቅ ሚና ሊኖራቸው ስለሚገባ ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል ሲሉም አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ሶሻል ዴምክራቲክ ፓርቲ ምክትል ሰብሳቢ እና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጸሃፊ ዶክተር ራሄል ባፌ በበኩላቸው መንግስት ኢትዮጵያ ውስጥ ለተንሰራፋው የሙስና ችግር እውቅና ሰጥቶ ለመታገል ውሳኔ ላይ ደርሶ ወደ ኮሚቴ ማቋቋም መሄዱ ጥሩ ነገር ነው። ሙስና የአገሪቱ ባህል እስኪመስል ስራ ተደርጎ የተወሰደበት ደረጃ ላይ ነው ያለው። በየደረጃው ያሉ የመንግስት ባለስልጣናትና ኃላፊዎች ከህዝብ በሚሰበሰብ ቀረጥ ደመወዝ እየተከፈላቸው ከስራ ማስኬጃው ባለፈ ተጨማሪ ክፍያ በመጠየቅ ህዝብ መብቱን በድጋሚ ክፍያ እንዲገዛ እያደረጉ ነው። ራሱን የቻለ ዘርፎች የመበልጸጊያ የስራ መስክ ተደርጎ ተወስዶ በአገር ደረጃ ከዳር እስከ ዳር እየተሄደበት ስለሆነ ትልቅ ቁርጠኝነትን እና የህዝብን ምላሽ ጭምር የሚጠይቅ ነው በማለት እርምጃውን በበጎ እንደሚመለከቱት ይገልጻሉ።

ዶክተር ራሄል፣ እንደሚናገሩት የአገልግሎት አሰጣጡ ሙስና የነገሰበት በመሆኑ ስርዓቱን መፈተሽና መሰረታዊ ምንጩን በማግኘት መሰረታዊ ለውጥ ማድረግ እስካልተቻለ ድረስ እንዲሁ በቀላሉ የሚቆም አይደለም። በጣም ስር የሰደደ ችግር በመሆኑ መሰል ኃላፊነቶችን መወጣት የሚችል በአንጻራዊነትም ቢሆን፣ ነጻ የሆነ አካል አለ ወይ ብለን ለመጠየቅ እስክንገደድ ድረስ የደረሰበት ጉዳይ ስለሆነ ትልቅ ቁርጠኝነትን የሚጠይ ነገር ነው። ትግሉ ከአናት ጀምሮ እስከታች ድረስ የሚደርስ ስለሆነ ከራስ ጀምሮ በኃላፊነት ስሜት መንቀሳቀስን ግድ የሚል ነው። የቦታው መጠን የሙስናውን

**"ሙስናን መታገል የመንግስትን፣ የህዝብን፣ የሃይማኖት ተቋማትን እና የሌሎችንም አካላት ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፣ እንደ አገር ትልቅ መፍትሄ ሊፈለግለት የሚገባ ጉዳይ ነው"**

መጠን ይወስናል እንጂ ሙስና ውስጥ የሚሳተፈው አካል ብዙ ነው።

ሙስናን መታገል የመንግስትን፣ የህዝብን፣ የሃይማኖት ተቋማትን እና የሌሎችንም አካላት ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው የሚሉት ፖለቲከኛዋ፣ እንደ አገር ትልቅ መፍትሄ ሊፈለግለት የሚገባ ጉዳይ ነው። አሁን ጉቦ እየተሰጠ ያለው ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ሳይሆን የተገባውንም መብት ለማስከበር ነው። መንግስት አሁን በጀመረው ልክ ቁርጠኛነቱን ካሳየና ሙስና ላይ የተጀመረው ትግል ፕሮፓጋንዳና ንግግር ብቻ ከመሆን አልፎ የእውነት ከሆነ በእርግጠኝነት ህዝብ ይተባበራል። መንግስት አቋሙ እርግጠኛ መሆኑን የሚያመላክቱ ማሳያ እርምጃዎችን መውሰድ ይጠበቅበታል። መንግስት አቋሙን በተግባር ከገለፀ ህዝቡ መኖር የማይችልበት ደረጃ ላይ ስለደረሰ አመኔታ አድሮበት ትብብር እንደሚያደርግ በእርግጠኝነት መናገር እንደሚችሉ ይገልጻሉ።

አያይዘውም፣ የተቋቋመው ኮሚቴ ገለልተኛ አቋም ይዞ ራሱንም ጭምር ቢሆን እያየ ለመሄድ የቆረጠ መሆን አለበት። አሁን ሙስና የድብብቆሽ ጨዋታ መሆኑ ቀርቶ በአደባባይ የሚፈጸም ግልጽ ጉዳይ ሆኗል። ስለዚህ የሚዘለል አካል ካለ፤ ከፍተኛ ኃላፊዎችን እየተወ የበታቾቹን ብቻ የሚያጠቃ ከሆነ፤ በዘር የሚሄድ ከሆነ እና በፖለቲካ ወገንተኝነት የሚሄድ ከሆነ ህዝብ ሁኔታውን ተመልክቶ ከመፍትሄው እንዲሸሽ ያደርገዋል። ስለዚህ ኮሚቴው በስፋት ወደ ስራ እየገባ ሲሄድ እንደ ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን ራሱን በተቻለ መጠን ገለልተኛ አድርጎ ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ከመሪ ጀምሮ ታች እስከሚገኘው ነዋሪ ድረስ በእኩል ደረጃ የህግ የበላይነትን የሚያስከብርበት አካሄድ መከተል አለበት።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የህዝቡና የመንግስት አካል ናቸው። የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ብልጽግና ፓርቲንም አቅፎ ነው ያለው። እውነት ነው ትግሉ ከፓርቲዎች መጀመር አለበት። በገዢው ፓርቲ ውስጥና በሌሎችም የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ያሉት አባላትም ሆኑ መሪዎች ምሳሌ መሆን መቻል አለባቸው። ሙስና እንደ አገር የጎዳን እና ከድህነት ወደ ባሰ ድህነት ያደረሰን ነገር ስለሆነ በጋራ ምክር ቤቱ ትኩረት ሰጥተን የምናየው ነገር ነው። ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ሌብነት ስራ እንደሆነ እና እስካልተያዘ ድረስ ሰው እየሰረቀ ቶሎ የሀብት ማማ ላይ መድረስ እንዳለበት እየመከርን እና በተግባርም ደግሞ ከመሪዎች ጀምሮ እስከበታች ሰራተኛ ድረስ እየፈጸምን ነው የመጣነው። በጉቦ መንገድ ካልመጣ እውቀትን እንኳን ማውረድና ማስረጽ የማንችልበት ደረጃ ደርሰናል። ለኢትዮጵያ እንደ አገር ይሄ በጣም ከባድ ነው። ነገር ግን፣ የግድ አንድ ቦታ ላይ ትግሉ መጀመር ስላለበት ነው አሁን እየተጀመረ ያለው። አንድን ነገር መካብ ነው የሚከብደው ማፍረስ ቀላል ነው ሲሉ የተጀመረው እንቅስቃሴ ወደ ኋላ መመለስ እንደሌለበት አስረግጠው ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሃይማኖተኛ ያልሆነ ዜጋ በጣም ጥቂት ነው። የሃይማኖት ተቋማት በንጽህና ችግሩን ለመቅረፍ ሰርተው ቢሆን ኖሮ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ባልተገኘ እና የመንግስት ስርዓትም እንደዚህ ባልደረሰ ነበር። የሃይማኖት ተቋማት በሙስና ውስጥ የሚኖሩ ናቸው ሲሉ የሚወቅሱት ዶክተር ራሔል፣ በህይወት እና ሞት መሃል ባለ ጉዳይ እንኳን ገንዘብ ማግኘትን እንዲያስቀድሙ አድርገን የትውልድን አእምሮ አበላሽተን ነው የቀረጽነው። የትውልዱን አእምሮ ለመለወጥ በጣም ልንተጋና ቆርጠን ልንነሳ ይገባል። የሃይማኖት መሪዎች ደግሞ በተቻለ መጠን በትክክል ማስተማርና መተግበር ካሳዩና ከዘረኝነት፣ ፖለቲካ እና ሌብነት ከወጡ ዋጋ ቢያስከፍለንምና ሂደትን ቢጠይቅም በእርግጠኝነት እየቀረፍነው እንሄዳለን። ወላጆችም ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስተማር አንደበት የላቸውም። ልጆቻቸው ከደሞዛቸው በላይ እንደሚያኖሯቸው ያውቃሉ። ወላጆችም ለልጆቻቸው አርአያ መሆን ይገባቸዋል። በተጨማሪ፣ በማስረጃ በትክክል የተያዘ ሰው አስተማሪ የሆነ እርምጃ የሚወሰድበት ከሆነ ሌሎችን ያስተምራል ብዬ አምናለሁ። ስለዚህ አስተማሪ እርምጃዎችን በህግ አግባብ መውሰድ ያስፈልጋል ሲሉ ይመክራሉ።

መንግሥት አገርን የሚበላ ነቀዝ እና የአገርን አንጡራ ሀብት እየቦረቦረ ጥሪቷን ባዶ ለማስቀረት ሌት ተቀን የሚማስን ተባይ ሲል በገለፀው ሙስና ላይ በጸጥታው ዘርፍ እንዳደረገው ሁሉ ጠንካራና የማያዳግም ኦፕሬሽን ማድረግ እንዳለበት ጥናቶችንና የሕዝብ ውይይት ግምገማዎችን መሰረት በማድረግ አቋም መያዙን ገልጿል። በአንድ በኩል የመንግሥት ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና አሠራሮች ለሙስና ያላቸውን ተጋላጭነት የማጥፋት ሥራ እየተሰራ በሌላ በኩል ደግሞ የሙስና ተዋንያንን የማጋለጥና በሕግ የመጠየቅ ተግባር እንደሚከውንም አስታውቋል። የዘመን መጽሔት ዝግጅት ክፍልም ዜጎች ሙስናን ለመታገል የሚያደርጉትን ጥረት ከመቼውም ጊዜ በላይ አጠናክረው በመቀጠል ብሔራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴው የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እንዲደግፉ ጥሪውን ያቀርባል።



አቶ ሀሰን መሃመድ
በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና
አስተዳደር የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር



ዶ/ር መሃሪ ረዳኢ
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህግ ፋካሊቲ መምህርና
ተባባሪ ፕሮፌሰር



አቶ ጌታቸው ክፍሉ
የኢትዮጵያ አረጋውያንና ጡረተኞች ማህበር
ብሔራዊ ቦርድ ም/ሰብሳቢ

# ለጡረተኛው የቆመው የአዋጅ ማሻሻያ

**ንጉሴ ተስፋዬ**

አንዳንድ የፌዴራል መ/ቤቶች ሲቋቋሙ የማስፈጸም ስልጣን ብቻ ይዘው ይቋቋማሉ። ሌሎቹ ደግሞ የልማት ድርጅት ሆነው ሊደራጁ ይችላሉ። የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፣ እንደሌሎች ተቋማት ሁሉ የማስፈጸም ስልጣን በህግ ተሰጥቶታል። በተሰጠው ስልጣን መሠረትም ተቋማት ምን ያህል ሠራተኛ እንደቀጠሩ፣ የጡረታ መዋጮ መክፈልና አለመክፈላቸውን ያጣራል፣ ምን ያህል ገንዘብ እንደከፈሉም ኦዲት ያደርጋል። በኦዲት ግኝቱ መሰረትም ያልገባ የጡረታ መዋጮ ካለ እንዲገባ ያደርጋል፤ የጡረታ መዋጮ ገንዘብን በየወሩ ይከታተላል፣ ምርመራ ያደርጋል፣የገንዘብ መዋጮውንም በአግባቡ ሰብስቦ ያስተዳድራል። የጡረታ መዋጯቸውን በጊዜና በመግባባት ማስገባት ያልቻሉትን፣ በትዕዛዝ ከባንክ አካውንታቸው እንዲቀነስ በማድረግ፣ አልያም ንብረታቸውን እስከማሸጥ በሚያደርስ ቅጣት እንዲከፍሉ ያስገድዳል። በዚህም ለጡረተኞች በየወሩ የጡረታ አበላቸውን ይከፍላል፤ ጡረታ ለሚወጡት ደግሞ የአበል ውሳኔ ይሰጣል።

ተቋሙ፣ የአበል ውሳኔ ሲሰጥ የሚሰራው የዳኝነት ስራ ነው። የዳኝነት ተግባሩም የጡረታ ገንዘቡን ከመመዝገብ ጀምሮ መርምሮ ውሳኔ እስከመስጠት ይደርሳል። ለዚህም ነው "ተቋሙ በከፊል የዳኝነት ስልጣን አለው" የሚባለው። በአስተዳደሩ ውሳኔ አሰጣጥ ቅር የተሰኘን አካል አስተዳደሩ መልሶ ውሳኔውን እንዲያየው አሰራሩ ይፈቅድለታል። አሁንም በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ የሚያቀርብና ይግባኝ የሚል ተገልጋይ ካለ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ አባላት ባሉት ለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ቅሬታውን በቀጥታ ያቀርባል። ከዚያ በኋላ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት ካለበት ጉዳዩ ወደ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይሄዳል።

አሁን ላይ ደግሞ ተቋሙ ስራ አላሰራ ያሉ የአዋጅ አንቀጾችን በማሻሻል እና ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ማከናወን በሚያስችለው የለውጥ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። እንደ አቶ ሀሰን መሃመድ፣ በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ገለጻ፣ የተቋሙ ለውጥ ከተቋሙ ስያሜ ይጀምራል። የፌደራል ተቋማትን ለማደራጀት በወጣው 1263/2014 አዋጅ፣ የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይባል የነበረው፣ በኋላ በተሻሻለው፣ በአዋጅ ቁጥር 1267/2014 "አስተዳደር" የሚለው ስያሜ ጸንቶለታል። ቀደም ሲል ለሲቪል ሠርቪስ የነበረው የተቋሙ ተጠሪነትም በማሻሻያው የፋይናንስ ተቋማትን ለሚቆጣጠረው ለብሔራዊ ባንክ ሆኗል።

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፣ አንቀጽ 14፣ ንዑስ አንቀጽ ሁለት "ለ" ላይ ለጡረተኞች የሚሰበሰበውን ገንዘብ በቦርድ እያስጸደቀ አስተማማኝ በሆነ ኢንቨስትመንት ስራ ላይ እንዲያውለው ተፈቅዶለታል። በዚህም ከኢንቨስትመንት ተግባር ጋር በተያያዘ ተቋሙ በከፊል የገንዘብ ተቋም ሆነ ማለት ነው። በመሆኑም የሚሰበስበውን ገንዘብ ለጡረተኞች ከፍሎ፣ መጠባበቂያ ካስቀመጠ በኋላ የተረፈው ገንዘብ ዋጋ እንዳያጣ፣ የመግዛት አቅሙን ጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ በተመረጡ እና አዋጪ በሆኑ የኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ያውለዋል።

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በንጉሱ ዘመን የነበረ ተቋም እንደሆነና ለውጡ የሚጀምረውም ከዚያ ጊዜ ወዲህ ነው ያሉት ደግሞ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ህግ ፋካሊቲ መምህርና ተባባሪ ፕሮፌሰር ዶ/ር መሃሪ ረዳኢ ናቸው። እንደ ዶ/ር መሃሪ ማብራሪያ፣ በንጉሱ ዘመን የጡረታ መውጫ ዕድሜ ለወንድ 60፣ ለሴት ደግሞ 50 ነበር። ይህም ሴቶች ቀደም ብለው ከስራ ቢገለሉ ይሻላል በሚል ዕምነት የተተገበረና የጾታ ዕኩልነትን የሚያንጸባርቅ አልነበረም። የደርግ መንግስት ሲመጣ የሁለቱንም ጾታዎች የጡረታ መውጫ ዕድሜ 55 ዓመት ያደረገ ሲሆን፣ በኢህአዴግ ሥርዓት ደግሞ 55 ዓመት የነበረውን የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከጊዜ በኋላ የሁለቱንም ጾታ ዕድሜ ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ወደ 60 ዓመት ከፍ አድርጎታል።

ከአዋጅ ለውጡ ጋር በተያያዘ መነሳት የሚገበው ጉዳይ የግል ዘርፉም የጡረታ ሥርዓት የተበጀለት መሆኑ ነው። ድሮ የጡረታ መብት የነበረው የመንግስት ሠራተኛና የመንግስት የልማት ሠራተኛ ብቻ ነበር። ከቅርብ አመታት ወዲህ፣ የግል ዘርፉም ወደ ጡረታ ዕቅድ ውስጥ መግባት ችሏል። ቀደም ሲል ሠራተኛው የተሻለ የስራ ዕድል ቢያገኝም የጡረታ አገልግሎቴ ይቀርብኛል በሚል ስጋት ከመንግስት መ/ቤት ሳይወጣ እዚያው የመቀጠል አዝማሚያ ይታይበት ነበር። ሰራተኛው ከግል ዘርፉ ወደ መንግስት መ/ቤት እንዳይሄድም የተለያዩ ጥቅማጥቅሞች ይቀሩብኛል በሚል ፍርሃት የዝውውር እንቅስቃሴው ተገድቦ ቆይቷል። አሁን ግን አንድ ሠራተኛ ከየትኛውም መ/ቤት ያጠራቀመውን ገንዘብ፣ ያገለገልከበትን ዕድሜ እና የጡረታ መለያ ቁጥሩን ይዞ ወደ የትኛውም ተቋም መሄድ የሚችልበት አሰራር ተፈጥሯል። የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት፣ ሁለቱም አደረጃጀቶች ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ባንክ ስለሆነም ሰራተኛው ከስራ ጋር በተያያዘ ወደ የትኛውም ተቋም እንዳይንቀሳቀስ የሚገድበው አሰራር አለመኖሩ በለውጡ ሂደት የተገኘ አንዱ በበጎ ጎኑ የሚታይ ጉዳይ ነው።

በቅርቡ የወጡት የ2003 ዓ.ም እና የ2014 ዓ.ም አዋጆችም ቢሆኑ አጠቃላይ መርሃቸው ተመሳሳይ እንደሆነ የሚናገሩት ዶ/ር መሃሪ፣ በሁለቱም አዋጆች 60 ዓመት ዕድሜ የመጦሪያ ጊዜ ሲሆን፣ ከ60ዓመት በታች በጤናም ሆነ በአካል ጉዳት ምክንያት የመጦር ዕድል እንዳለ በሁለቱም አዋጆች መቀመጡን፣ ለጡረታ ብቁ ለመሆን ደግሞ ዝቅተኛው መነሻ የአገልግሎት ዘመን 10 ዓመት መሆኑን ይገልጻሉ።

በአዋጅ ማሻሻያው ከተዳሰሱ አንኳር ጉዳዮች መካከል አንዱ የጡረታ መዋጮ የተሰበሰበው

ገንዘብ ለተጠቃሚው እስኪከፈል ድረስ ምን ላይ መዋል አለበት የሚለው ነው። ቀደም ብሎ በነበረው አሰራር የሚሰበሰበው መዋጮ ገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለቦንዶችና ሌሎች አትራፊ የንግድ ዘርፎች ኢንቨስት እንዲደረግ ያዝ ነበር። ገንዘብ ሚኒስቴር ደግሞ ሌሎች ትልልቅ ተግባራትን የሚያከናውን ተቋም ስለሆነ መመሪያውን ሳያወጣ በመቅረቱ ገንዘቡ በባንክ ተቀምጦ ከዚህ ግባ የማይባል ወለድ ብቻ እየተሰበሰበበት፣ አትራፊ በሆነ ተግባር ላይ እንዳይውል ገድቦት ቆይቷል።

አሁን ግን፣ ይህን ችግር ለመቅረፍ ሲባል የማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ቦርድ የሚባል ተቋቁሟል። ቦርዱ፣ ገንዘቡ ምን ምን የኢንቨስትመንት ዓይነቶች ላይ ቢውል የተሻለ ውጤታማ ይሆናል ብሎ ወስኖ ኢንቨስት እንዲያደረግ ያዛል። በተለይም፣ ቦርዱ ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ባንክ መሆኑ፣ ልክ እንደ ባንኮችና ኢንሹራንሶች ሁሉ የተሻለ የኢንቨስትመንት አትራፊነት አቅጣጫን የማመላከት ዕድሉን ያሰፋለታል።

በተገኘው መረጃ መሰረት ከተቋሙ እና ከአዋጅ ማሻሻያው ጋር በተያያዘ፣ ወደ ዝርዝር ጉዳይ ሲገባ በለውጡ ከተዳሰሱት መካከል አንዱ የጡረታ "መለያ ቁጥር" ነው። የጡረታ መለያ ቁጥር ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረው በተቋሙ ወይም በግብር ሰብሳቢው አካል ነበር። በመሆኑም የጡረታ መለያ ቁጥር ድግግሞሽ እንዳይኖር፣ አንድ ሰው ሁለት ቁጥር እንዳይኖረው፣ ሁለት ሰዎች ደግሞ አንድ ዓይነት ቁጥር እንዳይኖራቸው እና ቁጥሮቹን ወጥ ለማድረግ ሲባል ብሔራዊ መለያ ቁጥር የሚሰጥ ተቋም እንዲቋቋም ተደርጓል።

የወታደር /የፖሊስ፣ የመከላከያ ሠራዊት፣ የመሳሰሉት/ መዋጮን በተመለከተ አሰሪው ይከፍለው የነበረው መዋጮም ከ25 ከመቶ ወደ 33 ከመቶ አድጓል። ምክንያቱ ደግሞ በእነዚህ ተቋማት የሚሰሩ ሰራተኞች የጡረታ መውጫ ዕድሜ እንደ ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች 60 ዓመት ሳይሆን፣ የጡረታ መውጫቸው በመቋቋሚያ ደንባቸው፣ ወይም ህጋቸው መሰረት ነው ስለሚል፣ በተለያየ ጊዜ በ55፣ በ45፣ ወዘተ ዕድሜያቸው ጡረታ እንዲወጡ ስለሚፈቅድላቸው ነው። የወታደር ስራ እንደሚታወቀው አደገኛ /Risk area/ ነው። በመሆኑም፣ በእነዚህ ምክንያቶች የሠራተኛውን መዋጮ መጨመር ሳያስፈልግ፣ የአሰሪው መዋጮ ብቻ እንዲጨምር ሆኗል።

በ714/2003 አዋጅ ተቋማት የአሰሪውንም ሆነ የሰራተኛውን መዋጮ በወቅቱ ሰብስበው ወደ ባንክ እንዲያስገቡ ደንግጓል። ይሁን እንጂ፣ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት እኛ ባንክ አይደለንም በሚል ምክንያት ለአዋጁ ተገዥ ባለመሆን ለአሰራር ችግር ፈጥረው ቆይተዋል። በማሻሻያ አዋጁ ላይ ግን፣ ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም ጉዳዩ እንደሚመለከተው ተደንግጓል። በመሆኑም አንዳንድ በመንግስት በጀት የማይተዳደሩ ገንዘቦችን በማይክሮ ተቋማት በማስቀመጥ

**የአዋጅ ማሻሻያው ዋና ዓላማ ተቋሙ የነበረበትን የአሰራር ክፍተት መቀየር እና ማስተካከል ሲሆን፣ ይህ ተቋሙ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ደረጃ ከሌሎች የመንግስት ተቋማት የተሻለ የፋይናንስ ተቋም ተደርጎ ይቆጠራል።**

የጡረታ ፈንዱ በአግባቡ ስራ ላይ እንዳይውል ያደርጉ የነበሩ ተቋማትንም የህግ ማዕቀፉ በአግባቡ ዳስሷቸዋል።

ባንኮች የሰበሰቡትን ገንዘብ ገቢ ሳያደርጉ ሲቀሩ የሚቀጡበት የህግ አግባብም በአዋጁ ላይ በግልጽ አልተቀመጠም ነበር። አሁን ግን ገንዘቡን በተቋሙ እንዲያስገቡ ታዘው ሳያስገቡ ገንዘብ ካወጡ ባወጡት ገንዘብ ልክ ተጠያቂ ይሆናሉ። የሚፈለገው ገንዘብ ባንክ ላይ የማይገኝ ከሆነም ተቋሙ ንብረት እስከማሸጥ የሚደርስ ስልጣን ተሰጥቶታል። ይህም፣ በገንዘብ ሚኒስቴር መመሪያ "ንብረት ይሸጣል" የሚለውን ለአሰራር ችግር ይፈጥር የነበረውን የበፊቱን አዋጅ በመሻር ተቋሙ ራሱ በሚያወጣው መመሪያ እንዲፈጸም ማድረጉ ሌላው የለውጡ አካል ነው።

የአዋጅ ማሻሻያው ዋና ዓላማ ተቋሙ የነበረበትን የአሰራር ክፍተት መቀየር እና ማስተካከል መሆኑን አቶ ሀሰን ያብራራሉ። እንደእሳቸው አገላለጽ፣ ይህ ተቋም በአፍሪካም ሆነ በዓለም ደረጃ ከሌሎች የመንግስት ተቋማት የተሻለ የፋይናንስ ተቋም ተደርጎ ይቆጠራል። ነገር ግን እስከዛሬ ድረስ በተግባር ሲታይ ተቋሙ ከአስፈጻሚነት ስራው በዘለለ ጠንካራ የፋይናንስ ተቋም መሆን አልቻለም ነበር፣ አሁን ላይ ግን፣ ቀድሞም ከነበሩት ኃላፊነቶቹ ላይ የገቢ ማስገኛ የሆነው የኢንቨስትመንት ስልጣን ተፈጥሮለታል።

የተቋሙ የለውጥ ዓላማ የጡረተኛውን ማህበረሰብ ለመጥቀምና ኑሮውን ለማሻሻል ነው። ተቋሙ በየጊዜው አሰራሩንና አደረጃጀቱን የሚያሻሽለውም ጡረተኛውን ማህበረሰብ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ስለሆነም፣ ተቋሙ የተቋቋመውም አረጋውያንንና የጡረተኛ ማህበረሰቡን ለማገልገል በመሆኑ ማሻሻያው ይህን ዓላማውን ለማሳካት የሚያደርገው እንቅስቃሴ አንዱ አካል ነው የሚሉት የኢትዮጵያ አረጋውያንና ጡረተኞች ማህበር ብሔራዊ ቦርድ ም/ሰብሳቢ አቶ ጌታቸው ክፍሉ ናቸው።

አቶ ሀሰን ደግሞ፣ የመንግስትን የትኩረት አቅጣጫና የለውጡን ጠቀሜታ አስመልክቶ እንደ ሀገር ሲታይ በዋናነት ከድህነት ወለል በታች የሚገኘውን የጡረተኛ ህይወት ማሻሻልና በኢንቨስትመንት ደግሞ ጠንካራ የገንዘብ ተቋም በመሆን አገሪቱን በኢኮኖሚ መደገፍ መሆኑን በማንሳት የአቶ ጌታቸውን ሃሳብ ያጠናክራሉ።

በቆዩት አዋጆች በተለይም በአዋጅ ቁጥር 714/2003 ተቋሙ ኢንቨስት እንዲያደርግ የተፈቀደለት የትሬዠሪ ቦንድ በመግዛትና የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ እንዲያደርግ የሚል ነበር። ይሁን እንጂ አዋጁ ከወጣ ከ10 ዓመት በላይ ቢሆነውም፣ገንዘብ ሚኒስቴር መመሪያ ባለማውጣቱ ምክንያት የኢንቨስትመንት ስራውን ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም። በዚህም ምክንያት የቆየውን አዋጅ፣ እንደገና እንዲሻሻል በማድረግ የኢንቨስትመንት ስራን ለመጀመር ተቋሙ በሂደት ላይ ይገኛል።

ተቋሙ የኢንቨስትመንት ስራን እንዲያከናውን ለምን ተፈቀደለት? ለሚለው ጥያቄ በዋናነት የጡረተኞችን ጥቅም ለማስከበር መሆኑን አቶ ሀሰን ያስረዳሉ። አያይዘውም፣ በፊት የነበረው አዋጅ በአምስት ዓመት ውስጥ ለጡረተኞች የአበል ጭማሪ ይደረጋል የሚል ቢሆንም፣ በተግባር ግን ጭማሪው በየሁለት ዓመቱ እየተከናወነ መሆኑን ያብራራሉ። ምክንያቱን ሲገልጹም፣ የጡረተኞች የገቢ መጠናቸው ከጊዜው ሁኔታ ጋር አብሮ የሚሄድ ባለመሆኑ እና የወቅቱን የኑሮ ሁኔታና የገንዘቡን የመግዛት አቅም በማገናዘብ ነው ብለዋል፤ የጡረተኞችን ኑሮ ለማሻሻል፣ የመክፈል አቅምን በኢንቨስትመንት ማጠናከር እንደሚያሻም ያሰምሩበታል።

ቀደም ሲል የነበረው የአበል ማስተካከያ ሊደረግ የሚችለው በየ 5 ዓመቱ ሆኖ በሚኒስትሮች ም/ቤት ሲወሰን ነበር። በአሁኑ አዋጅ ግን፣ የአበል ክለሳው ወደ ሚኒስትሮች ም/ቤት መቅረብ ሳያስፈልገው በየ 3 ዓመቱ በቦርዱ እንዲወሰን ሆኗል። ለውጡ ገና በሂደት ላይ ስለሆነ ወደፊት የሚታይ ቢሆንም፣ በወረቀት ባለው ደረጃ ሲመዘን የተሻለ የአሰራር ነጻነትና የውሳኔ ተለዋዋጭነት እንዲኖር ዕድል የሚፈጥር ስለሆነ ተስፋ የሚታይበት መሆኑን ዶ/ር መሃሪም ያስረዳሉ።

ተቋሙ ለጡረተኛው አበል መደጎሚያ ሊሆን የሚችል የኢንቨስትመንት ተግባር ማካሄድ እንዲችል መፈቀዱ ትክክል መሆኑን በተመለከተ

አቶ ጌታቸው ሲገልጹ፣ ተቋሙ እሪ በከንቱ ላይ ዘጠኝ ወለል ያለው ፎቅ ለጽ/ቤት መገንባቱን ያስረዳሉ። ነገር ግን፣ ተቋሙ ለሰራተኛው ምቾት ሳይሳሳ ለአረጋውያንና ለጡረተኞች በማሰብ ለገቢ ማስገኛ ለማዋል መወሰናቸው በራሱ ለኢንቨስትመንት ስራ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያመላክታል ብለዋል። በተለይም፣ ሌላው ተቋም ለራሱ ቢሮ ምቹ መሆን በሚጨነቅበት ወቅት፣ እነሱ ግን ለጡረተኛው ማህበረሰብ ማሰብ መቻላቸው የሚደነቅ ተግባር መሆኑን ያብራራሉ። ተቋሙንም በቅርበት እንደሚያውቁት በማንሳት፣ በአዲሱ አደረጃጀት የኢንቨስትመንት ተግባሩን በአግባቡ በመወጣት ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው እንደሚችል እንደ ማህበር ከፍተኛ እምነት አላቸው። በመሆኑም ሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችም ይህንን አርአያነት ያለው ተግባር ቢከተሉ ያለ ጥርጥር ለችግር ተጋላጭ የሆነ የህብረተሰብ ክፍል ኢትዮጵያ ውስጥ ሊጠፋ እንደሚችል ያምናሉ።

ዶ/ር መሃሪም፣ ተቋሙ በነበረው አሰራር እንደ አንድ ዋና ችግር ይቆጠር የነበረው ለጡረተኛ ማህበረሰብ የሚሰበሰበው ገንዘብ ኢንቨስትመንት ላይ ውሎ ለሀገር ጠቅሞ ለጡረተኛውም ከኑሮ ውድነት እና ከገንዘብ የመግዛት አቅም ጋር የተገናዘበ የጡረታ አበል እንዲከለስ አለማስቻሉ መሆኑን ያነሳሉ። እንደ ዶ/ሩ ማብራሪያ፣ አሁን ላይ ተቋሙ ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ባንክ መሆኑ፣ ኢንቨስትመንቱ በገንዘብ ሚኒስቴር ከሚወሰን ይልቅ ራሱን በቻለ የአስተዳደር ቦርድ እንዲወሰን ስለሚያደርገው የተሻለ ገቢና ትርፍ ወዳለበት ዘርፍ መዋጮውን የማዋል ዕድልን ይፈጥርለታል። በኢንቨስትመንት የተሻለ ትርፍ ከተገኘ ደግሞ የመንግስት ካዝና ሳይጠበቅ የጡረታ አበሉ በየጊዜው እየተከለሰ ጡረተኛው ተጠቃሚ የመሆን ዕድሉን ያሰፋለታል።

ለጡረተኛው ማህበረሰብ በመዋጮ የሚሰበሰበው ገንዘብ ቀላል የሚባል አይደለም። በመሆኑም ባንክ ላይ ቢቀመጥ በዓመት ወለዱ 7 በመቶ ብር ብቻ ነው። አንዳንድ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ግን 30 እና 35 በመቶ ገቢ የማስገኘት ዕድል አላቸው። ስለዚህ ገንዘቡ ወደ እነዚህ ዓይነት የኢንቨስትመንት ዘርፎች እንዲውል መደረጉ፣ በንግድ ዘርፉ አገርን ጠቅሞ መንግስትን ሳያስቸግሩ የጡረታ ማስተካከያ ለማድረግ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል። በዚህ የኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚገኘው ገቢም የትርፍ ግብር የማይቀነስበት ስለሆነ፣ ወደ 35 በመቶ የሚደርስ ግብር የማይከፈልበት የገንዘብ ደጎማ ማግኘት መቻል በቀላሉ የሚታይ ለውጥ አለመሆኑን ዶ/ር መሃሪ ያሰምሩበታል።

ቀጣዩ የተቋሙ ተግባር ሊሆን የሚችለው፣ በነበረው የሲቪል ሰርቪስ ህግ ኢንቨስትመንቱን ማስተዳደር ስለማይቻል የሰው ሃብት አስተዳደሩን መቀየር መሆኑን አቶ ሀሰን ያብራራሉ። በመሆኑም፣ ተቋሙ ከአደረጃጀቱ ባህርይ አኳያ በከፊል የፋይናንስ፣ በከፊል ደግሞ የመቆጣጠር ስራውን

**አሁን ላይ ግን፣ በአካባቢው ሊገኝ በሚችል በንግድ፣ በአቢሲኒያ፣ በኦሮሚያ እና በመሳሰሉ ባንኮች አማካኝነት የጡረታ አበላቸውን በመክፈል ከፍተኛ የሆነ ልፋትና ድካማቸውን፣ እንዲሁም የትራንስፖርት ወጪያቸውን መቀነስ መቻላቸው ትልቅ የአሰራራቸው ለውጥ ማሳያ ነው ።**

ማከናወን እንዲችል የተለየ ደንብ አዘጋጅቶ የኢንቨስትመንት ባለሙያዎችን መቅጠር የግድ ይለዋል። የሚቀጠሩት ባለሙያዎችም፣ ያለውን ካፒታል መነሻ በማድረግ አዋጭ የኢንቨስትመንት ዘርፍ አጥንተው ለውሳኔ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ መንገድ የተቋሙ ገንዘብ የመክፈል አቅሙ ሲጠናከር ለጡረተኞች የሚደረገው የአበል ጭማሪ የወቅቱን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የመጨመሪያ ጊዜውን ያሳጥረዋል። የሚጨመረው የገንዘብ መጠንም የተሻለ ይሆናል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለጡረተኞች ገንዘቡ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ እንዲሰጣቸው በማድረግ የኑሮውን ጫና እንዲቋቋሙ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል።

በቅርብ ጊዜም መንግስት የጡረታ ማስተካከያ አድርጓል። 1,258 ብር የነበረው ዝቅተኛው የጡረተኛ መነሻ ብር 2,218 ሆኗል። በዚህም ለዝቅተኛው ተከፋይ ወደ 1,000 የሚጠጋ ብር ተጨምሯል። ጭማሪው ከትልቁ ወደ ትንሹ በመሆኑ በመቶኛ ሲሰላ ከ76 ከመቶ በላይ ነው። ለዚህም ነው የኢንቨስትመንት ዋናው ጠቀሜታ የተቋሙን ገንዘብ የመክፈል አቅም በማሳደግ፣ በዚያው ልክ የጡረተኞችን ህይወት መቀየር ነው የተባለው።

የጡረታ አበል ማስተካከያውን በተመለከተ አቶ ጌታቸው ሲገልጹ፣ እንደ ማህበር ጥር 2014 ዓ.ም ጡረተኞች የኑሮውን ውድነት መቋቋም ስላልቻሉ ችግሩን እንዲቋቋሙ የጡረታ አበል ማስተካከያ ይደረግ በሚል ከተቋሙ ጋር ብዙ ውይይት አካሂደዋል። ውይይቱ ውጤት አምጥቶ ከመስከረም ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ የአበል ማስተካከያ ተደርጓል። ይህ ጭማሪ ደግሞ በየትኛውም ስርዓት ታይቶ አይታወቅም። ቀደም ሲል የ46 እና የ69 በመቶ ጭማሪ ቢደረግም፣ ይህ የአበል ማስተካከያ ግን ስር ነቀል ለውጥ ሊባል የሚችል ነው። ስለሆነም እንደ ማህበር የሚያስቡት በተቋሙ ከፍተኛ ለውጥ እየተካሄደ እንደሆነ ነው። አስተዳደሩ ደግሞ ከሃላፊዎቹ እስከ ሰራተኛው ለሚያቀርቡት ጥያቄ ሁሉ አወንታዊ የሆነ አመለካከት እንዳላቸውና ሃሳባቸውንም በቀናነት ስለሚመለከቱላቸው ሊመሰገኑ ይገባል ብለዋል።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ 60 እና ከዚህ በላይ የሆኑ 6.8 ሚሊዮን አረጋውያን አሉ። ጡረተኛው ግን 7,000 ሺህ ብቻ ነው። ማህበራቸው በየጊዜው የወቅቱን የኑሮ ውድነት መቋቋም ላቃተው ጡረተኛ ማህበረሰብ የአበል ጭማሪና ማስተካከያ እንዲደረግ ጥያቄ ማቅረባቸውን ይናገራሉ። መንግስት ደግሞ በፖለቲካ ሽኩቻ ከግራና ቀኝ በተወጠረበትና አገር ችግር ውስጥ በገባችበት፣ ከዚህም ከዚያም ተፈናቃይ በበዛበት፣ የመልሶ ማቋቋሙ ስራው ብዙ ወጪ በሚጠይቅበት፣ ለህዳሴ ግድብ ብዙ ብር በሚያስፈልግበት እና የተለያዩ ትልልቅ የልማት ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ተግባራዊ በሚደረጉበት ወቅት ማስተካከያው ተግባራዊ መደረጉ መንግስት ለጡረተኛው ማህበረሰብ ችግር ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱን አመላካች መሆኑን ያብራራሉ።

የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ ዘመናዊ በማድረግ ጡረተኞች እንዳይጉላሉ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኝም አቶ ሀሰን ይገልጻሉ። አሁን ባለው አሰራር አንድ ሰው ጡረታ ሲወጣ መረጃውን አሟልቶ ከተገኘ ውሳኔ ለመስጠት ከአንድ ሰዓት በላይ አይፈጅም። ወደ ፊትም ቢሆን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የበለጠ አሰራሩን ለማፋጠን እየተሰራ ነው።

ይህን ሃሳብ አቶ ጌታቸው ሲያጠናክሩት፣ ቀደም ሲል ጡረተኛው አበሉ ይከፈለው የነበረው በየቦታው ነበር። በፖስታ ቤት፣ ሌላ ጊዜ ጡረተኞች በሚሰበሰቡበት አካባቢ በሚል በጣም ከፍተኛ እንግልት ነበረው። በዚህም ጡረተኞች ለጸሀይና ዝናብ ይጋለጡ ፣ ከድካምና ልፋታቸው በተጨማሪም ለከፍተኛ የትራንስፖርት ወጪ ይዳረጉ ነበር። አሁን ላይ ግን፣ በአካባቢው ሊገኝ በሚችል በንግድ፣ በአቢሲኒያ፣ በኦሮሚያ እና በመሳሰሉ ባንኮች አማካኝነት የጡረታ አበላቸውን በመክፈል ከፍተኛ የሆነ ልፋትና ድካማቸውን፣ እንዲሁም የትራንስፖርት ወጪያቸውን መቀነስ መቻላቸው ትልቅ የአሰራራቸው ለውጥ ማሳያ ነው ይላሉ።

ከእጅ ወደ አፍ የሆነው የጡረተኛው ማህበረሰብ ኑሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጫናው እየበዛበት እንደሚሄድ ይታወቃል። መንግስት ደግሞ ይህን ችግር ለማቃለል የተለያዩ ርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል። በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተቋም ላይ የተካሄደው የአደረጃጀትና አሰራር ማሻሻያም የርምጃው አንዱ አካል ነው። በመሆኑም ለውጡን ዕውን አድርጎ የጡረተኞችን ህይወት ለመቀየር ለሚደረገው ትግል ሁሉም የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል እንላለን።

# የሕትመቶቹ ጥሪ

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

ዘመናዊ የሕትመት መሣሪያ የኢትዮጵያን መሬት የረገጠው የዛሬ 500 ዓመት እ.ኤ.አ በ1556 ዓ.ም እንደነበር፣ አዲስ አየለ፣ "የኢትዮጵያ ሚዲያ ታሪክ ከጥንት እስከዛሬ" በሚል በ2010 ዓ.ም ባሳተመው መጽሐፉ አስፍሯል። ጀርመናዊው ጆን ጉተንበርግ እ.ኤ.አ በ1439 የሕትመት ማሽንን ከፈለሰፈ በኋላ፣ መረጃን በጽሑፍ ለመቀባበል፣ ታሪክንም ለመከተብ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። የሕትመት ማሽን ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በእንጨት፣ በድንጋይና መሰል ቁሶች ላይ ስዕሎችንና ምልክቶችን በመጠቀም መረጃን የማስቀረት ልማድ ለዘመናት ሲሠራበትም ቆይቷል።

ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ያስቆጠረው የሕትመት ቴክኖሎጂ የሬዲዮና ቴሌቪዥን የ480 ዓመት ዕድሜ ታላቅ ነው። ባለንበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ ቴክኖሎጂው እጅግ ዘመናዊ የሚባል ደረጃ ላይ ደርሷል፤ ጥቁርና ነጭ ቀለማትን ብቻ ያትም የነበረው የሕትመት ቴክኖሎጂ ዛሬ ሁሉንም ቀለሞች በሚያትሙ ማሽኖች ተተክቷል። ጥቂት የሕትመት ቅጂዎችን ለማተም ብዙ ጊዜን ይጠይቅ የነበረበት ጊዜም አልፎ በጥቂት ሰዓታት በርካታ ቅጂዎችን ማተም ተችሏል።

ቴክኖሎጂው የደረሰበት ደረጃ በእጅጉ የላቀ ቢሆንም፣ በሀገራችን፣ ለሕትመት ሥራ መሠረታዊ የሆነውን "ወረቀት" ማግኘት ግን ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል ሆኗል። የኢትዮጵያ አሳታሚዎችና አታሚዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት፣ አቶ ተፈራ ስዩም፣ የወረቀት በሀገር ውስጥ በበቂ መጠንና ጥራት አለመመረትና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ወረቀት ላይ የሚጣለው ተደራራቢ ታክስ፣ ከውጭ ምንዛሪ ጭማሪ ጋር ተዳምሮ፣ የሕትመት ዋጋን እያናረ፣ አታሚና አሳታሚዎችንም ከኢንዱስትሪው እያራቀ እንደሚገኝ ይናገራሉ። ከጥቂት ዓመታት በፊት 400 እና 500 ብር ይሸጥ የነበረው አንድ እሽግ ወረቀት ዛሬ እስከ 6ሺ ብር እየተሸጠ ይገኛል፤ ይህም የሕትመት ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር አድርጓል። በዚህ ሳቢያም፣ ብዙ አሳታሚዎች መጽሐፍ ከማሳተም ተቆጥበዋል። ችግሩን ተቋቁመውና ደፍረው የሚያሳትሙትም በጥቂት ቅጂዎች ብቻ እንዲወሰኑ አስገድዷቸዋል። ቀደም ባሉ ጊዜያት 10ሺ እና 5ሺ ቅጂ ያዙ የነበሩ አሳታሚዎች 1ሺ እና 500 ቅጂ ማዘዝም ጀምረዋል። ይህ የቅጂ ብዛት ደግሞ፣ አይደለም ከኢትዮጵያ ህዝብ፣ ከአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ብዛት አንጻር እንኳ ሲታይ፣ በጣም የወረደና አንድ መጽሐፍ አሳትሞ ለጓደኛና ለሰፈር ሰው የማከፋፈል ያህል ነው በማለት ሕትመት የደረሰበትን አስጊ ደረጃ ያስረዳሉ።

ከ15 ዓመታት በላይ በሕትመት ኢንዱስትሪ የቆየው የጃጃው ማተሚያ ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ ነብዩ በለጠም፣ የወረቀት ዋጋ ጭማሪው የምንቋቋመው አይነት አይደለም ይላሉ። 400 ብር




ይሸጥ የነበረው ለየትኛውም መጽሐፍ ሕትመት የሚያገለግለው ባለ 60 እና 70 ግራም አንድ እሽግ ወረቀት፣ ዛሬ እስከ ሰባት ሺ ብር፣ 135 ብር ይሸጥ የነበረው የባንክ ወረቀት ደግሞ 4ሺ ብር መድረሱንም ይናገራሉ።

"ጸሐፊዎች መጽሐፍ የማሳተም ፍላጎት ቢኖራቸውም፣ የዋጋ ጭማሪው ሞራላቸውን ገድሎታል፣ ብዙ አታሚዎችም ማሽኖቻቸውን እየሸጡ ከኢንዱስትሪው ለመውጣት እየተገደዱ ነው፤ በ90 እና 70 ብር ይሸጥ የነበረ አንድ ትንሽ መጽሐፍ ዛሬ 400 እና 500 ብር ገብቷል፤ ቀድሞ በነበረው ዋጋ የኅብረተሰብ የንባብ ባህል ባልዳበረበት ሁኔታ ዛሬ በዚህ ዋጋ ገዝቶ ያነባል፤ የንባብ ባህሉንም ያሳድጋል ማለት ከባድ ነው" የሚሉት አቶ ነብዩ፣ ለዚህም፣ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ 1000ሺ እና 500 ቅጂ የሚታተሙ መጽሐፍት በ6ወራት ውስጥ እንኳ ተሸጠው አለማለቃቸው ማሳያ ነው በማለት፣ የወረቀት ዋጋ ጭማሪው ከንባብ ባሕል አለመዳበር ጋር ተዳምሮ አታሚና አሳታሚው፣ ብሎም ማኅበረሰብ ላይ የፈጠረውን ጫና ያስረዳሉ። በተለይ፣ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ የሚተላለፉ ፈጣን፣ አጭርና ፍሬ አልባ ጽሑፎች በተበራከቱበት በዚህ ጊዜ፣ የሕትመት ኢንዱስትሪው መዳከም ሲታከልበት መጽሐፍት፣ ጋዜጣና መጽሔቶችን ለማንበብ ይሞክር የነበረውን ጥቂት ትውልድ፣ ጨርሶ እንዳያጠፋው የሚል ስጋት እንዳደረባቸውም ገልጸዋል። በሌላው ዓለም ሕትመት በጣም አድጎ እጅግ ዘመናዊ ደረጃ ላይ መድረሱን የጠቀሱት አቶ ነብዩ፣ እንዲያውም በብዙ ሀገራት የሕትመት ዘርፍ ሰፊ ትኩረት የሚሰጠው፣ እንደ ቡናና ነዳጅ ሁሉ ኢኮኖሚን የሚደግፍ ትልቅ የጀርባ አጥንት ነው ብለዋል።

የ101 ዓመት እድሜ ባለፀጋው የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የሕዝብ ግንኙነትና ማኅበራዊ ጉዳይ ኃላፊ አቶ ዳንኤል ኃይሌ በበኩላቸው፣ የወረቀት ዋጋ መናር ለሕትመት ኢንዱስትሪው ዳገት ሆነ እንጂ፣ ዛሬም ከፍተኛ የሕትመት ፍላጎት መኖሩን ያነሳሉ፤ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያን በመጠቀም በሰፊው የሚበልጡን ያደጉ ሀገራት እንኳ የሕትመት ሚዲያውንም አጠናክረው እንደያዙት የጠቀሱት ኃላፊው፣ በሀገራችን የወረቀት ዋጋ በከፍተኛ መጠን መጨመሩ፤ የሕትመት ውጤቶች ዋጋ እንዲንር ማድረጉን ይናገራሉ። እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ የአንድ ኪሎ ሕትመት መሸጫ ዋጋ 13 ብር እንደነበር አስታውሰው፤ ከ2010 ዓ.ም ወዲህ ደግሞ 13 ብር ከነበረው የመሸጫ ዋጋ ላይ የ115 ከመቶ ጭማሪ በማድረግ 28 ብር፣ ከመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ 28 ብር ከነበረው የአንድ ኪሎ ሕትመት መሸጫ ዋጋ ላይ ከእጥፍ በላይ በመጨመር ወደ 62 ብር ከፍ ማድረጉንም አውስተዋል። ድርጅቱ ለዓመትና ሁለት አመት የሚያስፈልገውን ወረቀት በአንድ ጊዜ ገዝቶ ማስገባት መቻሉ፣ በወረቀት ላይ የታየው ከፍተኛ ጭማሪ የፈጠረው ውጥረት እንዲቀንስለት ያደረገ ቢሆንም፣ ጭማሪው አሳታሚዎች ላይ ከፍተኛ ጫና መፍጠሩን ይጠቁማሉ። ድርጅቱ በአጠቃላይ 14 የግልና የመንግሥት ጋዜጦችን የሚያትም ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በተለያየ ቋንቋ የሚያሳትማቸው 6 ጋዜጦች፣ 4 የመንግሥት ተቋማት የሚያሳትሟቸው ጋዜጦችና አዲስ አድማስ፣ ፎርቹን፣ ካፒታልና ሪፖርተር የተሰኙ የግል ጋዜጦች በዋጋ ጭማሪው ምክንያት በአማካይ ከ40 ከመቶ በላይ የቅጂ ብዛት መቀነሳቸውን ኃላፊው ተናግረዋል።

**የወረቀት በሀገር ውስጥ በበቂ መጠንና ጥራት አለመመረትና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ወረቀት ላይ የሚጣለው ተደራራቢ ታክስ፣ ከውጭ ምንዛሪ ጭማሪ ጋር ተዳምሮ፣ የሕትመት ዋጋን እያናረ፣ አታሚና አሳታሚዎችንም ከኢንዱስትሪው እያራቀ ይገኛል**



አቶ ተፈራ ሥዩም

እርሳቸው እንዳሉት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የወረቀት ዋጋ ጭማሪ ከውጪ ምንዛሪ ዋጋ መጨመር ጋር ተዳምሮ የሕትመት ዋጋ ላይ ጫና መፍጠሩ እንዳለ ሆኖ፣ ወረቀት ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባና በድጋሚ፣ ታትሞበት ጋዜጣና መጽሔት ሆኖ ሲወጣ የሚጣልበት ተደራራቢ ታክስ ለሕትመት ኢንዱስትሪው ፈተና ሆኗል።



አቶ ዳንኤል ኃይሌ

**ድርጅቱ ለዓመትና ሁለት አመት የሚያስፈልገውን ወረቀት በአንድ ጊዜ ገዝቶ ማስገባት መቻሉ፣ በወረቀት ላይ የታየው ከፍተኛ ጭማሪ የፈጠረው ውጥረት እንዲቀንስለት ያደረገ ቢሆንም፣ ጭማሪው አሳታሚዎች ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል**

"ነጋዴ እንደመሆናችን ሌላውንም ዘርፍ እናያለን፣ ከሕንጻ ተቋራጭ፣ ከኤሌክትሪክ እቃዎች እና ከሌሎችም ዘርፎች አንጻር ወረቀት ላይ የታየው ጭማሪ የተለየ ነው" ያሉት አቶ ነብዩ፣ ወረቀት ላይ ከሚጣለው ታክስ በተጨማሪ ለሕትመት ሥራ ፈተና የሆነው፣ ወረቀት በውስን አስመጪዎች እጅ መሆኑ ሲሆን፣ ይህም ዋጋ አወዳድሮ ለመግዛት ምቹ ሁኔታ አለመፍጠሩን ያስረዳሉ።

የሕትመቱ ዘርፍ ትኩረት የተነፈገው ነው ያሉት አቶ ተፈራ፣ ወረቀት ከሚጣልበት ተደራራቢ ታክስ የተነሳ ከውጪ አታሚዎች ጋርም በዋጋ ተወዳዳሪ መሆን አለመቻሉን ጠቅሰው፣ በዚህ ሳቢያ፣ መንግሥት በየጊዜው በዓመት 100 ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ ገንዘብ በማውጣት የተማሪ መጽሐፍትን በውጪ ሀገራት እያሳተመ እንደሚገኝም አንስተዋል። እንደእርሳቸው ገለጻ፣ መንግሥት የተማሪዎችን መጽሐፍት ከሀገር ውጪ ማሳተምን የመረጠው በሦስት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው፣ ወረቀት ላይ የሚከፈለው ቀረጥ፣ መጽሐፍ ከውጪ ሀገር ሲገባ ስለማይከፈልበት፤ መንግሥትም ይህን አማራጭ መጠቀሙ ሲሆን፣ በዚህም ሀገር ውስጥ ካለው የሕትመት ዋጋ አንጻር ሲታይ እስከ 50 ከመቶ ቅናሽ ያስገኛል። ሌሎቹ ምክንያቶች ደግሞ የሕትመት ፍጥነትና ጥራት ጉዳዮች ናቸው። መንግሥት "የሀገር ውስጥ አታሚዎች መጽሐፍቶቹን በፍጥነትና በሚፈለገው ጥራት አያደርሱልኝም" የሚል ምክንያት እንደሚያስቀምጥ የሚናገሩት አቶ ተፈራ፣ ይሁን እንጂ ችግሮቹ ቢኖሩም እንኳ፣ አንድ ሰው የቤቱ በር ችግር ቢኖርበት፤ በር ማስተካከሉን ትቶ ውጭ እንደማያድረው ሁሉ፣ መንግሥትም የሀገር ውስጥ አታሚዎችን ችግሮች ለይቶ በመፍታት ዘርፉን ለማበረታታት ቋሚ መፍትሔ መስጠት እና አላስፈላጊ የውጭ ምንዛሪንም ማውጣት እንዳልነበረበት ያሰምሩበታል።አቶ ተፈራ አያይዘውም፣መንግሥት የተማሪ መጽሐፍትን ለማሳተም በየጊዜው በርካታ ገንዘብ ከሚያወጣ አንድ ጊዜ መከፈል ያለበትን ዋጋ ከፍሎ ጥራትና ብዛት ላለው ሕትመት የሚያገለግሉ ማሽነሪዎች በሀገራችን እንዲኖሩ ቢያግዝ ለኢንዱስትሪውም ሆነ ለሀገር እጅግ መልካም ይሆን ነበር ብለው ይመክራሉ።

አቶ ነብዩም በተመሳሳይ፣ መንግሥት የተማሪ መጽሐፍትን በየጊዜው ሕንድና ቻይና እንደሚያሳትም ጠቅሰው፣ ይሁን እንጂ መንግሥት በርካታ የውጪ ምንዛሪ አውጥቶ መጽሐፍቱን ውጪ ሀገር ከሚያሳትም፣ ሀገር ውስጥ ላሉ አታሚዎች አከፋፍሎ ቢያሠራ ኢንዱስትሪውን ከማበረታታት ባሻገር የውጪ ምንዛሪንም ለማስቀረት ይጠቅም እንደነበር ይናገራሉ። ውጪ ሀገር ታትመው የሚመጡ አንዳንድ መጽሐፍትም በጉልህ የሚታይ የጥራት ችግር ያለባቸው መሆናቸውን ጭምር መታዘባቸውን ያስረዳሉ።

በአታሚዎችና አሳታሚዎች ማኅበር አማካኝነት ለሕትመት ሴክተሩ ኢንዱስትሪ መንደር የሚሆን ቦታ ይዘጋጅልን ብለው መጠየቃቸውን ያወሱት የማኅበሩ ፕሬዚዳንት፣ ጥያቄያቸው መልስ ካገኘ፣ ወደ ውጪ ሀገር የሚላኩ ሕትመቶችን ሀገር ውስጥ ማሳተም እንደሚቻል፣ በርካታ የሥራ እድልም እንደሚፈጠር፣ የውጭ ምንዛሪን ማስቀረት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርንም መፍጠር ይቻላል ይላሉ። ዘርፉን ለማበረታታት ተብሎ የማተሚያ ማሽን ከቀረጥ ነጻ እንዲገባ የተደረገበት ሥርዓት መኖሩንም ፕሬዚዳንቱ ጠቅሰው፣ ይህም ጅምር



አቶ ነብዩ በለጠ

**“መንግሥት በርካታ የውጪ ምንዛሪ አውጥቶ መጽሐፍቱን ውጪ ሀገር ከሚያሳትም፣ ሀገር ውስጥ ላሉ አታሚዎች አከፋፍሎ ቢያሠራ ኢንዱስትሪውን ከማበረታታት ባሻገር የውጪ ምንዛሪንም ለማስቀረት ይጠቅም ነበር**

ለዘርፉ ዕድገት መልካም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች አጋዥ አሠራሮችንም በመተግበር ምቹ ሁኔታን መፍጠር እንደሚቻል ጠቁመዋል። እንዲህ ዓይነት ኢንዱስትሪዎች ጥሬ እቃ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲኖር ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ ያሳሰቡት አቶ ነብዩም፣ ወረቀት በሀገር ውስጥ በበቂ መጠንና ጥራት መመረት ቢችል ኖሮ የሕትመት ኢንዱስትሪው የተጋረጡበትን ችግሮች ማለፍ ይችል ነበር በማለት ቁጭታቸውን ያጋራሉ። እንደእርሳቸው አስተያየት፣ ከ90 ከመቶ በላይ የሚሆነው የሀገር ውስጥ የወረቀት ፍላጎት ከውጪ ሀገር የሚገባ ሲሆን፣ በሀገር ውስጥ የሚገኙ በጣት የሚቆጠሩ የወረቀት ፋብሪካዎች ቢኖሩም፣ የማምረት አቅማቸው አነስተኛ፣ የሚያመርቷቸው ወረቀቶችም የምርት ጥራታቸው የወረደ፣ ለማሽን ሥራ የሚያስቸግሩ እና ለደንበኞች ለማቅረብም የማይመረጡ ናቸው።

በሀገራችን ትልቁ የሕትመት ማተሚያ ተቋም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ነው። ድርጅቱ በዓመት በአማካይ 2 ሺህ 354 ቶን ወረቀት ከውጪ ያስገባል። 746 ቶን ወይም ድርጅቱ ከሚያስፈልገው የወረቀት ፍጆታ መካከል 30 ከመቶ የሚሆነውን ደግሞ ወንጂ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ፐልፕና ወረቀት ፋብሪካ አክሲዮን ማኅበር እና አኒሞል ኢትዮጵያ ፕሮዳክትስ ሊሚትድ ኃ/የተ/የግል ማኅበር ከተሰኙ የሀገር ውስጥ አምራቾች እንደሚገዛ የሚናገሩት አቶ ዳንኤልም፣ የሀገር ውስጥ አምራቾች በጣም ጥቂት ከመሆናቸው ባሻገር የወረቀት ጥራታቸውም ከውጪ እንደሚገባው ደረጃውን የጠበቀ አለመሆኑን ገልጸዋል። በተለይ ደግሞ ድርጅቱ በብዛት የሚጠቀመው የጋዜጣ ወረቀት በሀገር ውስጥ እንደማይመረትም ጠቁመዋል። ከዚሁ ጋር በማያያዝም፣ ወረቀትን ጨምሮ፣ ለሕትመት ሥራ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቀለም፣ ኬሚካል፣ ፕሌት፣ የመሳሰሉት በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግ፣ እነዚህን ግብዓቶች ለማምረት ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ሲኖሩም ማበረታታት ያስፈልጋል ለሚለው ሐሳባቸውም አጽንዖት ሰጥተዋል።

“የውጭ ምንዛሪን ከመፍቀድ አንጻር መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ስለሚደግፈን፣ ብዙ የሕዝብ ልሳኖችን ማተም፣ የሚያስፈልገንንም ወረቀት በብዛት ማስመጣት ችለናል” ያሉት አቶ ዳንኤል፣ በርካታ ገንዘብ ወጥቶበት፤ ረጅም ሂደትንም አልፎ የምናገኘውን ወረቀት እያንዳንዱ ሠራተኛ ከብክነት በፀዳ ሁኔታ በአግባቡ እንዲጠቀም የግንዛቤ ሥራ እንደሚሠሩም ይናገራሉ። በተጨማሪም ወረቀቶች ከሕትመት ማሽኖች ጋር የተመጣጠኑ እንዲሆኑና ከዚህ አልፈው የሚወጡ ወረቀቶችን በመፍጨት ለሌላ ጥቅም እንዲውል የማድረግ ሥራ ስለሚሠራ፣ ከዚህ በፊት ይከሰት ከነበረው የወረቀት ብክነት አንጻር ሲታይ ከፍተኛ መሻሻል አለ ብለዋል።

የሕትመት ኢንዱስትሪው ከተጋረጡበት ፈተናዎች መካከል አንዱ በቂ የውጪ ምንዛሪ አለማግኘት እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ነብዩ፣ የወረቀት አስመጪዎቹ የውጪ ምንዛሪውን የምናገኘው ኤክስፖርት ከሚያደርጉ ሰዎች ገዝተን ነው እንደሚሉና ይህ ደግሞ፣ ወረቀት ለመግዛት የሚከፈለውን ዋጋ ከፍ እንደሚያደርገው ይናገራሉ።

አቶ ተፈራም ለዚህ ሴክተር የውጭ ምንዛሪ ቢመቻችና አታሚው የሚያስፈልገውን ወረቀት ራሱ የሚያስገባበት ሁኔታ ቢፈጠርለት ኢንዱስትሪው ላይ ያሉ ችግሮች ሊቃለሉ እንደሚችሉ ያምናሉ። ስለሆነም፣ መንግሥት "ወረቀት" ኅብረተሰብ መረጃና እውቀት የሚያገኙበት ሀገር የሚገነባበት መሠረታዊ ነገር እንደሆነ ተረድቶ ዘርፉን ትኩረት ሰጥቶ ቢመለከተው መልካም ነው የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

የአታሚዎችና አሳታሚዎች ማኅበር ላለፉት ሁለት ዓመታት በተለያዩ ምክንያቶች ተዳክሞ መቆየቱን፣ ድምፁን የሚያሰማበት መድረክም እንዳልነበረው የሚናገሩት የማኅበሩ ፕሬዚዳንት አቶ ተፈራ፣ አሁን ላይ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አማካኝነት በድጋሚ እንዲጠናከር መደረጉንና ስትራቴጂ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝም ገልፀዋል። ድርጅቱ መንግሥት ለኅብረተሰቡ በጣም አስፈላጊ የሆኑ የዕቃ ዋጋዎችን ለማረጋጋት የወሰዳቸውን እርምጃዎች በሕትመት ኢንዱስትሪውም እንዲደግመው፣ ከቀረጥ ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎችም በድጋሚ የሚታዩበት ሁኔታ እንዲፈጠር የሚመለከታቸውን አካላት ለማነጋገር በጥረት ላይ እንደሚገኝና ጥረቱም መፍትሔ ያመጣል ብለው እንደሚያስቡ ፕሬዚዳንቱ ያስረዳሉ። የሕትመት ኢንዱስትሪውን ማበረታታት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ የሀገርን ኢኮኖሚ ከማገዙ ባሻገር ብዙ መጽሐፍት እንዲታተሙና ወደ ገበያ እንዲወጡ፤በዚህም አንባቢና ነገሮችን በሚዛን የሚያይ አስተዋይ ትውልድ እንዲፈጠር ማስቻሉ ትልቁ ጠቀሜታ ነውም ብለዋል።

አቶ ነብዩም፣ የህትመት ኢንዱስትሪው የተጋረጠበትን ተደራራቢ ችግር ለመፍታት በማኅበር ሆነው እየተንቀሳቀሱ፣ በየጊዜው እየተሰባሰቡና እየመከሩ እንደሆነ አንስተው፣ ለሁሉም ነገር መሠረታዊ የሆነውን የሀገር ሰላም ማጽናት ከተቻለ፣ በኢንዱስትሪው ላይ ያሉ ችግሮች በሂደት እንደሚቀረፉ ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል። አቶ ዳንኤልም በበኩላቸው ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት አንጋፋ እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ ሕትመቶችን ምንም ትርፍ ሳያገኝ የሠራተኛና የጥሬ እቃ ብቻ በማስከፈል እንደሚሠራና በዘርፉ ያሉ ፈተናዎችና መፍትሔዎችን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር የፓናል ውይይቶችን በማካሄድ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንዳለ ገልጸው ወደፊትም ጥረቱን አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የሥልጣኔ፣ የአዳዲስ ግኝቶችና ሐሳቦች መተላለፊያ፤ የትውልዶች መገናኛ ድልድይ፣ የዴሞክራሲ መለማመጃ መሣሪያ የሆነውን የሕትመት ዘርፍ ከተጋረጡበት ፈተናዎች ታድጎ መልካም እድሎችን መፍጠር፤ ትውልድ ሳይታነጽ፣ ትናንትን ከዛሬ ሳያጋምድ፣ የኋላውን ከፊቱ ሳያስተሳስር የእውር ድንበሩን ከመጓዝ መታደግ ነውና የሚመለከተው ሁሉ ይድረስለት የሚለው የዝግጅት ክፍላችን መቋጫ መልዕክት ነው!

# ከደስታ ባሻገር

**ንጉሤ ተስፋዬ**

ወርሃ ጥር በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል አርሶ አደራችን በከፍተኛ ትጋት ሲለፋበት የቆየው የግብርና ስራ የሚጠናቀቅበትና አዝመራ ተሰብስቦ ጎተራ አስገብቶ እፎይ የሚልበት የዕረፍት ወቅት ነው። ከዕረፍቱ ጋር ተያይዞ ደግሞ ወሩ የተለያዩ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ስርዓቶች ይከናወኑበታል። በደስታና ጭፈራ የተሞሉት ክዋኔዎቹም ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ ከፍተኛ የሆነ ሀብትና ገንዘብ የሚፈስባቸው ናቸው።

በዚህ ረገድ የመጀመሪያው ተጠቃሽ የጥምቀት በዓል ነው። የጥምቀት በዓል ላጤው የትዳር ጓደኛ የሚመርጥበት/ሎሚ የሚወረወርበት/ እና በሁሉም ተወዳጅ የሆነችን ልጃገረድ ለግል ለማድረግ ከፍተኛ ፉክክር የሚያደርግበት፣ ጓደኛ ያለው ደግሞ በትዳር የሚጣመርበት በመሆኑ ይለያል። ለበዓሉ "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ...." በሚል ሁሉም ለጌጣጌጥና ለአልባሳት ተጨንቆና ተጠቦ በመዘጋጀት የደስታውና የጭፈራው ተካፋይ ይሆናል። ከጓደኛ እና ከአካባቢው በልጦ ለመገኘት ሲባልም ከትልቅ እስከ ትንሽ ሁሉም የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ነው። በጥምቀት በዓል ዕለት አምሮና ደምቆ መታየት ለትዳርም ሆነ ለከንፈር ወዳጅነት ለመታጨት አንድ መስፈርት ነው። በመሆኑም አንዳንድ ጊዜ ከመጠን በላይ መዋቡ መራጭን በማሳሳት ወቅቱ ካለፈ በኋላ ቁጭት ላይ የሚጥልበት አጋጣሚም ይስተዋላል። እዚህ ላይ አንድ ጨዋታ ትዝ አለኝ። አንድ የወንድ እናት በበዓሉ ዕለት ተውባ ያዩዋትን ልጃገረድ ለልጃቸው አጭተው ካጋቡ በኋላ ሁኔታዋን ሲያዩዋት እንደጥምቀቱ ዕለት አላስደስታቸውምና በስህተታቸው ሲያዝኑ ይቆያሉ። በዓመቱ ጥምቀት ላይ የተዋቡ ልጃገረዶችን ሲያዩ «የባለፈው ጥምቀት እኔን ገድለሃል፤ የዘንድሮው ደግሞ ማንን ትገድል ይሆን?» አሉ ይባላል።

በጨዋታ ያነሳነው ጋብቻ በወርሃ ጥር በስፋት ይፈፀማል። ከሠርግ ድግስ ጋር በተያያዘ የሚወጣው ወጪ በእጅ ያለን ሀብትና ገንዘብ ከማራቆት በዘለለ ብድር ውስጥ የሚዘፈቁ ብዙዎች ናቸው። ከሠርጉ በኋላ ከሚመጣው ዘርፈ ብዙ ጣጣ ይልቅ ከትላንት ደጋሾች ከእነ እገሊትና ከእነ እገሌ እንዴት አንሳለሁ በሚል ሀሳብ መጨነቁ ያመዝናል። በማህበረሰባችን በግልጽ እንደምናስተውለው የዚህ አስተሳሰብ ተገዥ ሙሽራውና ሙሽሪት ብቻ አይደሉም። ቤተሰብ፣ ወዳጅ፣ ዘመድ እና አካባቢውም ጭምር የአስተሳሰቡ ሰለባ ናቸው። የሚገርመው ደግሞ ደጋሹ ነገ የሚያጋጥመውን ችግር ከወዲሁ እያወቀውም ቢሆን በይሉኝታና በተለያዩ ተጽዕኖዎች ምክንያት የቋጠረውን ሀብቱን አሟጥጦ፣ የሌለው ደግሞ ተበድሮ ወደ ችግሩ የሚገባ መሆኑ ነው።

ይህን ሃሳብ ታጠናክራለች ብየ የማስባትን አንዲት ትንሽ ገጠመኝ ላቅርብ። ጥንዶቹ ከተዋወቁ ረጅም ጊዜ አልሆናቸውም። ይሁን እንጂ በጣም ይዋደዳሉ። ይህን ፍቅራቸውን ደግሞ ወደ ትዳር ለመቀየር ተስማምተዋል። በጋብቻው ላይ የሚያራምዱት ሃሳብ ግን የተለያየ ነበር። ሴቷ ገና ተማሪና ለድግስ የሚሆን ገንዘብ ባይኖራትም ለግሏ፣ ለቤተሰቧና ለአካባቢው ማህበረሰብ ክብር በመጨነቅ ጋብቻው በሠርግ ይሁን የሚል ጽኑ አቋም ነበራት። ወንዱ ደግሞ የመንግስት ሠራተኛ ቢሆንም ሠርግ ለመደገስ የሚያበቃው ደመወዝ የለውም። ያጠራቀመው ገንዘብም ሆነ ሀብት ስለሌለው መደገሱን አልፈለገውም። ይህን የሰፋ የሃሳብ ልዩነታቸውን ለማጥበብ ብዙ ጊዜ ተወያይተውበታል። ጉዳዩን በተደጋጋሚ ያውጡት ያውርዱት እንጂ በሃሳብ መቀራረብ ግን አልቻሉም። መጨረሻ ላይ የሴቷ ሃሳብ አሸነፈና የድግስ አነስተኛ ባይኖረውም፣ ለአነስተኛ ድግስ የሚሆን ገንዘብ በሚል ለመበደር ተስማምተው ሠርጉ ተደግሶ ተጋቡ።

ጥንዶቹ ተጋብተው ብዙ ሳይቆዩና ብድራቸውን ከፍለው ሳይጨርሱ፣ ሴቷ ከእርግዝና ጋር በተያያዘ ታመመችና ሆስፒታል ገባች። "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ ለህክምና የሚሆን ገንዘብ በማስፈለጉ በብድር ላይ ሌላ ብድር የግድ ሆነ። ከብዙ የህክምና ወጪ በኋላ ልጁ በጤና ተወልዷል። ይሁን እንጂ የተደራረበን ዕዳ እየከፈሉ ልጅ ማሳደግና በልቶ ማደር መቻልን በተመለከተ ያለውን ጭንቀትና ችግር እናንተ ራሳችሁ አስቡት።

የሰው ልጅ ካስተዋለው፣ ካዳመጠውና ካነበበው ብዙ መማር እንደሚኖርበት ይታሰባል። ድግስን በተመለከተ በገሃዱ ዓለም እየተከናወነ ያለው ሀቅ ግን በአብዛኛው ማለት በሚቻልበት ሁኔታ መሆን ያለበት ነገር አይደለም። ምናልባትም በዚህ በኩል ማህበረሰቡ ተምሯል ከተባለ በሌላው ሳይሆን በራሱ ውድቀት ነው "ከወደቁ ወዲያ መፈራገጥ ለመላላጥ" እንዲሉ። በመሆኑም ከአቅም በላይ ወጪ አውጥቶ በመደገስ ለጊዜው ተደስቶ በማግስቱ ሊወጡት ከማይችሉት ችግር ውስጥ ገብቶ መዳከር ትላንት ነበር፤ ዛሬ አለ፤ ነገም እንደሚኖር በገሀዱ ዓለም ብዙ አመላካቾች ይስተዋላሉ። ከዚህ በመነሳት ሰው መቼ ነው ቆም ብሎ ስለ ራሱ ማሰብ የሚጀምረው? እላለሁ።

ቀደም ሲል በአንዳንድ ክልሎች አርሶ አደሩ ዓመት ሙሉ የለፋበትን ሀብት በአንድ ወር ደግሶ እየጨረሰ ራሱንና ቤተሰቡን ለከፍተኛ ችግር ማጋለጡ ተገቢ አይደለም በሚል የአንድ ወቅት አጀንዳ ሆኖ ነበር። ችግሩን ለማቃለልም ድግሱን በአግባቡ እንዲደግስ የግንዛቤ ፈጠራና የማስተማር ስራ መሰራት ተጀምሮ እንደነበርም መረጃው ነበረኝ። ከዚያም አልፎ በአካባቢው ማህበራዊ አደረጃጀቶች እንደ ዕድር ዓይነቶች አማካኝነት ለድግስ ከፍተኛ ወጪ ማውጣት ጎጂ ባህል ነው በሚል እንዲወገዝና እንዲስተካከል አስገዳጅ አሰራርም ተቀምጦ ነበር። ይህ ጥሩ ጅምር ግን ዘላቂ ሆኖ አልቀጠለም።

በቅርቡ ደግሞ በአማራ ክልል የምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር ምክር ቤት በዚህ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አስተላልፏል። የውሳኔው ዋና ሃሳብ ዞኑ የበርካታ ጠቃሚ ባህላዊ እሴቶች ባለቤት እንደሆነና በክልሉ ከሚታወቁ ትርፍ አምራች ዞኖች መካከልም አንዱ መሆኑን ጠቅሷል። ይሁን እንጂ ማህበረሰቡ የተንዛዛ እና ከአቅም በላይ ድግስ በመደገስ ለፍቶ ያገኘውን ምርት በማባከን የአመጋገብና የአለባበስ ስርዓቱን ከመጉዳት አልፎ፣ ለርሃብና ለስደት መጋለጡን አንስቷል። በመሆኑም ምክር ቤቱ ችግሩን በዘላቂነት ለማስወገድ እንዲቻል በየደረጃው የሚገኘው የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች አመራሮች ጉዳዩን ቁልፍ ተግባር አድርገው እንዲይዙት በማሳሰብ የውሳኔውን ሙሉ ቃል ጥር አንድ ቀን 2015 ዓ.ም በደብዳቤ አሳውቋቸዋል፤ እሰየው የሚያስብል ተግባር ነው።

በእኔ አስተሳሰብ ድግስ አይደገስ፣ ሰርግም አይሰረግ የሚል ዕምነት የለኝም። ድግሱም ሆነ ሠርጉ ግን የነገ ህይወትን ታሳቢ ያደረገ ይሁን ባይ ነኝ። ከ"ማን አንሼ" ከሚል ኋላ ቀር አስተሳሰብና ከማንኛውም ዓይነት ይሉኝታ በመላቀቅ አቅምን ያገናዘበ ድግስ መደገስ መልካም ነው። ተጋቢዎችም ቢሆኑ ለነገ ህይወታቸው ተመሳሳይ አስተሳሰብና አቋም ሊኖራቸው ይገባል። አንደኛው የዛሬን ደስታና ክብር ብቻ አስቦ "እኔ ያልኩት ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ" የሚል፣ ሌላው ደግሞ የነገውንም ኑሮ ጭምር አሳቢ በመሆን በሃሳብ መለያየት ተገቢ ነው ብየ አላስብም። ደግሞም ዛሬ ላይ በትዳር አመሰራረት በትዳር አጋሮቹ መካከል የሃሳብ ልዩነት ካለ መጪውን ረጅም የኑሮ ዘመን እንዴት መግባባት ይቻላል? የሚለውን ሳይቀር ከግምት ማስገባት የሚጠቅም ይመስለኛል።

የነገን ህይወት ያለችግር ተስማምቶ እና ተግባብቶ ለመኖር በተጋቢዎቹ መካከል ስምምነት ከተፈጠረ ደግሞ የሰርግ ዝግጅቱ ብዙ አያሳስብም። በአንዳንድ አካባቢዎች የሚስተዋሉ በአነስተኛ ወጪዎች የሚፈጸሙ ጥሩ ጅምሮችን መከተል አንዱ አማራጭ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አሁን ላይ አልፎ አልፎ እየታየ እንዳለው እንደ "መቄዶኒያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል" ከመሳሰሉ በጎ አድራጊ ድርጅቶች ጋር በአነስተኛ ወጪ የተለያዩ ዝግጅቶችን አብሮ ማሳለፍ እየተለመደ መጥቷል። በመሆኑም ሠርጉን ፎቶግራፍ በመነሳት፣ ምሳ በማብላት፣ አነስተኛ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ እግረ መንገዱን የበጎ አድራጊ ድርጅቶችን የተቀደሰ ዓላማ አግዞ፣ ረድቶና ዕውቅና ሰጥቶ ማለፍ እሰየው የሚያስብል ተግባር መሆኑን ማሰብ ተገቢ ነው። በዚህም ከደስታ ባሻገር የሰብዓዊነት ተግባር በመፈጸም የዜግነት ድርሻን በመወጣት በቀጣይ የህይወት ዘመን ሁሉ የመንፈስ እርካታን ማግኘት መታደል ነው።



# ትኩረት የሚሻው የመድሃኒት አቅርቦት

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

ጤና ይስጥልን! ከሀብት ሁሉ የሚልቅ ሀብት ጤና ነው። የአገሬ ሰው ሲመርቅ ረጅም እድሜ ከጤና ጋር ይስጥህ ይላል፤ ፈጣሪውንም `ጤናዬን አትንሳኝ` ብሎ ይለምናል። በሕይወት ለመቆየት፣ ሰርቶ ለመለወጥ፣ ቤተሰብና ሀብት ለማፍራት ጤና መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታ ነውና በተቻለን መጠን ጤናችንን ለመጠበቅ እንሞክራለን። ጤናችንን የሚያቃውስ ሕመም ከገጠመን ደግሞ ወደ ጤና ተቋማት እናመራለን፤ ከፈጣሪ ቀጥሎ ፈውስ እናገኛለን ብለን የምናምነው በእነዚህ ተቋማት ነውና። የጤና ተቋማቱ አገልግሎት የመጨረሻ ግብ ደግሞ የታካሚዎችን ህመም የሚያስታግሱና የሚፈውሱ መድሃኒቶችን ማዘዝና የታዘዙላቸውን መድሃኒቶች በታከሙበት ጤና ተቋም እንዲያገኙ ማስቻል ነው።

ይሁን እንጂ፣ በአሁኑ ጊዜ በግልጽ እንደሚስተዋለው ማህበረሰቡ ወደ ህክምና ተቋም ለምርመራ ሄዶ የታዘዘለትን መድሃኒት እዚያው ምርመራ ባደረገበት፣ በተለይም፣ በአብዛኛው የመንግስት የጤና ተቋማት ማግኘት ከባድ እየሆነበት መጥቷል። ከጤና ተቋማቱ ዘንድ “መድሃኒቱ የለም” ማለትና አንዳንድ ጊዜም ከመርማሪ ሃኪሞች መድሃኒቱን ውጪ ግዙ ብሎ መታዘዝም እየተለመደ መጥቷል። በዚህም ምክንያት ህብረተሰቡ ለተጨማሪ ወጪ ከመዳረጉም ባሻገር በመድሃኒት ፍለጋ የሚያሳልፈው ውጣ ውረድ ከበሽታው ለመፈወስ የሚወስድበትን ጊዜ እያራዘመው፣ ለተጨማሪ በሽታ እየዳረገውም ይገኛል።

ከዚህ አንጻር፣ በአገራችን የመድሃኒት ግዢ ሂደትና አቅርቦት ምን ይመስላል፤ በመድሃኒት አቅራቢ አገልግሎትና በጤና ተቋማት መካከል ያለው ግንኙነትስ ምን መልክ አለው፣ በሚሉና በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸውን በተመለከተ ከኢትዮጵያ መድሃኒት አቅራቢ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰሎሞን ንጉሴ፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ፋርማሲ አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ደበላ ገመዳ እና ከአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ፋርማሲ ዳይሬክተር አቶ አበራ ገላና ጋር ቆይታ አድርገናል።

## የመድሃኒት ግዢ

ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፣ የመድሃኒት አቅራቢ አገልግሎት ለመንግሥት የጤና ተቋማትና ክፍተት ላለባቸው የግል የጤና ተቋማት መድሃኒቶችን የሚያቀርብ ሲሆን፣ በአሁኑ ሰዓት ግን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ እየሰራ ያለው ለመንግሥት የጤና ተቋማት ብቻ ነው። አገር ውስጥ ከሚገቡት ጠቅላላ መድሃኒቶች መካከልም ተቋሙ 86 ከመቶ የሚሆነውን ድርሻ ይወስዳል።

ከሶስት ዓመታት በፊት፣ 75 ከመቶ የሚሆኑ መድሃኒቶችን ከውጪ አቅራቢዎች 25 ከመቶ ያህሉን ከአገር ውስጥ ይገዛ የነበረ ቢሆንም፣ የአገር ውስጥ ምርት በመዳከሙ ምክንያት በዚህ ዓመት 92 ከመቶ መድሃኒት ከውጪ አቅራቢዎች፣ ሲገዛ ስምንት ከመቶ ብቻ ከአገር ውስጥ አቅራዎቢዎች ለመግዛት ተገዷል። ቀደም ሲል በአገር ውስጥ ይመረቱ የነበሩ፣ እንደ ሽሮፕ፣ በደም ስር የሚሰጡ ፈሳሾች የመሳሰሉት፣ አሁን ላይ እየተመረቱ ባለመሆናቸው የአገር ውስጥ ግዢ ቀንሷል። ቢሆንም፣ የአገር ውስጥ አቅምን አሟጦ ከመጠቀም አንጻር መጀመሪያ የአገር ውስጥ ጨረታ በማውጣት፣ የአገር ውስጥ አቅራቢ እድል እንዲያገኝ ከተደረገ በኋላ፣ ዓለም አቀፍ ጨረታ እንዲወጣ ይደረጋል። የአገር ውስጥ አቅራቢዎች ለብቻቸው ከሚሳተፉበት በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ጨረታም ተሳታፊ ይሆናሉ። ዋጋቸው እስከ 25 ከመቶ ከፍ ቢል እንኳ ቅድሚያ የማግኘት እድል አላቸው። እነዚህ እድሎች ተመቻችተውም የአገር ውስጥ አቅራቢ ድርሻ ግን ከ10 ከመቶ በታች ነው።

አቶ አበራ እንደነገሩን ደግሞ፣ አማኑኤል ሆስፒታል የመድሃኒት ግዢ የሚፈፅመው ከመድሃኒት አቅርቦት አገልግሎት ጋር የዓመት ውል በመዋዋል ሲሆን፣ አገልግሎቱ ለጤና ተቋሙ በየሳምንቱ መድሃኒት ያቀርብለታል። ከአገልግሎቱ ያጣውን መድሃኒት ደግሞ ጨረታ በማውጣት ከግል አቅራቢዎች ይገዛል። በተጨማሪም ከሌሎች የጤና ተቋማት አገልግሎት ላይ የማይውሉ መድሃኒቶችን በቅያሬ መልክ ወይም በልገሳ ይቀበላል።

## አገልግሎቱ ለመድሃኒት ግዢ ምን ያህል ያወጣል?

የመድሃኒት አቅራቢ አገልግሎት የመግዛት አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ይህም ቢሆን፣ በሌሎች ሸቀጦች

ላይ የሚታየው የፍላጎትና የአቅርቦት አለመመጣጠን በመድሃኒትም ላይ አለ ይላሉ። ዳይሬክተሩ እንደገለጹት፣ አገልግሎቱ ባለፈው ዓመት ለመደበኛ መድሃኒት ግዢ ብቻ 10 ቢሊየን ብር አውጥቷል። ከዚህ፣ የተገላባጭ መድሃኒት ፈንድ በተጨማሪ የ40 ቢሊየን ብር ግዢና ድጋፍም አከናውኗል። ተገላባጭ መድሃኒት ፈንድ የሚባለው አገልግሎቱ መድሃኒቶችን ገዝቶ፣ ጥቂት ትርፍ ጨምሮበት እያገላበጠ የሚያስተዳድረው ገንዘብ ሲሆን፣ ተቋሙ ለትርፍ የተቋቋመ ባለመሆኑ ጭማሪው አስተዳደራዊ ወጪዎችን ብቻ መሸፈንን ታሳቢ ያደረገ ነው። የጤና ፕሮግራም ገዝቶ የሚያገኘው የአገልግሎት ክፍያም ለመደበኛ በጀቱ እድገት ትልቅ አስተዋፅዖ ያደርግለታል። ሌላው፣ ከጤና ሚኒስቴርና ከተለያዩ ለጋሽ ተቋማት ጋር ተግባብቶ ውል በመግባት፣ የኤች አይቪ፣ ቲቢ፣ ወባ መድሃኒቶችና ክትባቶችን በማሰራጨት የሚያገኘው ገቢ ሲሆን፣ አገልግሎቱ፣ በጥቅሉ ባለፈው ዓመት የ51 ቢሊየን ብር ያህል ግዢ፣ አገልግሎትና ድጋፍ አከናውኗል። አቶ ደበላ በበኩላቸው የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ባለፈው ዓመት ከተለያዩ አቅራቢዎች የ135 ሚሊየን ብር መድሃኒት ግዢ እንደፈጸመ ይናገራሉ። አማኑኤል ሆስፒታል ደግሞ የ60 ሚሊየን ብር መድሃኒት ግዢ መፈጸሙን አቶ አበራ አሳውቀዋል።

## የዱቤ ሽያጭና ግዢ ምን ይመስላል?

"የግል አቅራቢዎች ክፍያ ወዲያውኑ ስለሚጠይቁና በጠየቁ ጊዜ ክፍያ ለመፈጸም የበጀት ጉዳይ እጃችንን ስለሚይዘው በዚህ ምክንያት የማንገዛቸው መድሃኒቶች ይኖራሉ" ያሉት አቶ ደበላ፣ የዱቤ ግዢ ለመፈጸም የማይቸገሩት ከመድሃኒት አቅራቢ አገልግሎት መሆኑን ይናገራሉ። አያይዘውም፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በአሁኑ ሰዓት፣ ከአገልግሎቱ የ50 ሚሊየን ብር እዳ እንዳለበት፣ ይህም መድሃኒት ለማቅረብ ለኮሌጁ ተግዳሮት እንደሆነበት ይገልጻሉ። የአገልግሎቱ ዳይሬክተር አቶ ሰሎሞን በበኩላቸው፣ የመድሃኒት አቅርቦት ስርጭት በቀጥታ ክፍያና በዱቤ ሽያጭ እንደሚካሄድ ጠቅሰው፣ የዱቤ ሽያጭ መጠን ከቀጥታ ክፍያ ሽያጭ መጠን እንደሚበልጥም አንስተዋል። እርሳቸው እንዳሉት፣ የዱቤ ሽያጭ አከፋፈል በጣም ትልቅ ችግር የፈጠረ፣ አገልግሎቱንም አጣብቂኝ ውስጥ የከተተ ነው። ይህንን ችግር ለመቅረፍ በቅርብ ጊዜያት የማስተካከያ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። የዱቤ ሽያጭ ስርዓት እንደ ስርዓት ችግር ባይኖርበትም፣ አስተዳደሩ ላይ ግን ከአገልግሎቱም ሆነ ከጤና ተቋማት ዘንድ ክፍተት አለ ያሉት አቶ ሰሎሞን፣ በተለይም፣ ከጤና ተቋማቱ ዘንድ ገንዘቡ የመንግሥት ነው በሚል እሳቤ ወደ ክፍያ አለማተኮር፣ በቂ በጀት ይዞ ከማስተዳደር አንጻር ክፍተቶች መኖራቸውን ጠቁመዋል። እርሳቸው እንደገለጹት፣ አገልግሎቱ በአሁኑ ሰዓት 1 ነጥብ 1 ቢሊየን ያልተከፈለው ዱቤ በጤና ተቋማት ዘንድ ሲኖረው፣ከዚህ ውስጥ ወደ 600 ሚሊየኑ በአንድና በሁለት ወራት ውስጥ ይከፈላል ተብሎ የሚጠበቅ ነው። ሌሎች እስከ አምስት ዓመታት የቆዩ ውዝፍ ክፍያዎች ካሉባቸው ተቋማት ጋር ደግሞ በመመካከር ወደ ክፍያ እንዲመጡ፣ በምክክር አልመጣ ያሉትን ደግሞ ክስ በመመስረት ወደ ሕግ በመውሰድ ክፍያዎችን የመሰብሰብ ሥራ እየተሰራ ነው።

ከዱቤ ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ለመፍታት፣ "ውል የተገባለት የአቅርቦት ሥርዓት"ን ወደ ስራ ለማስገባት እየተሰራ መሆኑን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፣ በሥርዓቱ የጤና ተቋማት ከአገልግሎቱ ጋር ውል በመግባትና ቅድመ ክፍያ በመክፈል ፍላጎታቸውን በተመጠነ መንገድ የሚያገኙበት ሲሆን፣ ይህም ተጠያቂነት ያለው አሰራር እንዲኖር፣ መድሃኒቶችንም ከብክነት የሚከላከል፤ የአገልግሎቱን የመግዛት አቅም በመጨመርም የክምችት መጠኑን ከፍ እንዲያደርግ የሚረዳው እንደሆነ አስገንዝበዋል።

## የመድሃኒት ስርጭቱ ምንን መነሻ ያደረገ ነው?

አገልግሎቱ በመላው አገሪቱ 19 ቅርንጫፎች ሲኖሩት፣ ሁለቱ በትግራይ ክልል የሚገኙና ወደ ስራ እየገቡ ያሉ ናቸው፤ "እኛ



አቶ አበራ ገላና



አቶ ሰሎሞን ንጉሴ

ከቅርንጫፎቻችን ጋር የምንገናኝበት፣ ቅርንጫፎቻችን ከጤና ተቋማት ጋር የሚገናኙበት የኮምፒውተር ሥርዓት አለ" ያሉን ዳይሬክተሩ፣ በእነዚህ ቅርንጫፎቹ አማካኝነት የሚደርሰውን የትመናና ምጠና ስራ እንዲሁም የመግዛት አቅምን ታሳቢ በማድረግ መድሃኒቶችን እንደሚያቀርብ፣ በዚህ አሰራር በአገራችን ካሉ ከ4000 በላይ ጤና ጣቢያዎችና ከ600 በላይ ሆስፒታሎች መካከል ለ80 ከመቶ ያህሉ ተደራሽ መሆን እንደቻለ፣ የመረጃ ሥርዓት መዘርጋቱም የት ቦታ የትኞቹ መድሃኒቶች አሉ ወይም የሉም የሚለውን ለማወቅ እንዳስቻለው ገልጸዋል።

## አገልግሎቱ ምን ያህል መድሃኒቶችን ያቀርባል! ምን ያህልስ በክምችት ይዟል!

አሁን ላይ አገልግሎቱ 262 መድሃኒቶችንና 151 የህክምና መገልገያዎችን በግዢ ያቀርባል። እንደ አቶ ሰለሞን ገለጻ እነዚህ መድሃኒቶች ወደ ተጠቃሚው እስኪደርሱ ድረስ ግን ያለው ችግር በጣም ሰፊ ነው። አገልግሎቱ መድሃኒቶችን ሙሉ በሙሉ ቢገዛም እንደ በጀት፣ ከፋርማሲ

ወደ ስቶር ያለው ሂደት፣ የሀኪሞች መድሃኒቶችን በብራንድ የማዘዝ ሁኔታ፣ በአጠቃላይ ያለመናበብ ችግሮች ከአገልግሎቱ ተነስቶ ወደ ጤና ተቋሙ ፋርማሲ፣ ከዚያም እስከ ተጠቃሚው እስኪደርስ ድረስ ረጅም ሂደቶችንና ተግዳሮቶችን ያሳልፋል። ስለሆነም አገልግሎቱ መድሃኒቶችን 100 ከመቶ አቀርባለሁ ቢልም፣ የተለያዩ አስቸጋሪ ሂደቶችን አልፎ ወደ ፋርማሲና ተጠቃሚው እስኪደርስ ያለው ሂደት አፈጻጸሙን ከመቶኛ ይቀንሰዋል። አቶ ደበላም አገልግሎቱ መድሃኒቶችን በበቂ መጠን አቀርባለሁ ቢልም፣ የሚያቀርቡት መድሃኒት ሆስፒታሉ ከሚፈለገው ከ50 እስከ 60 በመቶ ያህሉን ብቻ እንደሆነ፤ ይህ ልዩነት ለምን መጣ የሚለውን ደግሞ ማጣራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ከክምችት ጋር ተያይዞ ዳይሬክተሩ እንዳሉት፣ አገልግሎቱ ከሚያቀርባቸው ከላይ ከተጠቀሱ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች መካከል 84 ከመቶ ያህሉ በክምችት ይገኛሉ። በመሆኑም 16 ከመቶ የሚሆኑት በግዢ ሂደት ላይ ያሉ ናቸው። አገልግሎቱ፣ በክምችት አለኝ የሚለው የመድሃኒት አቅርቦት ቢያንስ ለአንድ ወር የሚያቆይ የመድሃኒት ክምችትን ነው።ይሁን እንጂ መሠረታዊና ሕይወት አድን የሚባሉ ቅድሚያ የሚሰጣቸው መድሃኒቶች ግን ሁሉም በሚባል ደረጃ በክምችት ውስጥ ይኖራሉ። መድሃኒቶች በክምችት በማይኖሩበት ጊዜ የተለያዩ እርምጃዎች ይወሰዳሉ። አንደኛው፣ ከግዢ ኤጀንሲ ጋር በመሆን የቀጥታ ግዢ ሥርዓትን መተግባር ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ በባህር ሳይሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ በአየር ትራንስፖርት አገር ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ዓለም አቀፍ ጫናዎች እየቀነሱ ስለመጡና ከሰላም መስፈን ጋር ተያይዞ ሰፊ ስራ መስራት ስለሚጠበቅ፣ የሚስተዋሉ ችግሮችን በሂደት እየተፈቱ የክምችት መጠንንም መጨመር ይቻላል።

## የመድሃኒት ግዢ ሂደትና አቅርቦት ተግዳሮቶች

አቶ ሰሎሞን በሰጡን ገለጻ፣ ኮቪድ፣ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ላይ የነበረው ጦርነትና በዚህ ሳቢያ የዓለም አቀፍ አቅራቢዎችና የፋይናንስ ተቋማት እምነት ማጣት፣ በግዢ ሂደት የተዋናዮች መብዛት፣ ለሎጂስቲክ አደጋ ተጋላጭነት የመድሃኒት ግዢ ሂደት ተግዳሮቶች ነበሩ። ሌላው አሁንም ያለ ችግር ደግሞ የአቅራቢ ማነስ ነው። ከውጪ ከሚገዙ መድሃኒቶች 78 ከመቶ ያህሉ ውስን አቅራቢ ያላቸው፣ የተቀሩት ደግሞ አንድ ብቻ አቅራቢ ያላቸው ናቸው። ምንም አይነት አቅራቢ የሌላቸው ልዩ መድሃኒቶችም አሉ። በዚህ ሁኔታ ውድድር አይኖርም፣ ከፍተኛ የሆነ የአቅርቦት መቆራረጥም ያጋጥማል።

አገልግሎቱ አቅርቦት ላይ ያለውን ችግር ለመፍታት ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን አካሂዷል።

**አገልግሎቱ አቅርቦት ላይ ያለውን ችግር ለመፍታት ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን አካሂዷል። ህንድና ቻይና አገራትም በአካል በመሄድ መስተካከል ያለባቸውን ነገሮች ለማስተካከል ጥረት አድርጓል። ከኢትዮጵያ የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን ጋርም ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ሥራ እየሠራ ነው።**

ህንድና ቻይና አገራትም በአካል በመሄድ መስተካከል ያለባቸውን ነገሮች ለማስተካከል ጥረት አድርጓል። ከኢትዮጵያ የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን ጋርም ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ሥራ እየሠራ ነው። በዚህም፣ ብዙ አቅራቢዎች በመመዝገብ ላይ ስለሆኑ፣በዚህ ዓመት የተሻለ ለውጥ ይኖራል የሚል ተስፋ አለ። በጣም ውስን አቅራቢ ያላቸው የካንሰር፣ የኩላሊት ንቅለ ተከላ፣ የልብ መድሃኒቶች አገር ውስጥ ስለማይመረቱ፣ አቅራቢዎቻቸውም በጣም ጥቂት በመሆናቸው፣ ውል ይዞ የማቋረጥ ፈተናዎች ያጋጥማሉ። ለዚህ መፍትሔ የሚሆን ሥርዓት እየዘረጋን ነው ያሉት አቶ ሰሎሞን፣ ቀዳሚው ተግባር ከአቅራቢዎች ጋር ተቀራረቦና ተቀናጅቶ መስራት ሲሆን፣ ሌላኛው የማዕቀፍ ግዢ ስርዓት መዘርጋት ነው። በዚህ ሥርዓት አቅራቢዎች አንድ ጊዜ ተወዳድረው እስከ ሶስት ዓመት መድሃኒት ማቅረብ የሚችሉበት ሥርዓት ተዘርግቷል። በዚህም ከባድ የአቅርቦት መቆራረጥ የነበረባቸው መድሀኒቶች ላይ የመጣው ለውጥ በጠንካራ ጎን የሚታይ ነው።

ቀደም ሲል በነበረው የበጀት እጥረት ከመድሃኒት አለመገኘት ጋር ተያይዞ ትልቅ ክፍተት እንደነበረ የተናገሩት አቶ አበራም፣ በዚህ ዓመት የውስጥ ገቢን በማጠናከር የፋርማሲውን መድሃኒት የማቅረብ አቅም የተሻለ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል። አቶ ደበላም፣ የሆስፒታሉ የመድሃኒት አቅርቦትን ለማሳደግ ከሚሰሩ ስራዎች በተጨማሪ፣ በተለይም በቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን በመተግበር መድሃኒቶች ሲጠፉ፣ ከሌሎች ሆስፒታሎች፣ ጤና ተቋማትና በሆስፒታሉ ውስጥ ካሉ ፋርማሲዎች መድሃኒቱ ወደ ተፈለገበት ቦታ እንዲመጣ ማድረግ ተችሏል። በዚህም ታካሚዎች መድሃኒት ፈልገው እንዳያጡ በተደረገው ሥራ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት እንደተቻለ አስረድተዋል።

## ተቋሙ ማቅረብ ያልቻላቸው መድሃኒቶች አሉ ወይ?

አገልግሎቱ ማቅረብ ያልቻላቸው መድሃኒቶች አሉ ወይም የሉም ስንል ተቋሙ የሚያቀርበው ምንድነው የሚለውን ማወቅ ያስፈልጋል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ አገልግሎቱ 262 መድሃኒቶች፣ 151 የህክምና መገልገያዎችና ሌሎች ኬሚካሎች በአጠቃላይ 1ሺህ 20 ዝርዝሮችን እንደሚያቀርብ አንስተው፣ ይህ ዝርዝር ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በየሁለት ዓመቱ የሚከለስ፣በሂደቱ ደግሞ ቁጥሩ ሊቀንስም ሆነ ሊጨምር እንደሚችል ይጠቁማሉ። በመሆኑም የሉም ተብለው የሚነሱ መድሃኒቶች በተቋሙ የአቅርቦት ዝርዝር የማይታቀፉ ብራንድ መድሃኒቶች ናቸውም ብለዋል። አቶ ደበላ ደግሞ፣ አገልግሎቱ ለሁሉም ጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች ተመሳሳይ መድሃኒቶችን እንደሚያሰራጭ ጠቅሰው፣ ስርጭቱ የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የሚሰጠውን ዘርፈ ብዙ የህክምና አገልግሎት ታሳቢ ያደረገ አይደለም ይላሉ። ሆስፒታሉ ለግዢ የሚያቀርባቸው 1 ሺህ 400 መድሃኒቶች፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችና ኬሚካሎች ሲሆኑ፣ ከእነዚህ ውስጥ 360ዎቹ መድሃኒቶች ናቸው። በመሆኑም ከላይ እንደተገለጸው ከአገልግሎቱ ማግኘት ያልቻላቸውን ከግል አቅራቢዎች በመግዛት ታካሚዎች ከሚፈልጓቸው መድሃኒቶች መካከል 70 ከመቶ በላይ የሚሆኑትን በሆስፒታሉ በሚገኙ 12 ፋርማሲዎች ውስጥ እንዲያገኙ ማድረግ ችሏል። አቶ ተፈራም በተመሳሳይ ሁኔታ አማኑኤል ሆስፒታል ለሚሰጠው የህክምና አገልግሎት የሚጠቅሙ፣በተለይም የሚጥል በሽታ/Epilepsy/ መድሃኒቶችን ማግኘት ከባድ እንደሆነ ተናግረዋል።

## የአገልግሎት ጊዜያቸው የሚያልፉ መድሃኒቶች

ከመድሃኒት ጋር ተያይዞ ብክነት አንዱ ፈተና እንደሆነ ዳይሬክተሩ ያስረዳሉ፣ በተቻለ መጠን የመድሃኒት ብክነትን ለመቀነስ አገልግሎቱ ጥረት እንደሚያደርግም ይጠቁማሉ። እርሳቸው እንደገለጹት፣ አገልግሎቱ መድሃኒቶችን ሲገዛ ከሚከተላቸው የግድ ከሚባሉ መስፈርቶች ቀዳሚው አቅራቢው የጥራት ማረጋገጫ አለው ወይ የሚለው ሲሆን፣ ሁለተኛው

እንደየመድሃኒቱ ባህርይ ከተመረተበት ጊዜ አንጻር 80 ከመቶ እድሜ ያለው መሆኑ ነው። እነዚህን መስፈርቶች አሟልቶ አነስተኛ ዋጋ የሰጠ አቅራቢ መድሃኒቶችን እንዲያቀርብ ይደረጋል። በዚህም የመድሃኒቱ የአገልግሎት ዘመን የሚያልፍበት ሁኔታ አይፈጠርም። ነገር ግን በተለያየ ምክንያት፣ ለምሳሌ፡- አቅራቢ የሌላቸውን መድሃኒቶች በመጠን ከፍ ተደርጎ ተገዝቶ፣ ጤና ተቋማት ሳይጠቀሙበት ሲቀሩ ጊዜው የሚያልፍበት መድሃኒት ሊኖር ይችላል። በሌላ መንገድ፣ተቋሙ ከሚገዛቸው መድሃኒቶች መካከል 2 በመቶኛው የአገልግሎት ዘመናቸው ሊያልፍ ይችላል በሚል የተቀመጠ መስፈርት መኖሩን ዳይሬክተሩ ይጠቅሳሉ። አያይዘውም፣ አገልግሎቱ ባለፈው ዓመት ከገዛቸው መድሃኒቶች መካከል 0.74ቱ የአገልግሎት ጊዜያቸው ማለፉን አንስተዋል። "ነገር ግን የዓለም ጤና ድርጅት ያስቀመጠውን መስፈርት ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ፣ አገራዊ ምልከታን መነሻ ያደረገ ምላሽ ለመስጠት ተቋሞች ያሉበትን ሁኔታ ማወቅ ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም መድሃኒቶቹ አገልግሎቱ ላይ እያሉ የአገልግሎት ዘመናቸው ገና ሆኖ፣ በጤና ተቋማት በሚኖራቸው ቆይታ ግን ጊዜያቸው ሊያልፍ ይችላል" ብለዋል።

ጊዜው ያለፈበት መድሃኒት በምንም ሁኔታ ወደ ጤና ተቋማት አይሰራጭም ያሉት ዳይሬክተሩ፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው የደረሱ መድሃኒቶችም እኛ ጋር ከሚበላሹ ጤና ተቋማት ሄደው ይበላሹ የሚል አቋምም የለንም ብለዋል። እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፣ ተቋሙ ላይ መድሃኒት በብዛት ተከማችቶ የአገልግሎት ጊዜው ሊያልፍ ሲል በመነጋገር የግሉ ዘርፍ በፍላጎት እጨርሳለሁ ብሎ ያመነበትን ያህል ግዢ እንዲፈጽም፤ የመንግሥት የጤና ተቋማትም በየሁለት ወሩ ይወስዱ የነበረውን መድሃኒት የአራት ወር እንዲሰጣቸው ይደረጋል፤ ይሁን እንጂ ያለ ጤና ተቋማቱ ፍላጎት የሚሰራጭ መድሃኒት ግን የለም።

አቶ ደበላ በበኩላቸው እንደተናገሩት፣ መድሃኒቶች የሚገዙት ተጠቃሚውንና የበሽታውን ባህሪ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ግምት ደግሞ ምንጊዜም ትክክል አይመጣም። በዚህ ምክንያት የመድሃኒቶች የአገልግሎት ጊዜ ሊያልፍ ይችላል። ለምሳሌ፡- ባለፉት ዓመታት የኮቪድ ህመምተኞችን ለማከም የተገዙ መድሃኒቶች፣ በሽታው በእጅጉ በመቀነሱና ተጠቃሚ ስለሌለው በብዛት የአገልግሎት ጊዜያቸው እያለፈባቸው ይገኛሉ። "ሌሎች፣ በብዛት የአገልግሎት ጊዜያቸው የሚልፍባቸው መድሃቶች ደግሞ እንደ ኤች አይ ቪ የመሳሰሉ የፕሮግራም መድሃኒቶች ሲሆኑ፣ እነዚህ መድሃኒቶች በበጀት ሳይሆን በዓለም አቀፍ ድጋፍ የሚገኙ ናቸው፤ ወደ ጤና ተቋማት በብዛት ስለሚገቡም ሳያልቁ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያልፋል፤ ተጠቅመንም ለሌሎች አካፋፍለንም የተረፉና የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፉ ባለፉት

**"የአገር ውስጥ አቅራቢዎች ላቀረቡት መድሃኒት ያሸነፉበትን 50 ከመቶ ክፍያ በዶላር እንዲያገኙ ለማስቻል እየሰራ ይገኛል"**

አራት አመታት የገቡ 18 ሚሊየን ብር የሚገመት መድሃኒት አቃጥለናል" ያሉት የፋርማሲ ዳይሬክተሩ፣ ከመድሃኒት አቅራቢ አገልግሎትና ከግል አቅራቢዎች በበጀት ከተገዙ መድሃኒቶች መካከል አንድም መድሃኒት የአገልግሎት ዘመኑ ያለፈ የለም ብለዋል። የአገልግሎት ዘመናቸው የሚያልፉ መድሃኒቶችም ከጠቅላላው ከሚገዙ መድሃኒቶች አንጻር ያለው ምጣኔ የዓለም ጤና ድርጅት ካስቀመጠው መስፈርት ያነሰ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ አቶ አበራ ገለጻ ደግሞ፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው ቅርብ የሆኑ መድሃኒቶች አይገዙም። አማራጭ ከጠፋ ግን በጣም አስፈላጊ የሆኑ መድሃኒቶች በጥቂት መጠን እንዲገዙ ይደረጋል። እነዚህ ጥረቶች ተደርገው ግን ባለፈው ዓመት የፕሮግራም መድሃኒቶችን ጨምሮ በአጠቃላይ 70 ሺህ ብር የሚገመት መድሃኒት የአገልግሎት ጊዜው ሊያልፍ ችሏል።

መድሃኒት አቅራቢ አገልግሎቱ ጤና ተቋማት መድሃኒቶችን ያለፍላጎታቸው እንዲገዙ ያስገድዳል ወይ ለሚለው ጥያቄ አቶ አበራ፣ "የፕሮግራም መድሃኒቶችን ከፍላጎት ውጪ እንድንገዛ ቀላቅሎ ይልካል" የሚል ምላሽ ሲሰጡ፣ አቶ ደበላ ደግሞ "ሙሉ በሙሉ ያስገድዳል፣ ሙሉ በሙሉ አያስገድድም ለማለት ይከብዳል በማለት፣ "ተቋሙ የአገልግሎት ጊዜያቸው የደረሰ መድሃኒቶችን ትፈልጋለህ ወይስ አትፈልግም ብሎ ጥያቄ ሲያቀርብ ለስድስትና ለሶስት ወር የሚጠቀምበት ታካሚ ሊኖር ይችላል በሚል እንደ ጤና ተቋም አንፈልግም ብለን አንጨክንም ስለሆነም መድሃኒቶቹን የሚጠቀመው ይጠቀምና ሌላው ጊዜው የሚያልፍበት ይሆናል" በማለት ያስረዳሉ።

## በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ

የአገር ውስጥ መድሃኒት ድርሻ ከ10 ከመቶ በታች ቢሆንም፣ ከመንግሥት በኩል ግን ትኩረት የተሰጠው በኢንደስትሪ ፓርክም እንዲደራጅ የተደረገ ዘርፍ መሆኑን ያነሱት አቶ ሰሎሞን፣ የመድሃኒት ምርት ትልቁ ችግር የዶላር አቅርቦት እጥረት እንደሆነ ይጠቅሳሉ። እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፣ የአገር ውስጥ ምርት አቅርቦትን ለመጨመር በዶላር በኩል ያለው ችግር በመመሪያ ጭምር እንዲፈታ አገልግሎቱ ከመንግሥት ግዢ ባለስልጣን፣ ከፋይናንስ ሚኒስቴርና ብሔራዊ ባንክ ጋር በመነጋገር የአገር ውስጥ አቅራቢዎች ላቀረቡት መድሃኒት ያሸነፉበትን 50 ከመቶ ዋጋ በብር፣ 50 ከመቶ የሚሆነውን ክፍያ ደግሞ በዶላር እንዲያገኙ ለማስቻል እየሰራ ይገኛል። ይህም፣ መድሃኒት በአገር ውስጥ ቢመረትም ጥሬ እቃው ከውጪ የሚገባ በመሆኑ የአገር ውስጥ አምራቾች ጥሬ እቃ የሚያመጡበትን ዶላር እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። በአሰራሩ ላይ ሁሉም አካላት መግባባት ላይ የደረሱ ሲሆን፣መመሪያውን ለማጽደቅ ደግሞ በሂደት ላይ ይገኛል።

አቶ አበራም፣ መድሃኒት አቅራቢ ድርጅቶች በባንኮች በኩል ዶላር ቅድሚያ እንዲያገኙ ቢመቻችላቸውና ለአገር ውስጥ አምራቾችም ፋብሪካዎችን በማደረጀት ምቹ ሁኔታ ቢፈጠርላቸው በመድሃኒት አቅርቦት በኩል የሚታየውን ችግር መፍታት ይቻላል የሚል አስተያየት አላቸው። በተጨማሪም መድሃኒቶች አገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ፍጆታን መሠረት ባደረገ መልኩ ስርጭት እንዲደረግ የጤና ተቋማት ከመድሃኒት አቅራቢ አገልግሎት ጋር ተናበው ቢሰሩ ክምችትና እጥረት ያለባቸውን የጤና ተቋማት በተገቢው መንገድ ለማስተዳደር መልካም ዕድል ይፈጥራል የሚል ሐሳብም ሰንዝረዋል።

አቶ ደበላ ደግሞ፣ አቶ ሰሎሞንና አቶ ተፈራ እንደገለጹት ሁሉ የዶላር እጥረት ጉዳይ ለመድሃኒት አቅርቦት ማጠር አንዱ መንስዔ እንደሆነና ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ መሆኑን ይናገራሉ። የመድሃኒት አቅራቢ አገልግሎት አገር ውስጥ ለሚገኙ የጤና ተቋማት ሁሉ መድሃኒትና የህክምና መገልገያ መሳሪያ ለማቅረብ አቅም እንደሚያጠረው በማንሳት፣ ተጨማሪ ጠንካራ የአገር ውስጥ አስመጪ ማቋቋም እንደሚያስፈልግም ያሳስባሉ። የግዢ ባህሪና የበጀት ፖሊሲም ከመድሃኒት ባህሪይ ጋር የተናበቡ ሊሆኑ ይገባል የሚሉት አቶ ደበላ፣ ፖሊሲ አውጪዎች ለጉዳዩ ትኩረት ቢሰጡት የተሻለ እንደሚሆን ጠቁመዋል። የጤና ተቋማት መድሃኒቶቻቸውን ሸጠው በሚያገኙት ገቢ መልሰው የሚያስፈልጋቸውን መድሃኒት የሚገዙበትና ጥቂት ትርፍ ጨምረው በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው የሚያቀረቡበት አሰራር ቢዘረጋ ለመድሃኒት አቅርቦት ችግር መፍትሔ ሊያመጣ ይችላል የሚል አስተያየትም ሰጥተዋል።

# ፀሐይና
# ምድራዊ ኩነቶች



ሽብሩ ተድላ (ፕሮፌሰር ኤሜሪተስ)




አታላይ አየለ (ፕሮፌሰር)

## መግቢያ

ፀሐይን በየቀኑ ስለምናያት ስለ እሷ በቂ መረጃ እንዲኖረን ያስፈልጋል የሚል እሳቤ አለን። ፀሐይ የተለያዩ ምድራዊ ተግባራትም አስተናጋጅ፣ ብሎም የኩነቶች መተለሚያ፣ መለኪያ ሆና ታገለግላለች። የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ሳይንስን ማኽዘብ (የሳይንስን ዘዴ እና ዕውቀት ለሕዝብ እንዲዳረስ ማድረግ) ሲሆን፣ እሳቤው የሚስተናገደው ስለ ፀሐይ እና ምድር ቁርኝት ትንተና በማቅረብ ነው። ሁላችንም ስለፀሐይ የተወሰነ ግንዛቤ አለን፣ ልዩነቱ ግን የግንዛቤው ጥልቀት እና ስፋት ላይ ነው። ፀሐይ የብርሃን እና የሙቀት ምንጭ፣ የጊዜ ልኬት መንስዔ መሆኗን ሁላችንም እናውቃለን። እንዲሁም የዘመን ክፍፍል (በጋ፣ በልግ፣ ክረምት፣ ፀደይ) ከፀሐይ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው እንገነዘባለን። በቂ ግንዛቤ የሌለን ስለ አመሠራረቷ እና ስለ ልዩ ባህሪያቷ ነው። ስለ ፀሐይ ያለን ግንዛቤ በዳበረ መጠን፣ በመሬት ዙሪያ ላለው ቁስ አካል፣ እንቅስቃሴ፣ የተሻለ ግንዛቤ እንድናዳብር ይረዳናል።

ፀሐይ የሰው ልጆችን ቀልብ ስባ፣ ከቁሳዊነት ዘልቃ መለኮታዊ ባህርይ እንዳላትም በብዙ አካባቢ ይታመን ነበር፣ አሁንም ቢሆን በተወሰኑ አካባቢዎች ያንን ዓይነት እምነት ያነገቡ አይጠፉም። ለምሳሌ፡- በጥንታዊ ግብጻውያን እምነት “ሬ” (Re)፣ ማለት ፀሐይ፣ የመላእክት የበላይ አካል ነበር፣ እንደ አለቃ ማለት ነው። እንዲሁም በግሪክ አካባቢ “ታይታን” (Titan) መለኮታዊ ፀሐይ ሆኖ ይታይ ነበር። እሱም “የፀሐይ ሰረገላ” በየቀኑ ከምሥራቅ ጀምሮ ወደ ምዕራብ እንደሚጋልብ ይታመን ነበር። ተመሳሳይ እምነቶች፣ በአፍሪካ፣ በደቡብ አሜሪካ፣ በሩቅ ምሥራቅ እና በአውስትራሊያም ነበሩ። በተጨማሪ ከሳምንት ቀናት “ሰንደይ” (Sunday/ Sun Day) እና “መንደይ” (Monday/Moon Day) ተብለው፣ ለፀሐይ እና ለጨረቃ፣ አንዳንድ ቀን በስማቸው ተሰይመውላቸዋል።

ፀሐይ በባህላችን በበጎ ሁኔታ ትመሰላለች፣ “እገሌ እኮ ፀሐይ ወጣለት” ሲባል፣ ቀንቶታል፣ የፈለገውን አገኘ እንደማለት ነው።”እነሱማ ጨለመባቸው” ሲባል ደግሞ፣ ጊዜ ከድታቸዋለች፣ አልተመቻቸውም እንደማለት ይቆጠራል። ሌሎች




**ለፀሐይ ቅርብ ከሆነችው ፈለክ ጀምረን እየራቁ የሚሄዱት በቅደም ተከተል፣ ሜርኩሪ (Mercury)፣ ቪነስ (Venus)፣ ምድር፣ ማርስ (Mars)፣ ጁፒተር (Jupiter)፣ ሳተርን (Saturn) ፣ ዩራነስ (Uranus) እና ኔፕቱን (Neptune)።**


> ፀሐይ የተመሠረተችው ከ4.568 ቢሊዮን ዓመታት በፊት ሲሆን፣ ያም የዩኒቨርስ ሲሶ እድሜ ማለት ነው። ”

ከፀሐይ ጋር የተዛመዱ አባባሎችንም ማንሳት ይቻላል።

### የፀሐይ እና የምድር አመሠራረት

ፀሐይ ከመጠነ ብዙ “ሃይድርጅን” (hydrogen/ H) እና “ሂልየም” (helium/ He) ክምችት የተገነባች “የጋዛዊ አለሎ እሳት” ናት። የፀሐይ የውጭ ገላዋ ሙቀት አምስት ሺ አምስት መቶ ዲግሪ ሴልሲየስ (5,500 $^{0}$C) ገደማ ሲሆን፣ የውስጥ ሙቀቷ አሥራ አምስት ሺ አምስት መቶ ዲግሪ ሴልሲየስ (15,500 $^{0}$C) ገደማ ነው።

ፀሐይ የተመሠረተችው ከ4.568 ቢሊዮን ዓመታት በፊት ሲሆን፣ ያም የዩኒቨርስ ሲሶ እድሜ ማለት ነው። “ሥርዓተ-ፀሐይ” (Solar System) የተመሠረተው በዚያው ወቅት ነው። ፈለኮቹ (Planets)፣ እንዲሁም ሌሎች የሥርዓቱ



አባላት ከአንድ ግዙፍ የብርሃን ደመና እንደተገኙ ይገምታል። እሱም ድብዝ ስብስብ ከዋክብት ("ኔቡላ"/ Nebula) ፣ሲባል ከደመናው እምብርት ፀሐይ ታነፀች፣ ፈለኮች (Planets) ከውጭ ካለው ስብስብ ተመሠረቱ። ከበድ ከበድ ያሉት ፈለኮች፣ ለፀሐይ ጠጋ ብለው፣ ይዘታቸው ቀለል ቀለል ያሉት ደግሞ ራቅ ብለው፣ የየራሳቸውን ኳስ መሰል አካላት መሥርተው ፀሐይን መዞር ጀመሩ። ይህ ስብስብ ነው "ሥርዓተ-ፀሐይ" (Solar System) በመባል የሚታወቀው።

"የሥርዓተ-ፀሐይ" (Solar System) አስኳል ፀሐይ ስትሆን፣ ስምንት ፈለኮች በተለያዩ ርቀቶች ፀሐይን ይዞራሉ። በተጨማሪም ሌሎች መጠነ ውስን የሆኑ ፈለኮች፣ እንዲሁም ኮሜቶች (Comets)፣ አስቴሮይድስ (Asteroids)፣ ወፈጥ ድንጋይ (Space rocks) እና ጠጣር በረዶ መሰል አካላት (Space ice) ይገኛሉ። የፈለኮችን ቁጥር ወደ ዘጠኝ አንዳንዶች ደግሞ ወደ አሥራ አንድ ከፍ የሚያደርጉ ጠበብትም አሉ።

በሰማየ ሰማያት ላይ ሌሊት የምናያቸው አንፀባራቂ አካላት ሁሉ ከዋክብት ሲሆኑ፣ የኛ ፀሐይ የምትገኝበት "ጋላክሲ" በ"ፍኖተ ሃሊብ" (Milky Way) የሚገኙ ሌሎች ፀሐዮች አሉ። እነሱም እያንዳንዳቸው የየግላቸው ሥርዓትን የመሠረቱ ግዙፍ አካላት ናቸው። ዩኒቨርስ ብዙ ቢሊዮን ጋላክሲዎችን ያቀፈ፣ በእያንዳንዱ ጋላክሲም ብዙ ቢሊዮን ፀሐዮች የሰፈሩበት፣ ልክየለሽ ክስትት ነው።

ከሌሎቹ "የፀሐይ ሥርዓት" አባላት ጋር ስትነፃፀር፣ ፀሐይ መጠኗ በጣም ግዙፍ ነው። ጠቅላላ ሥርዓቱ ከተገነባበት መጠነ ቁስ (mass)፣ ዘጠና ዘጠኝ ነጥብ ስምንት በመቶ (99.8%) የሆነው የፀሐይ ድርሻ ነው፡ ቀሪውን ውስን መጠነ ቁስ ነው ሌሎች አካላት የሚካፈሉት። በተለይ ወደ ፀሐይ ጠጋ ያሉት የምድራዊ ፈለኮች መጠነ ቁስ ድርሻ በጣም ዝቅተኛ ነው።

ፈለኮች በፀሐይ "ማህለሸሽ ኃይል" (Centrifugal Force) ተወንጭፈው፣ ተስፈንጥረው እንዳይርቁ፣ "በስበ ቁስ" (ግራቪቲ/ Gravity) ተወጥረው ይያዛሉ። ከፀሐይ ቅርብ ከሆነችው ፈለክ ጀመረን ራቅ ራቅ ብለው ወደሚገኙት ፈለኮች በተራ፣ በቅደም ተከተል፣ "ሜርኩሪ" (Mercury)፣ "ቪነስ" (Venus)፣ ምድር (Earth)፣ "ማርስ" (Mars)፣"ጁፒተር"(Jupiter)፣ "ሳተርን"(Saturn)፣ "ዩራነስ" (Uranus) እና "ኔፕቱን" (Neptune) ናቸው። የሥርዓተ-ፀሐይ አባላት የሆኑ፣ ቁጥራቸው የማይታወቅ ብዙ ጥቃቅን ፈለኮች እንዳሉ ይገመታል።

ከፀሐይ ቅርበት ያሉዋቸው ከባድ ከባዶች አራቱ ፈለኮች፣ "ሜርኩሪ፣" "ቪነስ"፣ ምድር፣ እና "ማርስ" "ምድራዊ/ የብሳዊ ፈለኮች" (Terrestrial Planets) ይባላሉ። እነሱም የተገነቡት ከድንጋይ

ከመሬት ተነስተን ወደ ላይ ወደ ሕዋ ብንዘልቅ፣ ርቀቱ በጨመረ መጠን፣ የአየር ግፊቱ ይቀንሳል። ከመሬት ገጽ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት/ ከፍታ ላይ፣ የአካባቢው አየር መጠን ሳስቶ አየር አልባ እንደሆነ፣ ብሎም የአየር ግፊት እንደሌለ ሊቆጠር ይችላል፤

እና ከብረት አስተኔዎች (Metals) ሲሆን፣ ከፀሐይ ራቅ ብለው የሚገኙት ሁለቱ ታላላቅ ፈለኮች፣ "ጁፒተር" እና "ሳተርን"፣ "ከሃይድሮጅን" (hydrogen/ H) እና "ከሂልየም" (helium/ He) ነው የታነፁት። ከዚያም ራቅ ብለው የሚገኙት ሁለት ፈለኮች፣ "ዩራነስ" እና "ኔፕቱን" ትናኝ በረዶ መሰል አካል ነው ያላቸው። ሁሉም ፈለኮች ፀሐይን ይዞራሉ። የዙረታቸው አቅጣጫ፣ የራሷ የፀሐይ ሹረት አቅጣጫ ነው። ይህን ዙረት ከሰሜን ዋልታ ላይ ሆነን ስንመለከተው፣ የሰዓት ዙረት ተቃራኒ (anticlockwise) ነው።

"ከየብሳዊ ፈለኮች" (Terrestrial Planets) ምድር ብቻ ናት አጃቢ ጨረቃ ያላት። መሬት ገና ሕፃን በነበረችበት ዘመን፣ ከአንድ ግዙፍ አካል ጋር ተጋጭታ፣ በግጭቱ መንስዔ ጨረቃ ተመሠርታ፣ የምድር አጃቢ ሆነች ተብሎ ይገመታል። ጨረቃ የሰውን ልጅ ቀልብ ከሚስቡት፣ ከምድር ውጭ ከሆኑ ግዙፍ አካላት አንዷ ስትሆን፣ በአንዳንድ የባህል ዘመን መተለሚያ ተደርጋ ተወስዳለች። ጨረቃ የሰው ልጅ ጎረቤት ስለሆነች፣ ጉርብትናውን ለማጠናከር፣ እሷን መጎብኘት እንደ አንድ ትልቅ የሳይንስ መርሃ ግብር ተደርጎ ከተወሰደ ዘመናት ተቆጥረዋል። ከምድር የተላከ ቁስ አካል (የሳይንስ መሣሪያ) በጨረቃ ላይ በመጀመሪያ ጊዜ ያረፈው በሶቭየት ሕብረት ተልኮ በግሪጎርያን ዘመን አቆጣጠር፣ "በሴፕቴምበር" 13 1959 ነበር። ከዚያም ከአስር ዓመት በኋላ "በጁላይ" 1969 አሜሪካ በጨረቃ ላይ ሰው ለማሳረፍ ቻለች፣ እንዲሁም በተከታታይ አሜሪካ ለስድስት ጊዜ ሰዎችን ጨረቃ ላይ ለማሳረፍ በቅታለች።

> ፀሐይ ውበትም አስተናጋጅ ናት። የሰው ልጆች ለማየት የሚችሉት ብርሃን (visible light) የተለያዩ ርዝመት (wave length) ያሉዋቸው (spectrum of wavelengths) የብርሃን ሞገዶች ጥምረት ሲሆን፣ ይህ ብርሃን በውሃ ጠብታ ውስጥ ሲያልፍ፣ ጥምረቱ ይበተንና በተለያዩ ቀለማት ያሸበረቀ ቀስተ ደመና ለማየት እንችላለን።

ሕያው አካላትን የምታስተናግድ የየብሳዊ ፈለኮች አባል የሆነችው ምድር ብቻ ናት፣ ምክንያቱም "ከበበ ውሃ" (Hydrosphere) በምድር ዙሪያ ብቻ ነው የሚገኘው። ይህም ሁኔታ ምድርን ከሌሎች ጓዶቿ ለየት ያደርጋታል። ኬሚካዊ ውሁድ ያለሆነ ነፃ ኦክስጅን ($O_2$) የሚገኝ ምድር ላይ ብቻ ነው። ምድር ይህንን ልዩ ተፈጥሮ ያገኘችው ከፀሐይ የምትገኝበት የርቀት መጠን ለህያው ፍጡር የተመጣጠነ የሙቀት መጠን ማግኘት የሚያስችል በመሆኑ ነው።

ምድር ስትመሠረት የጋለ ብርት አለሎ መሰል የነበረች ቢሆንም፣ በሂደት የገላዋ የላዩ ሽፋን ቀዝቅዞ፣ ውሃ እንዲጠራቀምበት አስቻለ፣ በሂደት ውቅያኖሶች ተመሠረቱ። ሕይወት በመጀመሪያ የተከሰተው በውቅያኖስ ውስጥ እንደሆነ ብዙ መረጃ ተገኝቷል። የምድር ዘመን በሦስት ግዙፍ የዘመን ክፍሎች ይከፋፈላል። አንደኛው "ዘመነ ጥንተ ሕይወት" ("ፓሊዮዞይክ"/ Paleozoic) ሲባል፣ አከርካሪ የሌላቸው (አከርካሪ አልባ/ የጀርባ አጥንት የሌላቸው) እና በመጀመሪያ ባለአከርካሪ የሆኑት የአሳ ዝርያዎች ዘመን ነው። ከዚያ ቀጥሎ ያለው ማእቀፍ፣ "ዘመነ ማዕከለ ሕይወት" ("ሜሶዞይክ"/ Mesozoic) ሲባል፣ ያም የዳይኖሶሮች ዘመን ነበር። የመጨረሻው እና ሦስተኛው ማእቀፍ "ዘመነ ቅርስ ሕይወት" ("ሴኖዞይክ"/ Cenozoic) በመባል ይታወቃል። ያም "አካለ ሰው"፣ የሰው ዘር መሰል የሕያው ሐረግ (ቅርንጫፍ) መታየት የጀመረበት ሲሆን፣ ጊዜውም ከሁለት ሚሊዮን ዓመታት በፊት ገደማ እንደሆነ ይገመታል። "ቅድመ ሰዎች"፣ እንደ ድንቅነሽ ያሉት፣ ከሦስት ሚሊዮን ዓመታት ገደማ በፊት ነበር ምድር ላይ የታዩት።

በፀሐይ ኃይል ታግዘው የራሳቸውን ምግብ የሚያመርቱት እፅዋት፣ በምድር ላይ መታየት የጀመሩት ከሦስት ቢሊዮን ዓመታት ገደማ በፊት እነሱን መሰል ሕያው አካላት በምድር ማንሰራራት በሕዋ ውስጥ የሚገኘውን ኦክሲጅን መጠን በጣም ከፍ አደረገው፣ የዚያም ኩነት ምክንያት እፅዋት "ካርቦን ዳይከሳይድ" ($CO_2$) ምገው ኦክሲጅን ($O_2$) ስለሚተፉ ነው።

### ፀሐይ፣ የኢነርጂ ምንጭ

ከላይ እንደተጠቀሰው የእኛ ፀሐይ፣ "የሥርዓተ ፀሐይ" (Solar system) አስኳል (እምብርት) ስትሆን፣ እሷም ለሥርዓተ-ፀሐይ ብቸኛ የኢነርጂ ቋት ናት። የፀሐይ ኢነርጂ የሚገኘው "ኑክሊየር እርስሰት" (Nuclear fusion) በመባል የሚታወቅ የኑክሊየር ኃይል ማመንጫ ሂደት ነው። በከፍተኛ ግፊት (pressure) እንዲሁም ሙቀት ሃይድሮጅንን (hydrogen/ H) ወደ ሂልየም (helium/ He) ሲቀየር (ሁለት የሃይድሮጅን አቶሞች አንድ ሂልየም አቶም ይገነባሉ)። በዚህ ሂደት የተገኘ ከፍተኛ የሆነ ኢነርጂ ይገኛል።

ፀሐይ በየቀኑ የምታመነጨው ኢነርጂ፣ በምድራችን ያሉ ኩነቶች ሁሉ በዓመት ከሚጠቀሙበት ኢነርጂ በጣም የላቀ ነው። ከፀሐይ የሚፈልቀው ኢነርጂ (ብርሃን እና ሙቀት) ሶስት መቶ ሺ ኪሎ ሜትር በሰኮንድ እየተጓዘ፣ አንድ መቶ አምሳ ሚሊዮን ኪሎ ሜትርን አቋርጦ፣ ከስምንት ደቂቃ ገደማ በኋላ ምድር ላይ ይደርሳል።

ከፀሐይ በብርሃን ነፀብራቅ (Solar radiation) እና ሙቀት በሚመነጭ ጉልበት ("ሶላር ኢነርጂ" / Solar Energy) የሰው ልጆች መጠቀም ከጀመሩ ዘመናትን አስቆጥረዋል። በፀሐይ ኢነርጂ ቀጥታውን ተጠቅሞ የውሃን እና የቤት አካባቢ አየር ሙቀት ከፍ ለማድረግ ይቻላል። በተዘዋዋሪ መንገድ ፀሐይ ከምታስተናግዳቸው ነፋስ እና የባህር ሞገድ የሚገኝ "ሜካኒካል ጉልበት" (mechanical energy) የኤሌክትሪክ ኢነርጂ ማመንጨት ይቻላል።

በፀሐይ ኢነርጂ በመጠቀም (ሌሎችም የኢነርጂ ምንጮች ለዚህ ተግባር ሊውሉ ይችላሉ) የሃይድሮጂንን አቶም (H) ከውሃ "ሞሊኪውል" ($H_2O$) ነጥሎ በማውጣት እና ያንን ጋዝ ለሞተር ማንቀሳቀሻ ነዳጅ ማድረግ ይቻላል። "በሃይደሮጅን" ነዳጅ የሚንቀሳቀሱ መኪናዎች በሙከራ ደረጃ ፋብሪካ ላይ ይገኛሉ። ምንም እንኳ በሃይደሮጅን ነዳጅ መርከብ፣ አይሮፕላን፣ ወዘተ ማንቀሳቀስ የሚቻል ቢሆንም፣ በዘመናችን ከሃይድሮጅን በተገኘ ኢነርጂ፣ በብዛት፣ በቋሚነት፣ የምንጠቀም ለርኬቶች ማስወንጨፊያነት ነው። ከሃይድሮጅን በተገኘ ኢነርጂ ስንጠቀም፣ የነዳጁ ዝቃጭ የውሃ እንፋሎት (water vapour) ስለሆነ በካይ አይደለም። ይኸም ምድርን ከአስጊ ሁኔታ ሊታደጋት ይችላል። ከሃይደሮጂን በተገኘ ኢነርጂ የመጠቀሙ ተግባር ዋናው እንቅፋት፣ ነዳጁ በቀላሉ ለአደጋ በመጋለጡ፣ ፍንዳታ እና ቃጠሎ ማስከሰቱ ነው።

ፀሐይ የተየለሌ ኢነርጂ የምታፈልቅበትን መንገድ እንደምሳሌነት ተወስዶ፣ ያንን ዘዴ

በመከተል፣ ወይም በመኮረጅ፣ ሁለት የሃይደሮጅን ኑክሊየሶችን በመቀላቀል፣ “ኑክሊየር እርስሰት” በሚገኝ ኢነርጂ የኤሌክትሪክ ኢነርጂ ማመንጨት ሲሆን፣ ይህም ስኬታማ መሆኑ በሙከራ ተደርሶበታል። ይህን ሙከራ አዳብሮ ለቀን ተቀን ተግባር ለመጠቀም ዓመታት ይፈጃል፣ ሂደቱ ግን ተጀምሯል።

ፀሐይ ውብትም አስተናጋጅ ናት። የሰው ልጆች ለማየት የሚችሉት ብርሃን (visible light) የተለያዩ ርዝመት (wave length) ያሉዋቸው (spectrum of wavelengths) የብርሃን ሞገዶች ጥምረት ሲሆን፣ ይህ ብርሃን በውሃ ጠብታ ውስጥ ሲያልፍ፣ ጥምረቱ ይበተንና በተለያዩ ቀለማት ያሸበረቀ ቀስተ ደመና ለማየት እንችላለን። ይኸም ከተፈጥሮ አስደናቂ እና ውብ ስጦታዎች አንዱ ሲሆን፣ ያንን ውበት የምታበረክትልን ፀሐይ ናት።


## የምድራችን ከባቢ አየር (ሕዋ / Atmosphere)

የመሬት ቅርጽ ዱባ መሰል ሲሆን፣ ዙሪያዋን የሚሸፍን አየር እንዲሁም ብናኝ፣ ትናንሽ አካላት ይገኙሉ፣ ይህ ስብስብ ነው በጥቅሉ “ከባቢ አየር” (ሕዋ /Atmosphere) የሚባለው። ዋናዎቹ የከባቢ አየር አባላት ናይተሮጅን (Nitrogen/ $N_2$) ሰባ ስምንት በመቶ (78%) እና ኦክስጅን (Oxygen/ $O_2$) ሃያ አንድ በመቶ (21%) የሕዋ ድርሻ አላቸው። በሕያው ገላ ውስጥ እንደ እሳት አቀጣጣይ የሚቆጠረው ኦክስጅን ነው። ኦክስጅን ኢነርጂ በመጠቀም ሂደት ዋና ሚና አለው። ከዚያ በተጨማሪ አስጊ የሆኑ የፀሐይ ጨረሮች ምድር እንዳይደረሱ አንድ የኦክስጅን ዓይነት፣ “ኦዞን” (Ozone/ $O_3$)፣ እንደ መጋረጃ ሆኖ ያገለግላል።

በሕዋ ውስጥ ያለው “ካርቦን ዳይኦክሳይድ” ($CO_2$) የሕዋ አየር ድርሻ ዜሮ ነጥብ ዜሮ ሦስት በመቶ (0.03%) ብቻ ነው። በመሬት ዙሪያ ባለው አየር ውስጥ የሚገኘው ካርቦን በሁለት ኬሚካላዊ መዋቅር ይከፈላል፣ እነሱም “ሚቴን” (methane-CH4) እና “ካርቦን ዳይኦክሳይድ” (carbon dioxide/ $CO_2$) ናቸው። ሁለቱም ትናኝ (ጋዞች) ሲሆኑ፣ መሬት ላይ የደረሰው የፀሐይ ሙቀት በቀላሉ ተንፀባርቆ ወደ ሕዋ እንዳይመለስ፣ እንደመጋረጃ ሆነው ያገለግላሉ።

አንዱ አማቂ የጋዝ ዓይነት ኦዞን ($O_3$) ነው። በተጨማሪ “የኦዞን” ሽፋን ሕያውን ከአደገኛ “ልእለ ጨረር” (Ultraviolet radiation-UV) ከመጠቃት ይታደጋል። ጨረሩ በሰው ገላ ላይ ሲያርፍ የሰው ቆዳን ያቃጥላል፣ የቆዳ ካንሰር መንስዔም ይሆናል፣ እንዲሁም ዓይን ላይ ጉዳት ያደርሳል። በመሬት ዙሪያ የሚገኝ፣ “ማግነጢስ ሕዋ”(magnetosphere) በመባል የሚታወቅ ከጨረር መከላከያ ተጨማሪ ሌላ ኃይልም አለ።

መሬት ላይ የደረሰው የፀሐይ ሙቀት በቀላሉ ተንፀባርቆ ወደ ሕዋ እንዳይመለስ፣ እንደመጋረጃ




ካርቦን ዳይኦክሳይድን (CO2) በ“ብርሃን አስተፃምር“ (photosynthesis) ወደ ምግብነት ሲቀየር

ሆነው የሚያገለግሉ ጋዞች፣ “ዝገ ክበብ አየር” (Greenhouse effect) ተብሎ የሚታወቀውን ሁኔታ ይፈጥራሉ። የመሬት ከባቢ ሙቀት በአማካኝ 14 $^{0}$C ነው፣ “የሜቴን” እና “የካርቦን ዳይኦክሳይድ” (Carbon dioxide) መጋረጃ ባይኖር ኖሮ፣ ሙቀቱ በአማካኝ በሰላሳ አምስት ዲግሪ ሴልሺየስ (35 $^{0}$C) ዝቅ ይል ነበር። ይህም ማለት በአማካኝ የመሬት ሙቀት ከዜሮ በታች ሃያ አንድ ዲግሪ ሴልሲየስ (-21$^{0}$C) ሆኖ፣ ውቅያኖሶች በጠቅላላ ወደ ጠጣር በረዶነት ተቀይረው፣ በውስጣቸው ሕያው ነገር ሊኖሩ አይችሉም ነበር፣ ብሎም ምድር ሕይወት አልባ ፣ በጣም ውስን ሕያው አስተናጋጅ ትሆን ነበር።


ከቅርብ ዘመን ጀምሮ፣ የሕያው ቅሬት የሆነ፣ “ካርቦናዊ-ውሁድ” (organic compound) በነዳጅ መልክ፣ የሞተሮች ማንቀሳቀሻ ሲደረግ፣ ከርሰ-ምድር ውስጥ ታምቆ የነበረው ካርቦን፣ አየር ውስጥ ካለው ጋር መቀላቀል ችሏል። በዚህም ምክንያት አየር ውስጥ ያለው የካርቦን መጠን ናረ/ ከፍ አለ፤ ብሎም ለአየር-ቅጥ መለወጥ/ መናወጥ፣ ከዚያም ለምድር ከባቢ አየር ሙቀት መጨመር፣ ዋናው መንስዔ ሆኗል። ሙቀቱ የጨመረው “ዝገ ክበብ አየር” (Greenhouse effect) ተብሎ የሚታወቀው ሲሆን፣ የሙቀቱ ዋና ምንጭ ደግሞ ፀሐይ ናት።

የመሬት ሙቀት እንዳይንር የሚያግዙ የመሬት ሽፋኖችም አሉ፣ ያም የጠጠረ ውሃ (በረዶ/ሸኸት/ Ice) ነው። አልቢዶ (Albedo) የሚባለው ክስተት ምድር ላይ የሚደርስን የፀሐይ ብርሃን አንፀባርቆ ወደ ሕዋ ይመልሳል፣ ብሎም የአካባቢው የሙቀት መጠን እንዳይንር ያግዛል። በከፍተኛ ደረጃ የፀሐይን ብርሃን የማንፀባረቅ ባህርይ ሲኖራቸው፣ በበረዶ (ጠጣር ውሃ/ Ice) የተሸፈኑ አካባቢዎችም ናቸው።

እሳተ ገሞራ በሚፈነዳበት ጊዜ ወደ ሕዋ የሚተፋው አቧራ መሰል ብናኝ፣ የፀሐይ ብርሃን እና ሙቀት ወደ መሬት እንዳይደርስ ይጋርዳል፣ ብሎም ለአካባቢ መቀዝቀዝ ምክንያት ሆኖ ለወራት ሊቀጥል ይችላል። በተቃራኒው በጥቁር ቁስ የተሸፈኑ አካባቢዎች፣ ለአካባቢ ሙቀት መናር ምክንያት ይሆናሉ። ስለሆነም በጢስ ጥላሸት የተሸፈነ የበረዶ አካባቢ በቀላሉ በረዶ እንዲሟሟ ያደርጋል። የሟሟው በረዶ ውሃ ስለሚሆን፣ በዚህ መንገድ የተገኘ ውሃ የውቅያኖሶችን ገፅታ ከፍ ያደርገዋል፣ ባህር ዳር የሚገኙ ከተማዎችም በጎርፍ ይጥለቀለቃሉ።

## ፀሐይና በምድራችን ላይ ያሉ ግዙፍ ኩነቶች

በዓለማችን (በምድራችን) ላይ ላሉት ነባራዊ ሂደቶች በሙሉ፣ ለአየር ሙቀት፣ ለነፋስ አቅጣጫ ብሎም እንቅስቃሴ፣ ለውቅያኖስ ሙቀት፣ ለግዙፍ የውሃም ሆነ የአየር ማዕበል፣ ውሽንፍር፣ የፀሐይ እጅ አለበት። ጥቂቶቹን ኩነቶች በምሳሌነት




እናንሳ፡ -

**የአየር ግፊት (Air pressure)**

መሬት ላይ ሆነን ወደ ላይ ብንመለከት፣ የደመና ከለላ ከሌለ፣ ሰማያዊ ሰማይ ብቻ ነው የሚታየን። በሕዋ ውስጥ ያለውን አየር ለማየት ባንችልም፣ ከላያችን ያለው አየር ገላችንን ይጫነዋል። ጭነቱም በእያንዳንዷ ሴንቲሜትር ካሬ ያለው ክብደት አንድ ነጥብ ዜሮ ሦስት ሦስት (1.033) ኪሎ ግራም ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በመሬትም ላይ ያለው ጭነት (የአየር ግፊት/ Air pressure) ይኸው ክብደት ነው።

ከመሬት ተነስተን ወደ ላይ ወደ ሕዋ ብንዘልቅ፣ ርቀቱ በጨመረ መጠን፣ የአየር ግፊቱ ይቀንሳል። ከመሬት ገጽ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት/ ከፍታ ላይ፣ የአካባቢው አየር መጠን ሳስቶ አየር አልባ እንደሆነ፣ ብሎም የአየር ግፊት እንደሌለ ሊቆጠር ይችላል፤

በመሬት ላይ ያለው የአየር ግፊት በሙቀት መንስዔ ሊቀያየር ይችላል፣ ቀዝቃዛ አየር ከባድ ሲሆን፣ በአንፃሩ ሙቅ አየር ቀላል ነው። በቀዝቃዛ ሕዋ ውስጥ ሰብሰብ ብለው የሚገኙ የአየር ሞሌኩሎች፣ ሙቀት ሲያገኙ ይበታተናሉ። ሲበታተኑ በተወሰነ ቦታ ላይ ያለው የአየር ሞሌኩሎች፣ መጠን ቀንሶ ክብደቱም አብሮ ይቀንሳል። ቀዝቃዛ አየር ያለበት የከፍተኛ ግፊት አካባቢ (High pressure area) በመባል

> የምድር ሰሜን ዋልታ ከፀሐይ በሚርቅበት ወቅት፣ ከመሬት ሰቅ ሰሜን ያለው ቀዝቃዛ ወቅት፣ ከመሬት ሰቅ በታች ያለው የሙቀት ወቅት ይሆናል።

ሲታወቅ፣ በአንፃሩ ሙቅ አየር ያለበት አካባቢ የዝቅተኛ ግፊት አካባቢ (Low pressure area) በመባል ይታወቃሉ። የአየር ግፊት መለዋወጥ መንስዔ ሙቀት ሲሆን፣ የሙቀት ምክንያት ደግሞ ፀሐይ ናት።

በተወሰነ አካባቢ የአየር መታመቅም የአየር ግፊት መናር መንስዔ ይሆናል፣ በፊኛ ውስጥ አየር አምቀን ስናስገባ፣ የአየሩ ግፊት ፊኛውን ይወጥረዋል። ይህም የሆነው በውስን ቦታ ብዙ የአየር ሞሌኩሎች በማመቅ እና ዴንሲቲው (density) እንዲጨመር በመደረጉ ነው። ስለሆነም የዴንሲቲ መጨመርም የአየር ግፊት ንረትን ያስከትላል።

ነፋስ ከፍተኛ የአየር ግፊት ካለበት አካባቢ፣ ወደ ዝቅተኛ ግፊት አካባቢ ነው የሚነፍስ። በዓለማችን የተለያዩ ስሞች የተሰጡዋቸው የነፋስ ዓይነቶች አሉ፣ ከእነኚህ ውስጥ ከሰው ልጆች የባህር ላይ ጉዞ ጋር የተቆራኘው "ምሥራቁ ነፋስ" (ጥብሪት/ Trade winds) ይባላል። "በምሥራቁ ነፋስ" እገዛ፣ መርከቦች በአትላንቲክ፣ በሰላማዊ እና በኢንድያን ውቅያኖሶች፣ በአስተማማኝ ሁኔታ ተንቀሳቅሰው፣ የዓለም ዙሪያን ለማዳረስ ችለዋል። በዘመናችንም መርከቦች በነፋሱ አቅጣጫ የሚጓዙ ከሆኑ ፍጥነታቸው ይጨማራል፣ ከነፋሱ በተቃራኒ አቅጣጫ የሚጓዙ ከሆኑ ደግሞ ፍጥነታቸው ይቀንሳል። የነፋስ እንቅስቃሴ በየአይሮፕላን ጉዞ ላይም ተመሳሳይ ተፅእኖ ያደርሳል።

በብዙ ሺ ካሬ ኪሎ ሜትር በሚለካ የውቅያኖስ ገፅታ ላይ የሚገኝ ውሃ ሙቀት ሲጨምር፣ ከባህር በላይ ያለው የአየሩ ሽፋን ሙቀት አብሮ ይጨምራል። ሙቁ አየር በቀዝቃዛ አየር ወደ ተሸፈነው አካባቢ ከላይ ሲገሰግስ፣ ከታች ያለውን ውሃ ይጎትተዋል፤ ይስበዋል፤ የውሃው ጉዞ (current) ፍጥነትም እንዲጨምር ያደርገዋል። የውቅያኖስ ውሃ እንቅስቃሴ ከላይ በሚታይ ሁኔታም ሆነ ውስጥ ለውስጥ ይካሄዳል። ቀዝቃዛ ውሃ ከታች ተነስቶ ወደ ባህሩ ገፅታ ሲፈስ፣ ከላይ ያለው ሙቅ ውሃ ደግሞ ቀዝቃዛው ወደነበረበት አካባቢ ይንቀሳቀሳል። በሂደት ቀዝቃዛው ውሃ "ንጥረ ምግብ" ግብዓቶችን ከነበረቡት/ከሚገኙበት ጥልቅ ባህር፣ የፀሐይ ብርሃንና ሙቀት ወደሚደርስበት ወደ ባህሩ ገጽ አካባቢ ያመጣቸዋል።

የእንቅስቃሴው መንስዔ በፀሐይ ኢነርጂ በመሬት ሰቅ አካባቢ ያለው አየር እንዲሁም የውቅያኖስ ውሃ ከሰቁ ራቅ ብሎ ከሚገኝ አካባቢ በበለጠ ሁኔታ ለሙቀት ስለሚዳረግ ነው። ስለሆነም የነፋሱም ብሎም የውሃው እንቅስቃሴ መንስዔ የፀሐይ ኃይል ነው።

ፀሐይ በምድር ላይ ያለው የቀን ተቀን ሙቀት ሚዛናዊ እንዲሆን ታግዛለች። ቀን ፀሐይ በምታበራበት ጊዜ፣ የብስ (በአፈር የተሸፈነው አካል) ሙቀት ከውሃ አካላት (ውቅያኖስ፣ ባህር ሃይቅ) ሙቀት ጋር ሲነፃፀር ከፍ ያለ ነው። የብስ ላይ ያለው አየር ወደ ላይ ሲንር፣ በውሃ ገፅታ ላይ ያለው አየር ወደ የብስ ይነፍሳል፣ ብሎም የአካባቢውን ሙቀት ዝቅ ያደርገዋል። በተቃራኒው፣ ሌሊት የብስ አካባቢ ያለው የሙቀት መጠን በቶሎ ዝቅ ስለሚል፣ አካባቢው በቶሎ ይቀዘቅዛል፣ ብሎም የብስ ላይ ያለው ቀዝቃዛ አየር በዚያን ጊዜ ወደ ውሃ አካል (ባህር ወዘተ) ይነፍሳል። ውሃ ገፅታ ላይ ያለው ሙቅ አየር ከውሃ አካል ወደ የብስ ይነፍሳል። በዚህ ኩነት የብስ ላይ

ያለው ሙቀት እና ውሃ አካባቢ ያለው ሙቀት ሚዛን እንዲጠብቅ ሂደቱን ፀሐይ ታስተናግዳለች።

**ፀሐይ እና ወራት**

ምድር አንድ ጊዜ ፀሐይን ስትዞራት አንድ ዓመት ይባላል። ምድር ፀሐይን ስትዞር ገደድ ብላ/ ተንጋዳ ስለሆነ፣ ለፀሐይ ጠጋ ያለው አካባቢ የሙቀት ወቅት (ሳመር/Summer)፣ ራቅ ያለው ደግሞ የቀዝቃዛ ወቅት (ዊንተር/ winter) ይሆናል።

በስእሉ ላይ እንደሚታየው የምድር ሰሜን ዋልታ ከፀሐይ በሚርቅበት ወቅት፣ ከመሬት ሰቅ ሰሜን ያለው ቀዝቃዛ ወቅት፣ ከመሬት ሰቅ በታች ያለው የሙቀት ወቅት ይሆናል። በተቃራኒው የደቡብ የምድር ዋልታ ከፀሐይ በሚርቅበት ወቅት፣ ከመሬት ሰቅ ሰሜን ያለው የሙቀት ወቅት፣ ከሰቅ በታች ያለው ደግሞ ቀዝቃዛ ወቅት ይሆናል።

ከምድር ሰቅ በሰሜን በኩል የሙቀት ወቅት ከግንቦት እስከ ነሐሴ ሲሆን፣ በዚያን ወቅት ከምድር ሰቅ ደቡብ ያለው አካባቢ የብርድ ወቅት ነው። በተቃራኒው ከምድር ሰቅ ደቡብ ያለው አካባቢ የሙቀት ወቅት ከታኅሣሥ እስከ የካቲት ሲሆን፣ በዚያን ወቅት ከምድር ሰቅ በስተሰሜን ያለው አካባቢ የብርድ ወቅት ነው።

በተለምዶ በእንግሊዝኛ "ሳመር" የሚባለው ወቅት በሰኔ፣ በሐምሌ እና በነሐሴ ስለሆነ እኛ ክረምት የምንለው ወቅቱ እነሱ "ሳመር" የሚሉት ነው። ስለሆነም ነው በጋ እና ክረምት የሚለውን ትተን፣ የብርድ ወቅት እና የሙቀት ወቅት ብለን የገለጽነው።

ምድር በራሷ ላይ አንድ ጊዜ ስትዞር፣ በፀሐይ ጎን ያለው ብርሃን፣ በተቃራኒ ጎን ያለው ግማሽ አካል ጨለማ ይሆናል፣ የብርሃኑ እና የጨለማው ጊዜ ድምር አንድ ቀን ይባላል፣ ሃያ አራት ሰዓት። መሬት ሰቅ አካባቢ ያሉ ቦታዎች፣ ተመጣጣኝ የጨለማ እና የብርሃን ጊዜ አላቸው፣ ስለሆነም 12 ሰዓት ጨለማ 12 ሰዓት ብርሃን ያገኛሉ። ከመሬት ሰቅ በራቅን መጠን ብርሃኑ እና የጨለማው የጊዜ መጠን ድርሻ በተመጣጣኝ ሁኔታ እንደርቀቱ ይቀያየራል።

**ተፈጥሮያዊ ዑደቶች**

ፀሐይ በተፈጥሯዊ ዑደቶች ላይ ወሳኝ ሚና አላት። በፀሐይ መንስዔ ለሚከሰቱት ግዙፍ የቁስ ዑደቶች የውሃ ዑደት እንደምሳሌነት ሊወሰድ ይችላል። ምድራችን ላይ ውሃ ሦስት ዓይነት ባህርያት አሉት፣ እነሱም ጠጣር (በረዶ/ ሸኸት)፣ ፈሳሽ (ውሃ) እና ጋዝ (የተነነ ውሃ/ እንፋሎት/ ደመና) ናቸው። የውሃ ዑደት የውሃ ባህርያት የመቀያየር ውጤት ነው። ውሃ በፀሐይ ሙቀት መንስዔ ተኖ፣ ፈሳሽ የነበረው ወደ እንፋሎትነት

> **በአፈር አመሠራረትም የፀሐይ እጅ አለበት። ዝናብ ከሰማይ ሲወርድ አየር ውስጥ ያለውን ካርቦን ዳይኦክሳይድ አሟምቶ፤ የራሱ አካል አድርጎ ወደ መሬት ይወስዳል (ያዘንበዋል)።**

ይቀየራል፣ ያም የሰማይ ዳማና ይሆናል። ደመናው ሲቀዘቅዝ የተሸከመው ውሃ በዝናብ መልክ ወደ መሬት ወርዶ ወንዞችን፣ ሃይቆችን ይሞላል፣ ወንዞችም ወደ ውቅያኖስ ይፈሳሉ። ለፀሐይ የተጋለጠው ውሃ ሙቀቱ ይጨምርና እንደገና ይተናል፣ ከዚያም ደማና፣ ብሎም ዝናብ ይሆናል፣ ዑደቱ ይቀጥላል።

**ፀሐይ እና ሕይወት**

የጋዝ (gas) ይዘት ያለው "ካርቦን ዳይከሳይድ" ($CO_2$) ምንም መጠኑ ትንሽ ቢሆንም ምድራችን ሕይወት አልባ እንዳትሆን ዋና ሚና አለው። ይኸውም ከላይ እንደተጠቀሰው የፀሐይ ጨረር ሙቀት ምድር ላይ ከደረሰ በኋላ ተንፃባርቆ ወደ ሕዋ እንዳይመለስ ሽፋን፣ መጋረጃ ሆኖ የፀሐይ ሙቀት ምድር ላይ እና ዙሪያ ታምቆ እንዲቆይ ስለሚያደርግ ነው። መጠኑ እስከተወሰነ ድረስ ሙቀቱ ለሕይወት አስፈላጊ ነው። ይህም ከላይ እንደተጠቀሰው "ዝገ ክበብ አየር" (green house effect) ይባላል፣ ባህሪዩም መስኮቱ እንደተዘጋ መኪና ሊመሰል ይችላል። መስኮቱ የተዘጋ መኪና ውስጥ ያለው አየር፣ ውጭ ካለው አየር በላቀ ደረጃ ይሞቃል።

የእፅዋት ቅጠሎች በፀሐይ ብርሃን ኃይል ታግዘው "ካርቦን ዳይኦክሳይድን" ($CO_2$) በመማግ ወደራሳቸው አካልነት ይቀይራሉ፣ ይኸን የሚተገብረው የእፅዋት ፋብሪካ "ክሎሮፊል" (Chlorophyll) ሲባል፣ የመፈብረኩ ሂደት "ብርሃን አስተፃምሮ" (ፍቶሲንቴስስ/ photosynthesis) ይባላል። በፀሐይ ኃይል ቀጥተኛ ተጠቃሚው ፋብሪካ "ክሎሮፊል" ካርቦን ዳይኦክሳይድን ($CO_2$) ምጎ፣ በምትኩ ኦክስጅንን ($O_2$) ይተፋል። "ኦክስጅን" ($O_2$) ለሕያው ሕልውና ወሳኝ ሚና አለው፣ ስለሆነም "ካርቦን ዳይኦክሳይድ" ለሕያው መሠረት ነው። እንስሳት የራሳቸውን ምግብ ስለማያዘጋጁ፣ በእፅዋት የተዘጋጀውን ምግብ ነው የሚመገቡ። በዚህ ሂደት ነው ፀሐይ በሕያው ላይ ያላት ሚና ቁልጭ ብሎ የሚታየው።

እፅዋት ወይም እንስሳት በባህር ውስጥ ሲሞቱ፣ ቅሬቶቻቸው ይበሰብሳል፣ ብስባሹ ለሕያው የምግብ ግብዓት ወደ ሆኑ ንጥረ ነገሮች ይቀየራል። ሆኖም የፀሐይ ብርሃን እና ሙቀት ወደማይደርስበት፣ ብሎም እፅዋት ወደማይኖሩበት ይዘቅጡና፣ ከምግብ ግባትነት ይሰወራሉ። በውቅያኖስ፣ በባህር፣ በሃይቅ፣ የውስጥ የውሃ እንቅስቃሴ (ማዕበል/ current) እነኚህን የዘቀጡ "ንጥረ-ምግብ" እፅዋት ወደሚኖሩበት፣ ጥልቀተ-ውስን ወደሆነ የውሃው አካል ይወስዳሉ፣ ብሎም "ለውሃ አቅላሚ" (አልጌ/ algae) ለምግብ ግባትነት ያገለግላሉ።

በውሃ ውስጥ፣ "ለቀዳማይ አምራችነት" (Primary productivity)፣ "ለአልጌ" እና ተመሳሳይ ንዑስ እፅዋት የእድገት ግብዓት የሚሆኑ "ንጥረ-ምግብ" (Nutrients) በዚህ ሂደት ነው የሚገኙ። "ውሃ አቅላሚዎችን" የሚመገቡ እንስሳት፣ በተለይ የዓሳ ዝርያዎች ምግብ አግኝተው ለመራባት ይበቃሉ። እነኚህ ዓይነት የውሃ እንቅስቃሴዎች (ከጥልቅ ባህር ወደ ላይ የሚዘልቁ) ባሉበት አካባቢ መጠኑ ጠቀም ያለ አሳ ማምረት ይቻላል።

በአፈር አመሠራረትም የፀሐይ እጅ አለበት። ዝናብ ከሰማይ ሲወርድ አየር ውስጥ ያለውን ካርቦን ዳይኦክሳይድ አሟምቶ፤ የራሱ አካል አድርጎ ወደ መሬት ይወስዳል (ያዘንበዋል)። ካርቦን ዳይኦክሳይድ ከውሃ ጋር በመዋሃድ ወደ "ካርቦኒክ አሲድ" (Carbonic acid) ተቀይሮ፣ አለት ይሰነጣጥቃል፣ ይሰባብራል፣ እንዲሁም በሌሎች አካላት ላይ የአሲድነት ተፅዕኖ ያደርጋል። በቀን የፀሐይ ሙቀት በሌሊት ቅዝቃዜ ሲከሰት፣ ድንጋይ (አለት) ይፈረካከሳል፣ ይሰባበራል፣ ብሎም ወደ አፈርነት ይቀየራል። በምድር ላይ የሚበቅሉ እፅዋት የምግብ ፍጀታ የሚያገኙ፣ በ"ብርሃን አስተፃምሮ" ከሚገኘው በተጨማሪ አፈር ነው። ስለሆነም ፀሐይ በእጅ አዙር ለአፈር መገኘትም አንዷ ምክንያት ናት።

ፀሐይን ከብዝሃ ሕይወት አንፃር እንፈትሻት። የመሬት ሰቅ አካባቢ ከሰሜን እና ከደቡብ ዋልታ አካባቢዎች የላቀ የፀሐይ ሙቀት እና ብርሃን ያገኛል። ያም የመሬት ቅርጽ ዱባ መሰል ስለሆነ፣ የመሬት ሰቅ አካባቢ ከሌላው አካባቢ ለፀሐይ የተሻለ ቅርበት አለው። እንዲሁም ሌሎች

አካባቢዎች በተወሰኑ ወራት ጠንፍ በረገጠ ብርድ ሲቆፈደዱ፣ የመሬት ሰቅ አካባቢ ሁልጊዜም ከፀሐይ ሙቀት እና ብርሃን አይነፈግም። ኬሚካላዊ ሂደቶች በሙቀት መንስዔ በመሬት ሰቅ አካባቢ ፈጣን ስለሆኑ፣ የረገፉ ቅጠሎችም ሆኑ ሕያው አልባ የሆኑ እፅዋት እና እንስሳት ቅሪቶች ውስጥ ያለው ኬሚካላዊ ውሁድ፣ በቀላሉ ይፈራርስ እና በውስጡ ያለው "ንጥረ-ነገር" (nutrients) ለምግብ ግብዓትነት ያገለግላል።

የዚህ ውጤት የሕያው መራባት እና እድገት ግብዓት የሆኑ ንጥረ-ምግብ በብዛት ይገኛሉ። ስለሆነም በአካባቢው የሕያው እድገት፣ በተለይ እፅዋት በጣም ፈጣን ነው። ለምሳሌ በሰሜን እና በደቡብ ዋልታዎች አጠገብ ያሉ እፅዋት አስረተ-ዓመታት የሚፈጅባቸው የእድገት መጠን፣ በምድር ሰቅ አካባቢ ያሉት ተመጣጣኝ እድገት በጥቂት ዓመታት ሊከናወን ይችላል።

የተለያዩ ኩነቶች ተደምረው፣ በመሬት ሰቅ አካባቢ ያሉ የእርጥበት እጥረት የሌለባቸው ቦታዎች የብዝሃ ሕይወት ባለፀጋዎች ሆነዋል። በዓለማችን ያሉ የተፈጥሮ ግዙፍ ደኖች፣ "የአማዞን" እና "የኮንጎ" ደኖች የሚገኙ በምድር ሰቅ አካባቢ ነው። በእነዚህ ደኖች ውስጥ በጣም ብዙ የእፅዋት እና የእንስሳት፣ ብሎም "የዘረ እንጉዳይ" (fungus) እና የማይክሮቦች "ብቸኛ ዝርያዎች" (species) ይገኛሉ። የብቸኛ ዝርያዎች ቁጥር በጨመረ መጠን፣ የብዝሃ ሕይወት ሃብትም በተመጣጣኝ ሁኔታ ይጨምራል።

ፀሐይ እንዲሁም ከእንስሳት ባህሪዎች ጋር የተዛመደች ናት፣ በእንስሳት ስደት/ ፍልሰትም ወሳኝ ሚና አላት። ለምሳሌ:- ብዙ የአእዋፍ ዝርያዎች "ከሰሜናዊ ሄሚስፊር" (Northern Hemisphere) ቀዝቃዛ ወራት ሸሽተው ወደ መሬት ሰቅ (equator) አካባቢ ይሰደዳሉ። ወቅቱን ጠብቀው "ሰሜናዊ ሄሚስፊር" ከቆፈድ ሲላቀቅ፣ ቀደሞ ወደ ነበሩበት አካባቢ ይመለሳሉ። በዚህ ተግባር አእዋፍ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን ያቋርጣሉ።

በፀሐይ እና በሕያው ግንኙነቶች፣ ብዙ አስደናቂ እና አስገራሚ የሆኑ ኩነቶች ተከስተዋል። ለምሳሌ:- በቀዝቃዛ ወራት አሸልቦ ወቅቱን በእንቅልፍ መሰል ሁኔታ ማሳለፍ ማለት በ"ሸሺጋ" (hibernation) ሁኔታ የገላ ሙቀት፣ የልብ ትርታ፣ ብሎም አተነፋፈስ እንዲቀንስ ይደረጋል። በዚህ ሂደት ለሕያው አካል የሚያስፈልገው የኢነርጂ መጠን ተቀጥቦ፣ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግል ይደረጋል። "ሸሺጋ" በብዛት የሚከሰተው በቀዝቃዛ ወራት ሲሆን፣ ከእንቅልፍ በጣም በረዘመ ሁኔታ ተከስቶ፣ ሕልውናን ሳይገዳደር ለወራት ሊዘልቅ ይችላል። ከሌላ አንፃር ድርቅ እና ሙቀቱ የናረባቸውን ወቅቶች "በአህብቦት" estivation) ከተለመዱ የሕያው ተግባራት ተቀጥበው መጥሮ ጊዜን ማሳለፍ የሚችሉ ሕያው አካላት አሉ። እንዲሁም ቀን የብርሃንና የሙቀት ጊዜ ስለሆነ እና ሌሊት በተቃራኒው ጨለማ እና ቀዝቀዝ ያለ ስለሆነ፣ በብዙ እንስሳት ጨለማ የእረፍት ጊዜ (የእንቅልፍ) እና ቀን የእንቅስቃሴ ጊዜ ተደርጎ "በየሕያው ወቅት ልክ" (biological rhythm) ይስተናገዳል።

**የኤሌክትሪክ ኃይል ከፀሐይ ማግኘት የተቻለው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሲሆን (እንደ ግሪጎሪያን አቆጣጠር በ2021)፣ በዓለማችን ከሚመረተው የኤሌክትሪክ ኃይል አራት በመቶ (4%) በቴክኖሎጂ እገዛ ከፀሐይ የሚገኘው ኢነርጂ ነው።**

## መደምደሚያ

በምድራዊ ኩነቶች ሁሉ የፀሐይ እጅ አለበት። ካለ ፀሐይ አስተናጋጅነት ሕይወት መኖር ይቅር እና ልትታለምም አትችልም ነበር። ፀሐይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ፣ የሕያው ምግብ ፋብሪካ ሞተር ናት። ለሕያው አስፈላጊ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በፀሐይ እገዛ ነው የሚተገበሩት።

ፀሐይ ለሰው ልጆች የተስፋም፣ የስጋትም ምንጭ ናት። ስጋቱ ከአየር ቅጥ ለውጥ ጋር የተጓዳኘ ሲሆን፣ ተስፋው ደግሞ ፀሐይ የወደፊት ወሳኝ ብክለት አልባ የኢነርጂ ምንጭ መሆን ስለምትችል ነው። ፀሐይ የምትከስመው ያላትን እምቅ ኢነርጂ ተጠቅማ ስታበቃ ሲሆን፣ ያም አምስት ቢሊዮን ዓመት ገደማ እንደሚፈጅ ይገመታል፣ ስለሆነም ቋቱ በቅርብ ጊዜ አይነጥፍም።

የስጋት ምንጭ የሆነው፣ ቀጥታውን ፀሐይ ሳትሆን፣ ሰበነክ የሆነ ተግባር ከፀሐይ ሙቀት ጋር ተቆራኝቶ የሚከሰት ችግር ነው። የችግሩ መንስዔ የእፅዋት ቅሪት የሆኑ፣ በከርሰ ምድር የሚገኙ የነዳጅ ዘይትን እና የድንጋይ ከሰል ያለአግባብ ከመጠቀም የሚመነጭ ነው። በዚህ ተግባር የሚያመነጨው የጋዝ ዓይነት "ካርቦንዳይኦክሳይድ" ($CO_2$) ነው የአየር ቅጥ ለውጥ (Climate Change) ዋናው መንስዔ የሆነው። በሕዋ ሽፋን ብክለት መንስዔ የምድራችን ሙቀት እየናረ ሄዶ፣ ምድራችን ለሕያው መኖሪያ ምቹ የማትሆንበት ደረጃ ልትደርስ ትችላለች። ይህንን ስጋት ለመቅረፍ ብዙ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እየተመሠረቱ እና መርሃ ግብሮች እየተተገበሩ ይገኛሉ። በአገራችን የዛፍ ተከላ ፕሮግራምም (የአረንጓዴ አሻራ) የዚህ እንቅስቃሴ አካል ነው።

የተስፋው ምንጭ በቴክኖሎጂ እገዛ በፀሐይ ኢነርጂ በመጠቀም አላስፈላጊ ብክለትን ማስቀረት ነው። ከድንጋይ ከሰል እና ከፈሳሽ ነዳጅ የሚገኘውን ኢነርጂ ከፀሐይ በሚገኝ ኢነርጂ መተካት ነው። ከተስፋ ጋር ተዛምዶ ስለ ፀሐይ ኃይል ብዙ እየተባለ ነው። በዘመናችን በቴክኖሎጂ አማካኝነት ከፀሐይ የሚገኝ ኢነርጂ ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ኢነርጂ ቀለል ባለ ወጪ ለማግኘት ተችሏል። ከፀሐይ የሚገኘው ኢነርጅም መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። ፀሐይ ተዝቆ የማያልቅ የእምቅ ኢነርጂ ምንጭ ስለሆነች፣ የሰው ልጆች ከተፈጥሮ በዘለለ በቴክኖሎጂ የሚታገዝ የኢነርጂ ማምረቻ በመሆን ታገለግላለች።

የኤሌክትሪክ ኃይል ከፀሐይ ማግኘት የተቻለው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሲሆን (እንደ ግሪጎሪያን አቆጣጠር በ2021)፣ በዓለማችን ከሚመረተው የኤሌክትሪክ ኃይል አራት በመቶ (4%) በቴክኖሎጂ እገዛ ከፀሐይ የሚገኘው ኢነርጂ ነው። ምንም እንኳ ከፀሐይ የሚገኘው ኢነርጂ ብክለት አልባ ቢሆንም፣ በአጠቃቀም ላይ ጥቂት ተግዳሮቶች አሉት። ለጊዜው ዋናው ማነቆ፣ ኢነርጂ ማመንጨቱ ሳይሆን፣ የተገኘውን ኢነርጂ በምን መልክ አቆይቶ ለመጠቀም የመቻሉን አቅም ማጎልበቱ ነው። ችግሩ ማከማቻው እንጂ ማምረቱ አይደለም። ዋናው የኢነርጂ ማቆያ ባትሪ ስለሆነ፣ የባትሪ ይዘት ቴክኖሎጂ በማዳበር ችግሩ እንደሚፈታ ይታሰባል።

ለወደፊት ብክለት አልባ የኢነርጂ ምንጭ የሚሆነው፣ ፀሐይ ኢነርጂ የምታመነጭበት ዘዴ በመኮረጅ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል። የፀሐይ ኢነርጂ ምንጭ ሁለት የሃይድሮጅን አቶም ኑክሊየሶችን በመቀላቀል (nuclear fusion) የተገኘ ሲሆን፣ በኢነርጂው አጠቃቀም ሂደት አካባቢ የሚበክል ዝቃጭ አይኖርም። የሚገኘውም ኢነርጂ የትየለሌ ነው። ስለሆነም ፀሐይ የብሩህ ተስፋ ፏፏቴ፣ የሕይወት መሠረት፣ ብሎም ተፈጥሮ የለገሰችን ተተኪ የሌላት ስጦታ ናት።



ገዳሙ የተገደመው ቅዱስ ያሬድ ተብሎ በሚታወቀው ተራራ ስር ከሚገኘው ዋሻ ውስጥ ፊቱን ወደ ሰሜን አቅጣጫ፣ ወደ ጠለምት ወረዳ አዙሮ ነው። ቅዱስ ያሬድ ገዳም ዙሪያውን በጠለምት፣ በአዳርቃይ፣ በጃናሞራ እና በበየዳ በአራት ወረዳዎች የተከበበ ነው።

# የገዳሙ ትንሳኤ

**የፕሮጀክቱ ሥራ ትልቅ የባህል፣ የታሪክ እና የቅርስ ማዕከል ተደርጎ የሚታይ በመሆኑ፣ የሚመለከተው ሁሉ ፕሮጀክቱን በአግባቡ ተገንዝቦ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማድረግ የቅስቀሳ ተግባር ይከናወናል።**



በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ በለጠ

**ንጉሤ ተስፋዬ**

ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ከእናቱ ታውክሊያ (ክርስቲና) እና ከአባቱ ይስሐቅ (አብድዩ) ሚያዝያ 5 ቀን 505 ዓ.ም. በአክሱም ከተማ ተወለደ። የቤተ ክህነት ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ የብሉይና የሐዲስ መምህር ሆኖ አገልግሏል። በተለይም ቅዱስ ያሬድ ዘመን በማይሽራቸው የዜማ ድርሰቶቹ በዓለም ይታወቃል። በቅዱስ ያሬድ የተደረሱት የዜማ መጽሐፍት አምስት ሲሆኑ እነሱም ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ዝማሬ፣ መዋሲት እና ምዕራፍ ናቸው። የዜማ ድርሰቶቹንም ያዘጋጃቸውም በሦስት ዓይነት ድምፅ ሲሆን በግእዝ፣ በዕዝል እና በዓራራይ ዜማ ነው። እነዚህ የዜማ አይነቶች ደግሞ የአንዱ ድምፅ ከሌላኛው ያልተደበላለቀ ወጥ የሆነ ድምፅ ያላቸው ናቸው። ዜማዎቹን በስምንት ምልክቶች ቀምሮ አስቀምጧቸዋል። የምልክቶች አገልግሎትም በትምህርት ሂደት ጊዜ የጠቋሚነት ሚና በመጫወት ለዜማው መጠበቅ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው።

ቅዱስ ያሬድ በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት በሰሜን ተራሮች ቅዱስ ያሬድ በመባል በሚታወቀው ተራራ ስር፣ ዋሻ ውስጥ በምናኔ ተወስኖ ፈጣሪውን በብሕትውና እያገለገለ ኖሯል። ብዙ ዓመታትን በዋሻው ውስጥ ካሳለፈ በኋላ ግንቦት 11 ቀን በ 571 ዓ.ም ተሰውሯል (አርጓል)። ይህ ያረገበት ልዩ ቦታ ደግሞ የ "ደብረ ሃዊ ቅዱስ ያሬድ ገዳም" ተሰኝቶ ሃይማኖታዊ ሥርዓት እየተከወነበት ተጠብቆ ይገኛል።

ቅዱስ ያሬድ ገዳም የሚገኘው በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ዞን በየዳ ወረዳ ውስጥ ነው። ገዳሙ የሚገኝበት አካባቢ በተፈጥሮ አቀማመጡ፣ በውስጡ በሚገኙት ብርቅየ የዱር እንስሳትና አእዋፋት መገኛ በሆነው እና በዩኔስኮ በተመዘገበው የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ ነው። በተለይም ደግሞ በበየዳ ወረዳ ውስጥ ከሚገኘው ከስመ ገናናው የራስ ደጀን ተራራ፣ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የተራራውን ሰንሰለት ተከትሎ በቅርብ ርቀት ላይ ሳብራ ቀበሌ ይገኛል። ገዳሙ የተገደመው ቅዱስ ያሬድ ተብሎ በሚታወቀው ተራራ ስር ከሚገኘው ዋሻ ውስጥ ፊቱን ወደ ሰሜን አቅጣጫ፣ ወደ ጠለምት ወረዳ አዙሮ ነው። ቅዱስ ያሬድ ገዳም ዙሪያውን በጠለምት፣ በአዳርቃይ፣ በጃናሞራ እና በበየዳ በአራት ወረዳዎች የተከበበ ነው። ገዳሙ ከእነዚህ አራት ወረዳዎች አማካይ በሆነ ቦታ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ ይሁን እንጂ ከሁሉም ወረዳዎች ጋር በየብስ ትራንስፖርት በቀላሉ የመገናኘት ዕድል የለውም።

አካባቢው ተራራማ፣ ገደላማ፣ ጠመዝማዛና ትልልቅ አለት ድንጋይ የሚበዛበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለተለያዩ መሰረተ ልማት




አዲስ የሚገነባው የደብረሃዊ ቅዱስ ያሬድ አንድነት ገዳም ዲዛይን



አቶ ካሳሁን ንግሩ

> **ግንባታ የሚያርፍበትን ቦታም ከሶስተኛ ወገን ነጻ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።**

ዝርጋታ አስቸጋሪ ነው። ስለሆነም ወደ ገዳሙ ለመድረስ ብቸኛው አማራጭ በእግር መጓዝ ነው። እሱም ቢሆን በእግር የመጓዝ ልምድና ጥንካሬን፤ ከፍተኛ ብርድን መቋቋምን፤ ተራራ መውጣትና መውረድን እንዲሁም ለቀናት የሚበላ ስንቅ መያዝን ይጠይቃል። በእነዚህና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች ገዳሙ ትኩረት ተነፍጎት ቆይቷል። በመሆኑም ይህን ስመ ገናና እና ታሪካዊ ሀብት የቅርብም ሆነ የሩቅ ምዕመን ሊያየው፣ ሊጎበኘውና ሊንከባከበው አልቻለም። የጉዞውን ውጣውረድና ዘርፈ ብዙ ችግር መቋቋም የሚችልና በአካባቢው በቅርብ ርቀት የሚኖረው ማህበረሰብ ግን የዘወትር ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ለዘመናት አስጠብቆት ኖሯል። በገዳሙ ውስጥ የሚኖሩ መነኮሳትም በቂ መተዳደሪያ የላቸውም። የቀለብ ፣ የአልባሳት እና የመጠለያ ችግር አለባቸው። አሁን ላይ ግን መነኮሳቱ፣ የአካባቢው ማህበረሰብና ገዳሙ ለዘመናት ከዋጠው ድቅድቅ ጨለማ ተላቀው ብርሃን ሊወጣላቸው፣ ወጋገኑን ከሩቅ መታየት የጀመረ ይመስላል።

የደብረ ሃዊ ቅዱስ ያሬድ ገዳም 1500ኛ ዓመት ምስረታ በዓል በ2005ዓ.ም. በአዲስ አበባ በማህበረ ቅዱሳን ተከብሮ ነበር። ከዚህ በዓል መከበር ጋር ተያይዞ ወደ ገዳሙ የጉዞ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ገዳሙን የመጎብኘት ሥራም ተከናውኗል። በጉብኝቱ የተስተዋለውን የገዳሙን ሁለንተናዊ ችግር በመገንዘብ ገዳሙን ዘመናዊ በሆነ መንገድ ለመሥራት 10 አባላት ያሉት የእርዳታ አሰባሳቢ ዐቢይ ኮሚቴ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትሪያርክ ጠቅላይ ጽህፈት ቤት ሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ተቋቁሟል። የገዳሙ አስተባባሪ ኮሚቴ የተመረጠው ደግሞ በፕሮጀክቱ የበላይ ኃላፊ በሊባኖስና መካከለኛው ምስራቅ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በብጹ አቡነ ዲሜጥሮስ ነው። ጥር 19 ቀን 2008ዓ.ም ደግሞ የበየዳ ወረዳ የአካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠባበቅ ጽህፈት ቤት በሳብራ ቀበሌ በሰጠው ስድስት ሄክታር መሬት ላይ የመሰረት ድንጊያ ተጥሏል።

የ"ደብረ ሃዊ ቅዱስ ያሬድ ገዳም የግንባታ ፕሮጀክት ማህበር ሰብሳቢ በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ በለጠ ይባላሉ። በሙያቸው ጋዜጠኛና ደራሲ ሲሆኑ፣ የአሐዱ ሬዲዮና ቴሌቭዥን ዋና ሥራ አስኪያጅ እና በኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ደግሞ ዋና ጸሐፊ ናቸው። እንደሳቸው ገለጻ ገዳሙ ታሪካዊ እና ሃይማኖታዊ ቅርስ ይሁን እንጂ የገዘፈ ታሪካዊነቱን በሚመጥን ደረጃ እየተጠበቀና ማበርከት የሚገባውን አገልግሎትም እየሰጠ አይገኝም። የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የአማራ ክልል፣ ከዚያም አልፎ ሀገር ከዚህ ቅርስ ማግኘት የሚገባውን ሁለንተናዊ ጥቅም እያገኘ አይደለም። እንዲያውም ገዳሙ ከጊዜ ብዛት የተነሳ እየፈረሰ እና በውስጡ የሚገኙ መነኮሳት ሳይቀሩ የተለመደ አገልግሎትን ለመስጠት እየተቸገሩ ነው። በመሆኑም ማህበሩ የተለያዩ ችግሮች ያሉበትን ገዳም ደረጃውን በጠበቀ መንገድ ማልማት እንዲቻል፣ የግንባታ ፕሮጀክት አዘጋጅቶ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በማቅረብ አስጸድቆና ህጋዊ ፈቃድ አግኝቶ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኝ የበጎ ፈቃድ ስብስብ ነው።

በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ እንደሚያስረዱት ቅዱስ ያሬድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ ዋነኛው የዜማ፣ የድርሰት፣ የታሪክ፣ የብዙ ፍልስፍናዎች ባለቤት እና ታላቅ ሊቅ መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ቦታው እጅግ ታሪካዊ፣ ብዙ ገቢረ ታምራት ያለበት እና የቤተክርስቲያኒቷ ዋናው ቅዱስ የሚባለው ቅዱስ ያሬድ የተሰወረበትን ቦታ ለማየት፣ ለመሳለም፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ለማከናወን ሰዎች ይመላለሱበታል። ገዳሙ ለሕዝበ ክርስቲያኑ፣ በአጠቃላይም ለኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ ማዕከል መሆን የሚችል ቦታ ይሁን እንጂ በልዩ ልዩ ምክንያት ትኩረት ሊሰጠው ባለመቻሉ ብዙ ችግሮች ገጥመውታል። ምዕመናን እንደልባቸው ወደ ገዳሙ ለመሄድ ስለማይችሉም ተሰውሮ የሚገኝ ዘርፈ ብዙ ሀብት ለመሆን በቅቷል። ይህን

ታሪካዊ ስፍራ ከቦታው ድረስ በመሄድ ሁኔታውን የተመለከቱና የተረዱ ታላላቅ ሰዎች፣ ሕዝብ እንዲያውቀው ሲሉ የገዳሙን የግንባታ መነሻ ሃሳብ አቅርበዋል።

በግንባታው የተካተቱ ተግባራትን በተመለከተ በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ ሲናገሩ፣ ማህበሩ በሕጋዊ መንገድ በተረከበው ስድስት ሄክታር መሬት ላይ በዋናነት አካባቢውን በማልማት የቅዱስ ያሬድ መንፈሳዊ ከተማ ማድረግ ነው ይላሉ። የፕሮጀክቱ ዓላማም የነበረውን ቤተክርስቲያን ማደስ ብቻ ሳይሆን ለምዕመናን ገዳሙ ምቹ ሆኖ ብዙዎች ሄደው የሚያርፉበት፣ የጥናትና ምርምር ማዕከል የሚሆንበት፣ የተለያዩ ሀገረ ስብከቶች ሲሄዱ የየራሳቸው ማረፊያ የሚኖራቸው እንዲሁም የቤተክርስቲያኒቱ አስተምህሮ ትምህርቶች የሚሰጡበት ቦታ ማድረግ እንደሆነም ያስረዳሉ። ቦታውን ምዕመናን እና ምዕመናንት እንደልባቸው እንዲመላለሱበት ማድረግ ሲባል ግን ውጣ ውረዱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በቀላሉ ሮጦ ተብሎ የሚገባበት ሳይሆን ተጓዦች መንገዱ አመቺ ባለመሆኑ እንዳይቀሩ፣ ረጅም ጊዜ ቢወስድባቸውም እያረፉና ቀስ እያሉ ወደ ቦታው የሚደርሱበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ማለት መሆኑን በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ አስምረውበታል። ፕሮጀክቱ ወደ ገዳሙ የሚያደርሱ የመንገድ እና ሌሎች መሰረተ ልማቶችም ታሳቢ መደረጋቸውን፣ በተለይም አካባቢው የመሰረተ ልማት ችግር ያለበት ስለሆነ፣ ከአካባቢው የሕዝብ ተመራጭ የፓርላማ አባላት ተወካዮች ጋር በመወያየት፣ የሰሜን ጎንደር ዞን፣ የአማራ ክልል፣ ከዚያም አልፎ የፌዴራል የባህል የቱሪዝምና የቅርስ ባለሙያዎችንና የሥራ ኃለፊዎችን በማነጋገር ከፕሮጀክቱ በተጓዳኝ እንዲሠራ ለማድረግ መታቀዱን በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ አብራርተዋል።

የደብረ ሃዊ ቅዱስ ያሬድ ገዳም ፕሮጀክት የበላይ ጠባቂዎች ተሰይመውለታል። በአባልነት ብጹዓን አባቶች እና የሃይማኖት መሪዎች የተካተቱ ሲሆን ፕሮጀክቱን የመምራት፣ የመቆጣጠር እና ችግር ሲያጋጥም ደግሞ ለችግሩ መፍትሄ የማፈላለግ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል። የደብረ ሃዊ ቅዱስ ያሬድ ገዳም ፕሮጀክት በተጠናው ጥናት መሰረት በአጠቃላይ ይፈጀል ተብሎ የታሰበው የበጀት መጠን ከሁለት ነጥብ አምስት እስከ ሶስት ቢሊዮን ብር የሚደርስ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የግንባታው ሥራም ከአምስት እስከ ሰባት ዓመታት ድረስ ይጠናቀቃል ተብሎ ይታሰባል።

አቶ ካሳሁን ንግሩ በአማራ ክልል የሰሜን ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ቡድን መሪ ናቸው። ተቋማቸው በደብረ ሃዊ ቅዱስ ያሬድ ገዳም ግንባታ ፕሮጀክት ተገቢው ዕውቅና እንዳለው ይናገራሉ። ከዚያም አልፎ የግንባታ ዲዛይኑን ለአካባቢው ማህበረሰብ ይፋ የማድረግና ለባለድርሻ አካላትም ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ መከናወኑን ያብራራሉ። ግንባታ የሚያርፍበትን ቦታም ከሶስተኛ ወገን ነጻ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል። ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ረገድም ተቋሙ የግንባታ ፕሮጀክቱ ዕውን እንዲሆን ለማስቻል ከአጋር ተቋማት ጋር በመነጋገር የግንባታ ቦታውን መስጠትና ለተፈናቃይ አርሶ አደሮች ምትክ ቦታ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል። በተለይም ከወረዳ ቤተክህነት፣ ከገጠር መሬት አስተዳደርና አጠባበቅ እንዲሁም ከግብርና እና ከቱሪዝም ጋር በጋራ በመሥራት ለፕሮጀክቱ የሚገባውን ድጋፍ ለማድረግ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ይገልጸሉ። አሁን ላይ ፕሮጀክቱ በመፍረስ ላይ የሚገኘውን የቆየውን ህንጻ ለመተካት በግንባታ ሂደት ላይ ከመሆን በዘለለ በአካባቢው የጎላ እንቅስቃሴ አለመኖሩን ያስረዳሉ።




ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው

## ቅርስ የሁሉም የአገሪቱ ሕዝብ ሀብት በመሆኑ፣ ሁሉም ዜጋ ጠብቆና ተንከባክቦ ለሚቀጥለው ትውልድ የማስተላለፍ የታሪክ ግዴታና ኃላፊነት አለበት።

እንደ በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ ማብራሪያ ደግሞ፣ የፕሮጀክቱን የግንባታ በጀት ለማሟላት የተለያዩ ፕሮግራሞች ታቅደዋል። በቅዱስ ያሬድ ስም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በየዓመቱ የሚካሄድ ትልቅ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽን ለማካሄድ ታቅዷል። የቅዱስ ያሬድ ቤተሰቦችን በመመስረትም በራሳቸው፣ በልጆቻቸው እና በቤተሰቦቻቸው በሚፈልጉት ስም አስራት እንዲከፍሉ ለማድረግ ታስቧል። ከአገር ውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንንም በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በማስተባበር ለማሳተፍ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። የፕሮጀክቱ ሥራ ትልቅ የባህል፣ የታሪክ እና የቅርስ ማዕከል ተደርጎ የሚታይ በመሆኑ፣ የሚመለከተው ሁሉ ፕሮጀክቱን በአግባቡ ተገንዝቦ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማድረግ የቅስቀሳ ተግባር ይከናወናል። ቅዱስ ያሬድ ከተወለደበት ተነስቶ የተማረባቸውን፣ የተጓዘባቸውን፣ ያስተማረባቸውን፣ መንፈሳዊ አገልግሎት የሰጠባቸውን እና የተሰወረበትን መንገዶችና ቦታዎች በሙሉ ያካተተ ለቅስቀሳ ተግባር የሚውል ዶክመንተሪ ፊልምም ተዘጋጅቷል።

በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ ሲያስረዱ፣ ፈርሶ የነበረው የቤተክርስቲያን ህንጻ በዘመናዊ መልክ እና አካባቢውን በሚመጥን መልኩ ተሠርቶ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። ለግንባታ የተፈቀደውን ስድስት ሄክታር መሬት ደግሞ የመከለል ሥራ በመሥራት በኢትዮጵያ የሥነ ህንጻ ማህበር የፕሮጀክቱን ዲዛይን በነጻ የማሠራት ሥራ ተከናውኗል። የተዘጋጀውን ዲዛይንም የሥነ ህንጻ፣ የታሪክ፣ የቅርስ፣ የሃይማኖት እና የተለያየ የሙያ ዘርፍ ባለሙያዎች እንዲተቹት በማድረግ ተጠናቋል። ተስፋ ሰጪ የሆኑ የገቢ ማሰባሰቢያ የቅስቀሳ መርሃግብሮች፣ በተለይም በድረ ገጽ እና በዲጂታል ሚዲያው ሥራ ላይ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ባላቸው በጎ ፈቃደኞች ዕገዛ ተግባሩ ተጀምሯል። በማህበራዊ ሚዲያውም በቅዱስ ያሬድ ስም የሚከናወኑ ተግባራትም የክንውኑ አካላት ናቸው።

ወደ ተግባር ለመግባት ከፕሮጀክቱ የበላይ ጠባቂዎች ጉባዔ በኋላ ለመጀመር ታቅዷል። ይህን ትልቅ ፕሮጀክት ዕውን ለማድረግ በሚደረገው እንቅስቃሴ በጎላ መልኩ ብዙ አባጣ ጎርባጣ ጉዳዮች ያላጋጠማቸው መሆኑን በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ ይናገራሉ። በቦታው በተለይም በቱሪዝም ዘርፉ ፣ከሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ጋር ተያይዞ ብዙ ዓለም አቀፍ ጥናቶች ተካሂደዋል። ለምሳሌ አካባቢው በአየር ላይ ከትልልቅ ተራራዎች ጋር የሚገናኝ ስለሆነ የገመድ ትራንስፖርትን ለመስራት ታስቦ ነበር። ነገር ግን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማህበሩ የተለያዩ ውይይቶችን በማድረግ፣ አካባቢው ገዳም በመሆኑ መንፈሳውያን እና መናንያን ያሉበት ስለሆነ፣ ምንም ዓይነት የድምጽም ሆነ፣ ሌላ ብክለት ሳይፈጠር የሚኅበኙበትን ሁኔታ ለመፍጠር መስማማት ተችሏል። ወደ ፊትም ቢሆን ፕሮጀክቱ አገራዊ ቅርስ ስለሆነ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ሊኖር የሚችለው የሥራ ግንኙነት በመግባባትና



የቆየው ቤተክርስቲያን



አዲስ የሚሠራው ህንጻ

በመተጋገዝ ላይ የተመሰረተ እንደሚሆን በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ አብራርተዋል።

በፕሮጀክቱ አተገባበር ዙሪያ ትልቁ እና ዋናው ችግር የመንገዱ ሁኔታ ነው። በተለይም ጎብኚዎች አካባቢውን ተመልክተው ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ፕሮጀክቱ አገራዊ በመሆኑ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ሳይቀር ሁኔታውን ተገንዝቦ በዚህ ታሪካዊ ፕሮጀክት ላይ አሻራውን እንዲያሳርፍም ይፈልጋል። በዚህ ረገድ አሁንም ቢሆን በአካል ተገኝተው ጉዳዩ የአንድ ዕምነት ብቻ ሳይሆን አገራዊ ጉዳይ በመሆኑ ‹‹አብረናችሁ ነን›› የሚሉ በርካታ የሙስሊሙ ማህበረሰብ መኖራቸውን በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ ያስረዳሉ። በመሆኑም ፕሮጀክቱ ብዙዎች የሚጎበኙት ታሪካዊና መንፈሳዊ ቦታ ነውና ጎብኚዎች እንዳይቸገሩ ጥርጊያ መንገዱ መሠራት ይኖርበታል። የመንገዶች መሠራት ደግሞ ለፕሮጀክቱ ዕውን መሆን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል የሚሉት በኩረ-ትጉሐን ጥበቡ፣ የአካባቢው ሕዝብ ደግሞ በመሰረተ ልማቱ ግንባታ ለመተባበር በጣም ፈቃደኛ በመሆኑ የክልሉም ሆነ የፌዴራል መንግሥት ትኩረት ሰጥተው ሊያግዙ እንደሚገባ ያሳስባሉ። የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማትም እንደ ዩኔስኮ ዓይነቶች ዕገዛ እና ድጋፍ የሚያደርጉበትን ሁኔታ መፍጠርም ተጨማሪ አማራጭ እንደሆነ ይገልፃሉ።

ፕሮጀክቱ አገራዊ በመሆኑ ሁሉን ኢትዮጵያዊ ይመለከተዋል በሚል እሳቤ በመነሳት ሚዲያው አቅዶ የማስተዋወቅ ሥራ ቢሠራ፤ የተሻለ ግንዛቤ ፈጥሮ ፕሮጀክቱ የህብረተሰቡን ሁለንተናዊ ድጋፍ እንዲያገኝ ቢያደርግ እና ሂደቱንም ቢከታተለው፤ በተለይም ትውልድና አገር ላይ የሚሠሩ የሚዲያ ተቋማት ሽፋን መስጠት ቢችሉ ውጤታማ የመሆን ዕድሉን ከፍተኛ እንደሚያደርገው በኩረ ትጉሐን ጥበቡ ያስገነዝባሉ።

አቶ ካሳሁን በፕሮጀክቱ ሥራ ላይ የወደፊት ተሳትፏቸውን ሲገልጹ፣ የፕሮጀክቱ ዕውን መሆን በዋናነት የሚጠቅመው የአካባቢውን ህብረተሰብ ስለሆነ በጉልበቱ፣ በገንዘቡ እና በእውቀቱ እንዲያግዝ የወረዳ፣ የዞን፣ የክልልና የፌዴራል መንግሥታትም የሚጠበቅባቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ የመጠየቅ፣ የማስተባበርና የመከታተል ሥራ የበለጠ አጠናክረን የምንሠራው ጉዳይ ነው ብለዋል።

በፕሮጀክቱ ግንባታ ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችን በተመለከተ አቶ ካሳሁን ሲያነሱ፣ የመጀመሪያው ጉዳይ የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ኮሚቴ ከታች ከቦታው ድረስ በመውረድ ሥራውን አለመከታተሉና እንቅስቃሴውን ቶሎ መሬት ላይ ማውረድ አለመቻሉ ነው ይላሉ። ከመንገድ መሰረተልማት ጋር በተያያዘም በየደረጃው የሚገኘው የገጠር መንገድ ባለሥልጣን ጽህፈት ቤት ትብብሩ አነስተኛ መሆኑን ይናገራሉ።

ደብረ ሃዊ ቅዱስ ያሬድ ገዳም የሚገኘው በዩኔስኮ በተመዘገበው በስመ ገናናው የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ ነው። ይህን ትልቅ የመስህብ ቦታ ደግሞ በርካታ ሰው ይጎበኘዋል። ጉብኝቱ የተሟላ መሆን እንዲችል ግን የገዳሙ ፕሮጀክት ዕውን መሆን የግድና አስፈላጊ ነው። መንግሥት አቅዶ ከሚተገብራቸው ፕሮጀክቶች በተጨማሪ በማህበረሰቡ ተሳትፎ ታቅዶ ይህን መሰል ፕሮጀክት ሲመጣ የሚመለከታቸው መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ተግባራት በባለቤትነት ስሜት መወጣት ይኖርባቸዋል።

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው “ቅርሶቻችን እንጠበቅ” በሚለው ርዕስ ሐምሌ 20 ቀን 2005 ዓ.ም በኢንተር ኮንትኔታል ሆቴል በተዘጋጀው የምክክር መድረክ ላይ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ የቅርስ ሀብት ከምችት በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ጥረት ብቻ አስፈላጊው ጥበቃና ቁጥጥር እየተደረገላቸው ለቀጣዩ ትውልድ ሊበቁ ይችላሉ የሚል እምነት እንደሌላቸው ገልጸዋል። ይልቁንም ቅርስ የሁሉም የአገሪቱ ሕዝብ ሀብት በመሆኑ፣ ሁሉም ዜጋ ጠብቆና ተንከባክቦ ለሚቀጥለው ትውልድ የማስተላለፍ የታሪክ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አስረድተዋል።

በረዳት ፕሮፌሰሩ እንደተገለጸው ግዴታና ኃላፊነት በመውሰድ በቅንነትና በበጎ አድራጎት ተግባር በመነሳሳት በኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ በቅዱስ ያሬድ ስም የተሰየመውን የደብረ ሃዊ ቅዱስ ያሬድ ገዳም በማህበረሰቡ ተሳትፎ እንዲጠበቅና እንዲታደስ የሚደረገው እንቅስቃሴ ይበል የሚያሰኝ ተግባር ነው። ገዳሙ ከርቀቱ፣ ከተፈጥሮ አቀማመጡ እና በመሰረተ ልማት አለመኖር ችግር ምክንያት ከስሙ በዘለለ ጥበቃና እንክብካቤ ተነፍጎት ቆይቷል። እዚህ ግባ የሚባል የማስተዋወቅና የማስጎብኘት ሥራ አልተሠራለትም። ይህን ትልቅ ታሪካዊ ቅርስና አገራዊ ሀብት፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ሳይለቅ እና ለጉብኝት አመቺ በሆነ መልኩ በማህበረሰቡ ሁለንተናዊ ተሳትፎ ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ በአዲስ መልክ ለመገንባት እየተደረገ ያለውን ጥረት ለማገዝ የአገሬን ልማት እወዳለሁ የሚል ዜጋ ሁሉ የበኩሉን ድርሻ በማበርከት ኃላፊነቱን ቢወጣ መልካም ነው እንላለን።

# ደምሴ ፅጌና ተመሳጣሪ ታሪኮች

ግርማ መንግሥቴ

ለሐገራችን የሥነ-ጽሑፍና የጋዜጠኝነት ሙያ ዕድገት ከፍተኛ አበርክቶዎችን ካደረጉት አንዱ ነው። የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ለሚሊኒየም ያሳተመው ልዩ አጀንዳ ላይ ሰፍሮ እንደሚገኘው፣ ደምሴ ፅጌ፡-

በአዲስ አበባ ከተማ ታኅሳስ ፳፩ (21) ቀን ፲፱፻፵፫ (1943) ዓ.ም. ተወለደ። ከ፲፱፻፶፪ (1952) ዓ.ም. ጀምሮ በስብስቴ ነጋሜ አንደኛ ደረጃ ት/ቤትና በሽመልስ ሀብቴ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተምሮ፣ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በ፩፱፻፷፫ (1963) ዓ.ም አጠናቀቀ። ከዚያም በመምህርነት ሙያ ሠልጥኖ ዲፕሎማ ካገኘ በኋላ በአ.አ. ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ- ጽሑፍ ክፍል በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቋል።

ደምሴ ጽጌ የተለያዩ ወጥና ትርጉም ሥራዎችን አሳትሞ ለአንባቢያን ያቀረበ ሲሆን፣ ከሥራዎቹ መካከልም "ፍለጋ"፣ "ምትሀት"፤ ከትርጉም ሥራዎቹ ደግሞ የጀምስ ሀድሌይ ቼዝን "ትንግርት" በሚልና፤ ከባሴ ሀብቴ ጋር በመሆን "ጠብታ ማር"ን አሳትመዋል። እንዲሁም "ጭጋግና ጠል" በሚል ርዕስ በታተመ መድበል ውስጥ ከሌሎች ደራስያን ጋር በጋራ ሥራዎቹን አቅርቧል። ጥበቡ በለጠ በፌስቡክ ገፁ (ፌብ. 7 2017) ላይ እንዲህ ይለናል፤

ዓለም ብዙውን ጊዜ በግርምት ውስጥ ነች፤ መውጫና መግቢያዋ አይታወቅም። በትንሽ ዓመታት ርቀት ላይ አብረውን የነበሩ ሰዎች በአፀደ ሥጋ እንደዋዛ ተለይተውን ሲያልፉ እናያለን። ለምሳሌ በ1985 ዓ.ም ኢትዮጵያዊ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን፣ ደራሲ መስፍን አለማየሁ እና ደራሲና ጋዜጠኛ ደምሴ ፅጌ አንድ ላይ ያወጉ ነበር።

በተለይ መስፍን አለማየሁና ደምሴ ፅጌ፣ ፀጋዬ ገ/መድህንን ቃለ-መጠይቅ አድርገውለት ነበር። እነዚህ ሶስት ሰዎች በብዙ ነገሮች ዙሪያ ቁጭ ብለው ይፈላሰፉ ነበር። ዛሬ ግን ሶስቱም የሉም። ሶስቱም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት፣ ይህን የጋራ ጨዋታቸውን ባካሔዱ በ15 ዓመታት ጊዜያት ውስጥ ነው። ሶስቱም ዛሬ ባይኖሩም በመስከረም ወር በ1985 ዓ.ም "ለዛ" ብለው በሚጠሩት መጽሔታቸው ላይ ያወጉትን አጠር አድርጌ ላቅርብላችሁ። (የጥበቡን መልእክት ከፌስቡክ ገጹ ላይ መመልከት ይቻላል። )

ከላይ ከጥበቡ ገጽ ላይ የወሰድነው ቅንጫቢ ስለ "ለዛ" ከማስታወስም ባለፈ የደምሴን ውሎና ማንነት ያሳየን ዘንድ ነውና ወደ ሌላው እንለፍ። (በነገራችን ላይ "ለዛ" ተወዳጅ የኪነጥበብ፣ በተለይም በሥነ-ጽሑፍና ፍልስፍና ላይ የምታተኩር መጽሔት ነበረች። ምን ያደርጋል፣ ያለ ጊዜዋ ተወልዳ፣ ወቅቱ የተጋጋለ ፖለቲካ እንጂ ጥበብና ፍልስፍና የሚጣጣሙበት ባለመሆኑ፣ ባጭር ቀረች። )

ከዚሁ ሳንርቅ ሌላም ሰው ዋቢ አድርገን ስለ ደምሴና ዘመነኞቹ ትንሽ እንበል።

የአውግቸው ተረፈ (ህሩይ ሚናስ)ን ህልፈት ተከትሎ የቅርብ ጓደኛው የሆነውና ስለ እሱም የጻፈው ተሾመ ብርሃኑ ከማል፡-

"ያኔ እነ ጋሽ ስብሐት፣ ደምሴ ፅጌ፣ የሺጥላ ኮከብ፣ ባሴ ሀብቴ ሰሞነኛ ስለነበሩ ህሩይ [አውግቸው ተረፈ]ም አድናቆትና ክብርን አግኝቶ ስሙ ጎላ ብሎ መጠራት ጀመረ።

"እያስመዘገብኩ ነው" የተሰኘው አጭር ልቦለድ ታሪኩ፣ " ዕብዱና ሌሎች"ም በሬዲዮ በተደጋጋሚ ቀረቡ። በአሮጌ መጻሕፍት ሻጭነቱ የማውቀው ህሩይ ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ ማለቱ አስደሰተኝ። ወዳጅነታችን ቀጠለ። " የደምሴ ዘመነኞች (contemporaries) እነማ እንደ ነበሩ ብቻ ሳይሆን ስለ አዋዋላቸው፣ ስራና ተግባራቸውም የሚነግረን ብዙ ታሪክ በጉያው ሸሽጎ እናገኘዋለን።

## የደምሴ ውለታና የመዘንጋቱ ጥግ

የፈረንሳይ ለጋሲዎኑ አቶ ጌታቸው ሽፈራው "በኢህአፓ ስሙ 'አቢ' በተአምር ከተረፉ እና ለረጅም እስር ከተዳረጉ ወገኖች አንዱ ሲሆን፣ ለ"የቀይ ሽብር" መታሠቢያ ህውልት ቤተ-መጻሕፍትን በልገሳ በተገኙ መጻሕፍቶች በመሙላት እና የለጋሾቹን ፎቶ ግራፍ በቤተ-መጻሕፍቱ በማኖር እንዲዘከሩ እና ውለታቸው እንዲጋባ በማድረጉ ይታወሳል።

ከእነዚህ ለጋሽ ዜጎች መካከል ጋዜጠኛ ደምሴ ፅጌ አንዱ ሲሆን፣ ደምሴ የለገሳቸው መጻሕፍት በጣም በርካታ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፤ በተለይ አንዳንድ የፍልስፍና መጻሕፍቶቹን ሌላ ስፍራ ለማግኘት የማይቻሉ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል" የሚለው ስለ ደምሴ የሚናገረው ነገር መኖሩ ብቻ ሳይሆን፤ የደምሴን ኑዛዜና የመጻሕፍቱ ወደ ተጠቀሰው ተቋም ያደረጉትን ጉዞና የርክክብ ስነስርአቱን በቅርብ የምናውቅ ሰዎችን ትዝታ መቀስቀሱም ልዩ ያደርገዋል።

እዚህ ላይ አንድ የሚያሳዝን አቢይ ጉዳይ ቢኖር፣ ሀብታሙ ሽፈራው የሚባሉ (የቤተመጻሕፍቱ



አደራጅ ይመስሉኛል) "የጌታቸው ሽፈራውን (አቢ) እና የደምሴ ፅጌን ፎቶ የሚልክልኝ ባገኝ ደስ ይለኛል። " በማለት በማህበራዊ ድረ-ገጻቸው ላይ ለንባብ ያበቁት። ደምሴ በዚህ ደረጃ ነው እንግዲህ የተዘነጋው።

( የ www.EthiopianWriters.com አስተናባሪዎችስ ምነው ደምሴን ዘለሉት እሳ፤ ይቅርታ ረሱት ለማለት ነው። )

## ደራሲው ደምሴ ፅጌ

ደምሴ ፅጌ እንደምናውቀውም፣ በብዙዎች እንደተመሰከረለትም (አነጋጋሪነቱ እንዳለ ሆኖ) ሁለገብ ነው። ያነባል፤ ይጽፋል፤ ያድታል (ኤዲቲንግ)፤ ያሄሳል። ጋዜጠኛ ነው። ደራሲና ገጣሚም ነው። የጋዜጠኝነቱን በኋላ የምናየው ሆኖ በደራሲነት ሙያው ካፈራቸው መካከል አንዱ በሆነው በ"ምትሀት" የአጫጭር ልቦለዶች መድበል "ለውድ አንባቢያን" በሚል ስር፣ ከማውጫው በፊት ያሰፈረውን እንዳለ ወስደን የትህትናውን ጥግ እንመልከተው።

አንዳንዴ ሳስበው አጭር ልቦለድ የሰነፍ ጸሐፊዎች ሥራ ይመስለኛል። ሌላ ጊዜ ሳስበው ደግሞ እንዴት ተደርጎ ይለኛል ሀሳቤ ራሱ። እነቼሆቭን፣ እነሄሚንግዌይን፣ እነሞምን፣ እነስብሃትን፣ እነአዳም ረታን እንዴት ሰነፍ ትላቸዋለህ? ይለኛል። እናም እጠራጠራለሁ።

እኔ ግን ሰነፍ ነኝ። ስለዚህም በዚህች ትንሽ መድ[በ]ል ... ውስጥ የሰነፍ ስራዎችን ነው እማቀርብላችሁ። ልቤ ግን ይመኛል። አንድ ሶስት አራት ረጃጅም ልቦለዶችን ቢያበረክትላችሁ እንዴት ደስ ባለው! ምን ያደርጋል ረጅም ልቦለድ ባንድ ቁጭታ ወይም ባንድና በሁለት አመት፣ ተጨንቆ አምጦ መውለድ። የኔ ነፍስ ፍላጎቱ ቢኖራትም ይህን ማድረግ አልቻለችም።

እስከዚያው እነኝህን ለበርካታ አመታት

የተጠራቀሙ አጫጭር ልቦለዶችን ላበረክትላችሁ ፈቀድኩ። አንድ ነገር እናገኝባቸዋለን ካላችሁ አንብቧቸው። ቢያንስ ቢያንስ በሀበሻ ምድር ሞልቶ የተትረፈረፈውን ጊዜ ትገድሉባቸዋላችሁ። በቃ ከዚህ በላይ ምን ልበላችሁ። አዎ ይብቃ ...!

ይህች ነች እንግዲህ ደምሴ ብዙ መልእክቶችን ያስተላለፈባት "መግቢያ" (መግቢያ ያልኩት እኔ ነኝ)። ከመልእክቶቹም አንዱ "ትህትናው" ነው። "ሰነፍ ነኝ" ማለቱና እንዴት በአገሪቱ የመጀመሪያ የሆነውን ስራውን ያካተተ ስራ (በአይነቱ Postcard story ለመባል እንኳን የማይበቃውን (250 ቃላት እንኳን ስለማይሞላ) እና በጣም አጭር ልቦለድ፣ "የማይሞተው ፍቅር"ን) ሰርቶ "ሰነፍ ነኝ" ይለናል የሚል የአንባቢያንን ጥያቄ ማስነሳቱ ነው። እንዲሁም፣ ደምሴ የእነማን አድናቂና ተከታይ እንደ ሆነ እናውቅ ዘንድ እድሉን መፍጠሩ ሲሆን፣ ማህበራዊ ሂያሲነቱም ("ቢያንስ ቢያንስ በሀበሻ ምድር ሞልቶ የተትረፈረፈውን ጊዜ ትገድሉባቸዋላችሁ። " ማለቱን ልብ ይሏል) እንዲሁ አስደንጋጭ ነው። "በቃ ከዚህ በላይ ምን ልበላችሁ። አዎ ይብቃ ...!"

ያለውም ሌላው አስፈሪና አስደንጋጭ የመውጫ ሀሳቡ ነውና እዚህ ስናመጣለት ዝም ብለን አይደለም ማለታችን ነው።

በሌሎች ስራዎችም እንዲሁ ነውና "እራሱን ችሎ የሚቆም" የተባለለትንም "ፍለጋ" ረጅም ልቦለድ በዚሁ አይን በመመርመር አንዳች የደምሴ ሰብእና ማያ መሳሪያ ላይ መድረስ ይቻላል ማለት ነው። (በነገራችን ላይ፣ በወቅቱ "ፍለጋ"ን ያላነበበ ሰው አለ ለማለት የሚያስቸግር ሲሆን፤ ለዚህም አንድ የነቀምት ከተማ ቤተመጻህፍት ተጠቃሚ፦—

በወቅቱ አብዛኛውን ጊዜዬን ያሳለፍኩትም በከተማዋ እምብርት ላይ በምትገኘው የህዝብ ቤተ-መጻህፍት ነበር። ምንም እንኳን ያን ያክል ሰፊ የምትባል ባትሆንም በውስጧ በርከት ያሉ መጻሕፍትን አጭቃ የያዘች፤ ምጥን ቤተመጻሕፍት እንደነበረች አስታሰውሳለሁ። በዚህች ቤት ካነበብኳቸዉ መጻሕፍት መካከል ህያዉ ፍቅር (በደረጀ በቀለ)፣ ፍለጋ (በደምሴ ፅጌ)፣ ሀዲስ (በዓሉ ግርማ) ዛሬም ድረስ ትውስ ይሉኛል። በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬም የእነዚህ መጻሕፍት ስም በተጠራ ቁጥር ይህችኑ የነቀምቴ ከተማ የሕዝብ ቤተመጻሕፍትንም አብሬ ሳስታውስ ነበር።

በማለት ያሰፈሯትን ማንሳቱ በቂ ይሆናል።

እኚሁ የአሁኑ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ መምህር የቤተ-መጻሕፍቷንም የመጨረሻ እጣ ፈንታን አስመልክተውም፦—

ቤተ መጻሕፍቷ በር ላይ እንደደረስኩ ቀልቤን የገፈፈኝን ባነር ተመለከትኩ። ከ'ኔ ቁመት በእጥፍ የሚበልጥ "የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ" ጠርሙስ በቢጫ ቀለም ተውቦ በሩ ላይ ተገትሯል። ለትንሽ ደቂቃ በድንጋጤ ካለሁበት ቆሜ ጠርሙሱን አፈጠጥኩበት። አይኖቼን ወደ ግቢው ሳማትር ሰዎች መጻሕፍት ሲያነቡ ሳይሆን የቢራ ጠርሙሶችንና ጃምቦዎችን እያጋጩ ሲሳሳቁ አየሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በሚመላለስበት በዚያን ወቅት መቅደሱን የንግድ መናኸሪያ አድርገው ያገኛቸውን እርግብ ሻጮች "የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት!" ያለው ቃል ትውስ አለኝ። [...] አሁን "ይሄ መጠጥ ቤት እኮ የዱሮው የነቀምት ከተማ የሕዝብ ቤተመጻሕፍት ነበር። " ብሎ ታሪክ መናገር ምንኛ ይቀፋል?

ያሉትንም እንደ ሀገርና የእውቀት አምባ ድርቅ መመታት እዚህ ልንጠቅስላቸው ግድ ይሆናል። (እኛም፣ እዚህ አዲስ አበባ ያሉትንና የነቀምቴዋን ቤተመጻሕፍት አይነት እጣ ፈንታ የደረሳቸውንም አንድ ቀን እንዘረዝራቸዋለን ብለን እናስባለን። )

## አርታኢና ሃያሲው ደምሴ ፅጌ

የአሁኑ ዘመን አንባቢያን በሚገባ እንደምናውቀው፣ ጋሽ ስብሀትም ወደ አሁኑ ዘመን አንባቢያን ልብ ውስጥ ከገባባቸው አንዱ ስራው፣ ታግዶ በነበረውና በእነ ደምሴ ፅጌ የአርትኦት ስራ ታሽቶና ለዝቦ ለአንባቢያን በቀረበው "ትኩሳት" ስራው ሲሆን፤ በወቅቱም አስተያየት ሰጪዎች፣

ጋሽ ስብሀት ገብረ እግዚአብሄር በ60ዎቹ ሶስት ተፈጥሮአዊ ልብወለዶችን ጽፏል — ሌቱም አይነጋልኝ፣ ትኩሳት፣ እና ሰባተኛው መልአክ። ያውም በ60ዎቹ፣ ያውም ኢትዮጵያ ውስጥ፤ ስብሐት እንደማይታተሙ ያውቅ ነበር። ግን ለገዛ ስሜቱ ጻፈው። ጊዜ አለፈ። አዲስ ቀን መጣ። በ90ዎቹ ደምሴ ፅጌና ጥቂት የስብሐት ጓደኞች ሶስቱን ልብ ወለዶች አለዘቧቸው። በተለይ ትኩሳትን የሚቆረጠውን ቆርጠው የሚተወውን ትተው አሳታሙቱ። ስብሐት በሕይወት ዘመኑ ይታተማል የሚል እምነት አልነበረውም። በልጅ ልጆቹ ዘመን ታትሞ ጥቂት ፍራንክ ያገኙበታል የሚል እምነት ግን ነበረው። ይሁን እንጂ፣ እሱ ራሱ በህይወት እያለ ለዝቦ ታተመ። በማለት ማስፈራቸው ይታወሳል። ደምሴ ሁለገብ ሰብእና የነበረው ሰው ነበር ማለት ነው።

ወደ ሃያሲነቱ ደግሞ እንምጣ፡- በአንድ ወቅት፣ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ፍልስፍና አምድ ስር "የሥነ ግጥማችን አሁናዊ ይዞታ" በሚል ርእስ ስር ባወጣነው ጽሑፍ ውስጥ የጠቀስነውን ሀሳብ ዛሬ እዚህ መድገሙ ግዴታ ይሆናል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "ቁም ነገር" (ቅ.7፣ ቁ.18) ጠቅሰን አስፍረነው የነበረው የደራሲና ጋዜጠኛ ደምሴ ሀሳብ (ሂስ) "ሥነ ጽሑፋችንን ከየት የወረደ ዳፍንት ነው አፍኖ የያዘው?" በሚል ርእስ ያቀረበው ሲሆን፤ በሰጠው በሳልና የሰላ ሂስም የዘመኑን ግጥምና ገጣሚያን እንደሚከተለው ይሸነቁጣቸዋል፤

ሥነጽሑፋችን በተለይም ሥነግጥማችን ቀጭጯል፣ ደቋል፣ ተጨባጭ የጥበብ ወለላ የለውም፣ ህትመታቸው አንሶ አንሶ 200 ጠርዝ ላይ ደርሷል፤ ለመሸጥ ("መ" ይጠብቃል) አልቻሉም፤ በቁጥር እንጂ በጥበብ ወድቀዋል፤ ማንነት የላቸውም፤ አብዛኞቹ የቃላት ክምር (ድድር) እንጂ ግጥም ሊያሰኝ የሚችል ብቃት የላቸውም። የሚነግሩን አዲስ ነገር፣ የሚያሳዩን ውበት የላቸውም፤ የሚነበቡ አይደሉም፣ ቢነበቡም የመታወስ ብቃት የላቸውም። ድንቅነታቸው በደራሲዎቻቸውና ለውሽታም አድናቂዎቻቸው ብቻ ነው ....

(እያለ ይቀጥላል)።

ገጣሚያኑን በተመለከተም፤ "አያነቡም [ዮሀንስ አድማሱም በ1961 "ደራስያኑ የሚያነቡ አይመስልም። " ማለቱን ልብ ይሏል]፣ አይመራመሩም፣ ቀደምት ስራዎችን አይፈትሹም፣ የእለት ተእለት ገጠመኞቻቸውን ገልባጮች ናቸው። እርስ በ'ርስ ይገለባበጣሉ፤ [ይዘራረፋሉም]። የውጪ ስራዎችን አያነቡም፤ ያለማንበብ ደዌ ተጠናውቷቸዋል። የንባብ ጉድለት የጥበብ ጉድለት እንደሚያስከትል አያውቁም ...." ሲል ያሄሳቸዋል። መፍትሄውም እነዚህን ድክመቶችና ህፀፆች ማሻሻል መሆኑን በአፅንኦት ያሳስባል።

## ተርጓሚው ደምሴ

One of the internationally best-selling authors; one of the best known thriller writers of all time. ተብሎ የተመሰከረለትን፣ ከ50 በላይ መጻሕፍቱ ወደ ፊልም የተቀየሩለትን፣ በCrime fiction, mystery, thriller, detective ዘውጎች አጻጻፍ በከፍተኛ ደረጃ እውቅናን ያገኘው፣ Golden Age of Detective Fiction በሚል መገለጫ በሚታወቀው የሥነጽሑፍ ንቅናቄ (Literary movement) ዘመን የነበረውን፣ የደራሲ ጀምስ ሃድሌይ (James Hadley Chase, 24 ዲሴምበር 1906 — 6 ፌብሩወሪ 1985) ተወዳጅ ልቦለድ ትርጉም በደምሴ አማካኝነት "ትንግርት" (የህትመት ዘመን - 1982 ዐ.ል) በሚል ርእስ ወደ አገራችን የተሻገረ ሲሆን፣ ልክ እንደ ዋናው ደራሲ ሁሉ ደምሴም ከአንባቢያኑ ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትን አትርፎበታል። መጽሐፉም እስካሁን ድረስ በከፍተኛ ደረጃ እንደተወደደና ተነበበ ይገኛል።

በታዋቂውና የቢዝነስ መምህር በነበረው ዴል ካርኒንጌ (Dale Breckenridge Carnegie) የተጻፈውን፣ እስካሁንም አብዝቶ ከመጠቀስ ያልቦዘነውና (አነቃቂ መጽሐፍ "Inspirational Book" በመሆኑ የሚታወቀውን) ድንቅ "ራስህን ሁን" መጽሐፍ ከደራሲና ተርጓሚ ባሴ ሀብቴ ጋር በመሆን "ጠብታ ማር" በሚል ርእስ ለህትመት አብቅተዋል። ይህ ስራቸው እስካሁንም ከገበያ ላይ አልወረደም፤ የመነበብ እድሉም እየጨመረ እንጂ ሲቀንስ አልታየም።

## ከ"ጠብታ ማር"

መጽሐፉ ራስን ስለ መሆን፤ ራስን ፈልጎ ስለ ማግኘት

ነው። ሀያሲያን እንደሚሉት፣ ለመጽሐፉ ዘመን ተሻጋሪነቱ ምንጩ ወይም ምክንያቱ አነቃቂነቱ ሲሆን፤ በስነልቦና ዘርፍ ”ኢንስፓይሬሽናል ቡክ” ለመባሉም ምክንያቱ ይሄው ነው።

የሚከተሉት በብዙዎች ከመጽሐፉ በተጠቃሽ ጥቅስነት የሚጠቀሱ ናቸውና እንመልከታቸው።

[...] ራስህን ፈልግና ራስህን ሁን፤ አስታውስ፣ አንተን የሚመስል በምድር ላይ ማንም የለም። ራስህን ሁን። ራስህንም እወቅ። በህይወት ስትኖር ራስህን ካወቅህ አሸናፊ ትሆናለህ። ሌሎችን ለማስደሰት የራስህን ደስታ ማጣት የለብህም። በሌሎች ሰዎች ዘንድ ብንወደድ መልካም ነው። ሌሎች ሃሳባችንን ቢቀበሉልን፣ መንገዳችንን ቢደግፉልን፣ ፍላጎታችን ፍላጎታቸው ቢሆን እሰየው። ነገር ግን የሌሎችን አትኩሮት እና እይታን ስንፈልግ እስከመቼ መንገዳችንን እንስታለን? ሌሎች እንዲወዱን ስንል ህሊናችንን እንሸጣለን? ሌሎች እንዲያዩን ስንል ያለቦታችን እንቆማል? ከብዙሃኑ ጋር ለመቀላቀል ስንል ማንነታችንን እንለውጣለን? ልዩ መሆን ለምን ይሆን የሚያስፈራን? የራስን መንገድ መርጦ፤ የራስን ማንነት ይዞ፤ የራስን አስተሳሰብ መሪ አድርጎ መኖር ለምን ይሆን ለብዙዎቻችን የሚከብደን? እንደሚመስለኝ የብዙዎቻችን ችግር እንደ ሌላው ለመኖር ስለምንጥር ነው። ሌሎች የሄዱበት መንገድ ብቻ ትክክለኛው መንገድ ስለሚመስለን፤ ሜዳው ሁሉ መንገድ መሆን እየቻለ አንዲት ቀጭን መስመር ላይ እየተጋፋን ጊዜያችንን እያባከንን ነው። ራስህን ፈልግና ራስህን ሁን። አስታውስ አንተን የሚመስል በምድር ላይ ማንም የለም።

”የዴል ካርኒጌ ’ጠብታ ማር’ን - ይቅመሱ!” በሚል ርእስም ጌጡ የሚከተለውን አስፍሮ (ጠቅሶ) እናገኘዋለን።

ለምሳሌ ልጅህ ሲጋራ እንዳያጨስ ብትፈልግ ስለ ሲጋራ መጥፎነት አትስበክለት። ሆኖም ሲጋራ ማጨስ የአንድ እግር ኳስ ክለብ ተጫዋች እንዳይሆን ወይም በሩጫ ውድድር እንዲሸነፍ የሚያደርገው መሆኑን ንገረው።

የሌላውን ፍላጎት የመጠበቅ ነገር ከማንኛውም ነገር ጋር ማለትም ከሕጻናት ወይም ከጥጃ ወይም ከዝንጀሮ ጋር በምናደርገው ግንኙነት ሁሉ ሊታሰብበት የሚገባ ነገር ነው። ለምሳሌ ራልፍ ዋልዶ ኤመርሰንና ልጁ አንድ ቀን አንድ ጥጃ ወደ ጋጥ ለማስገባት ሞከሩ። ሆኖም፣ አብዛኛው ሰው የሚፈፅመውን ስህተት ፈፀሙ። እነሱ የሚፈልጉትን እንጂ ጥጃው የሚፈልገውን አላደረጉም። ኤመርሰን ከኋላ ወድሮ እምቢ አለ። ይህን ከንቱ ጥረቱን ታይ የነበረችው ሠራተኛ ጥጃው ምን እንደፈለገ ገባት።

ጠጋ አለችና ጣቷን በዘዴ ለጥጃው አጎረሰችው። ጥጃው ጣቷን መጥባት ሲጀምር ቀስ ብላ ወደ ጋጡ እየተራመደች ይዛው ገባች። ሠራተኛው ምንም እንኳን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ባይኖራትም በዚያች ወቅት ከኤመርሰን የበለጠ ማስተዋል ችላ ነበር።

**ከዕለታት በአንዱ ቀን እንዲህ ሆነ። ፀሀይና ንፋስ እኔ ነኝ ሃይለኛ፤ እኔ ነኝ ሃይለኛ በመባባል ተፎካከሩ። ነፋሱ ፀሀይንም አላት፤ ሃይለኝነቴን በተግባር አሳይሻለው። ...**

ከተወለድክ ጀምሮ ያደረግካቸውን ለምሳሌ ለቀይ መስቀል ማኅበር 100 ብር የሰጠህበት ጊዜ ቢኖር እንኳን ሌላውን ከመውደድ የመነጨ በጎ ሥራ ለመሥራት ስለፈለግህ ነው። ከመርዳት ፍላጎትህ ይልቅ የብር ፍላጎትህ ቢያይልብህ መቶ ብሩን ባልሰጠህ ነበር። እርግጥ አስተዋጽኦው እንድታደርግ የጠየቀህ ሰው እምቢ የማትለው ሆኖ ሊሆን ይችላል። ሆኖም አንድ እውነት አለ። ብሩን የሰጠኸው ምናልባት ከሰውየው አንድ የፈለግከው ነገር ስለነበረ ነው።

እንዲሁም፣

“ጠብታ ማር” (1981 ዓ.ም) በዴል ካርንጌ የተፃፈች፤ ደምሴ ፅጌና ባሴ ሀብቴ ግሩም በሚባል ሁኔታ ወደ አማርኛ የመለሷት ሸጋ መጽሐፍ ናት። እነሆ ከዚህች በቁም ነገር ከተሞላች መጽሐፍ ለዛሬ አንድ ቁም ነገር እንቆንጥር። ” የሚልን አስተያየታዊ መግቢያን ተከትሎ ደግሞ፤

ከዕለታት በአንዱ ቀን እንዲህ ሆነ። ፀሀይና ንፋስ እኔ ነኝ ሃይለኛ፤ እኔ ነኝ ሃይለኛ በመባባል ተፎካከሩ። ነፋሱ ፀሀይንም አላት፤ ሃይለኝነቴን በተግባር አሳይሻለው። “እዚያ ታች ካፖርት የለበሰው አዛውንት ይታይሻል? አንቺ ካፖርቱን ለማስወለቅ ግማሽ ሰአት ሲወስድብሽ እኔ ግን በአምስት ደቂቃ ውስጥ አስወልቀዋለው አላት። ”

ፀሀይ በደመና ተጋረደች። ነፋሱ፤ አውሎ ነፋስ እስኪሆን አቧራውን እያጨሰ ነፈሰ። ሃይሉ በጨመረ ቁጥር አዛውንቱ ካፖርታቸውን ይበልጥ ጥብቅ አድርገው ያዙ። ነፋሱ መረታቱን ሲያውቅ ፀጥ አለ።

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ወዲያውኑ ፀሀይ ብቅ አለችና ሞቅ ያለ ፈገግታዋን አዛውንቱ ላይ ፈነጠቀችባቸው። በዚህ ደስታ የተዋጡት አዛውንት ላባቸውን ጠረግ ጠረግ አረጉና ካፖርታቸውን አወለቁ። ይህንን ያየችው ፀሀይ ወደ ንፋሱ ዞር ብላ፤ “አየኸው ከሃይልና ጩከት ይልቅ፤ ፍቅርና ትህትና ጠንካራ ናቸው” አለችው።

ጠብታ ማር ይሄንን ያህል ጣፋጭና ተወዳጅም ሲሆን፤ ተርጓሚዎቹም ከወላጁ ደራሲ ካርኒጌ ባልተናነሰ ባለ ውለታዎቻችን ናቸው ማለት ነው።

## ዋና አዘጋጁ ደምሴ

ደምሴ የሕይወት ዘመኑን ሙሉ ያሳለፈው ከብዕርና ወረቀት ጋር ሲሆን፣ በሙያውም በጋዜጠኝነትና በደራሲነት፤ እንዲሁም፣ በሃያሲነት ዘርፎች ነበር።

”መጀመሪያ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ነበር የሰጠሁት ’ይሄን አሉባልታሽን አትሜ እራሴ ላይ ጣጣ አላመጣም’ አለኝ ደምሴ ፅጌ። ወስጄ ለኔሽን [ጋዜጣ] ሰጠሁ። ወጣ። ” (ስንዱ አበበ)። ስንዱ ምንም እንኳን ወቀሳዋ የሱን ሃላፊነት ያላገናዘበ፣ የግሉ ጋዜጣ ከሜንስትሪም ሚዲያ የሚለይበትን ሰፊ መስመር የዘነጋ . . . ቢሆንም፣ እንደ አንባቢ ስንመለከተው ደምሴ ምን ያህል ጥብቅ ሰው እንደ ነበር ያሳስበናል።

ከስራ ውጪ በአብዛኛው ውሎው ከእነ ስብሃት፣ ሡራፌል፣ ሥዩም፣ መስፍን ሀብተማሪያም ጋር የሆነውና ካፌ (ለምሳሌ፣ ሲቲሆል ሻይ ቤት (ማክሲም)) ሳይቀር የድርሰትና አባዜዋ ክርክርን የሚያጧጡፈው ደምሴን ምንም እንኳን ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ (ያው ራሱ ጋዜጣውም ታሪካዊ ነውና) ዋና አዘጋጅነቱ ጋር አያይዘን ነጥቦችን እናንሳ እንጂ፣ በበርካታ መጽሔቶች ላይ አሻራውን ያሳረፈ የተዋጣለት የብዕር ገበሬ ነበር።

የደምሴን ጋዜጠኝነት ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፤ በተለይም ከአዲስ ዘመን ጋር አያይዘን ስናነሳ ግን ”ደምሴ ለአዲስ ዘመን ሁሉ ነገሩ ነው። ጊዜና ገንዘቡን ብቻ ሳይሆን ሁሉ ነገሩን ለጋዜጣውና ”ዘመን መጽሔት” የሰጠ፤ አሻራውንም አሳርፎ ያለፈ ባለሙያ ነበር። ለምሳሌ ያህልም የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ”ርእሰ አንቀፅ” እንደ ደምሴ ጽጌ የዋና አዘጋጅነት ዘመን ተሳክቶለትም፣ ተዋጥቶለትም፣ አንባቢም አግኝቶ፤ ተነባቢም ሆኖ አያውቅም። የእሁድ ዕትሙ ”ዕለተ ሰንበት”ም ደምሴ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍሎለት የነበረ ተወዳጅ አምድ ነበር። ” የሚሉ አስተያየቶችን ሳንጠቅስ ማለፉ ተገቢ ስለማይሆን መጥቀስን መርጠናል።

የደምሴን የጋዜጠኝነት ሕይወትና ያጋጠመውን ፈተና አስመልክተው ማርች 11 2020 ለአንባቢ ሀሳባቸውን ያካፈሉት፣ ክብሩ (Kibru BookStore) የተባሉ ሰው (ደምሴን በቅርብ የሚያውቁት ይመስላሉ) ”ደምሴ ፅጌ፣ ነፃነት አስፋውና መለስ ዜናዊ” በሚል ርእስ ስር፤

ወደ አዲስ ዘመን ጋዜጣ በሀላፊነት ከመጣ በኋላ ብዙም የተመቸው አይመስልም ነበር። የስኳር በሽታንም የተዋወቀው አዲስ ዘመን ሲሰራ ነበር። “ማንበብ ብዙ ቀንሻለሁ። ቋንቋዬም የጋዜጣ ሆነ። ” ብሎ ወደ ኋላ ተመልሶ የቀድሞዎቹን የአማርኛ መጻሕፍትን ማንበብ ጀምሮ ነበር፤ አንጋፈው

መምህር፣ ደራሲና ጋዜጠኛ ደምሴ ፅጌ።

አንድ ወቅት ለአዲስ ዘመን መጽሔት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ቃለመጠይቅ ማቅረብ ፈለገ። ጉዳዩን ለነፃነት ነገራት፤ ምንም አልተቸገረም። ቃለመጠይቁን አመቻቸችለት። በተባለው ቦታና ሰዓት ተገኝቶ የሀገሪቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ቃለመጠይቅ አደረገላቸው። ደስ ብሎት ቃለመጠይቁን ይዞ ተመለሰ።

ቃለመጠይቁ መሰረት ያደረገ የመጽሔቱ ማስታወቂያ ተላለፈ። ደምሴም ለዘመን መጽሔት በሚሆን መልኩ ለማዘጋጀት መቅረፀ-ድምፁን ማጫወት ጀመረ። ያልጠበቀው ታሪክ ተከሰተ። ለካንስ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ድምፅ አልተቀረፀም። የሆነውን ማመን አልቻለም። ማስታወቂያው አስቀድሞ ሄዷል። አንባቢ ይጠብቃል። እናም ነፃነት ጋር ደወለ የሆነውን አጫወታት። የጉዳዩ ክብደት ያስጨነቀው ደምሴ ባጋጠመው ክፉ አጋጣሚ የተገረመችው የነፃነት ሳቅ መስማቴ ነገሩን ትንሽ ቀለለኝ አለ።

ለሁለተኛ ጊዜ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ለቃለመጠይቅ እድሉን አመቻቸችለት። የዛን እለት ግን የደምሴን መቅረፀድምፅን ለብቻው አለቀቀችውም ሲጀምር መስራቱን ሲጨርስ መቀረፁን አድምጣ ለደምሴ መለሰችለት። ደምሴ የእለቱን ሁኔታ ሲናገር ”የሚገርመው” አለ ”ስንለያይ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆኑ ነፃነት ሞቅ ባለ ሰላምታና ፈገግታ ሸኙተውኛል። ”

## ለሶስቱም ነፍስ ይማር።

## የመጀመሪያው ደምሴ

“ደራሲ የሌለው አገር ከዘመኑ የባሰ ጨለማ ነው” በሚል አስተያየቱ፤ እንዲሁም፣ የጋሽ ስብሀትን “ድርሰት የሚመጣልህ ስትደናበር ነው!” አባባል በማንሳት የሚታወቀው ደምሴ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ተገቢውን ስፍራ የያዘ ደራሲ ሲሆን፣ አንዱም በእስካሁኑ የሥነ ጽሑፍ ታሪካችን ያልነበረን እንዲኖር ማድረጉ ነው። በ”ምትሀት” (ገጽ 179፣ 1995 ዓ.ም) ውስጥ ከተካተቱ ስራዎቹ አንዱ ”የማይሞተው ፍቅር” በሚል ርእስ የቀረበው በጣም አጭር (tiny story፣ ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ስለ ”flash fiction”ንም እዚሁ ጋ ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል)፤ በአስተያየት ሰጪዎች አማካኝነት ለPostcard Stories ደራዋ Jan Carson short enough to fit on a postcard and is very readable--funny and poignant የሚል የባለሙያዎች አስተያየት እንደተሰጣት ሁሉ፤ ለደምሴም ይሄው አይነት አስተያየት ሊሰጠው የሚገባ ልቦለድ ሲሆን፤ ሙሉ ታሪኩም፡-

ተገዳ ስትዳር የዘጠኝ አመት ጨቅላ ነበረች። አስራ ሰባት ሲሞላት ነው ፍቅር ልቧን የዳሰሰው።

አፈቀረችው፤ አፈቀራት። አወቀችው፤ አወቃት። አንድ ቀን ውሃ ልትቀዳ ወንዝ ወርዳ ከፍቅረኛዋ ጋር እጥፋው ውስጥ ወደቀች።

“ባልየው” ወሬ ሰማ፤ ሽጉጡን ታጥቆ ተንደረደረ።

ተዋህደው እንደተኙ ደረሰባቸው።

ተኮሰ፣ እሷን ገደላት። ተኮሰ፣ ፍቅረኛዋን ገደለ፤

ተኮሰ፣ ራሱንም ገደለ።

የማይሞተው ፍቅር ግን ከሶስቱም ልብ ውስጥ ወጥቶ ሌላ ጉብል ፍለጋ፤ ሌላ ጎልማሳ ፍለጋ እያዘነ ገሰገሰ።

የሚል ነው። በቃ፣ ይኸው ነው አጭር ልቦለዱ። ይህ ደግሞ ደምሴን በአገራችን የአጭር ልቦለድ (በ61 ቃላት ላይ ብቻ የተመሰረተ) አጻጻፍ ታሪክ የመጀመሪያው ያደርገዋልና “የመጀመሪያው ደምሴ” ይኸው ነው።

**(ማስታወሻ፡-** የአለማችን አጭሩ ልብወለድ ባለ6 ቃላቱ “For sale: baby shoes, never worn.” ሲሆን፣ ደራሲውም ኤርነስት ሔሚንግዌይ መሆኑን ያስታውሷል። ደምሴ የሄሚንግዌይ አድናቂ መሆኑን ደግሞ በዚሁ መፅሀፍ (ምትሀት) ላይ መግለፁን ገልፀናል። )

## ደምሴ በእድሜ አመሻሹ ላይ

በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የዋና አዘጋጅነት ወንበርን ከያዘ በኋላ በስራ ብዛት ተጨናንቆ፣ የስኳር በሽታም በዚሁ ግዜ ይዞት እንደ ነበር፤ እንዲሁም የሙሉ ጊዜ ስራውንም ጋዜጣው ላይ አድርጎ ይሰራ የነበረው አንጋፋው መምህር፣ ደራሲና ጋዜጠኛ ደምሴ ፅጌ የቀድሞው የአማርኛ መጻሕፍትን እንደ ገና መልሶ ማንበብ ጀምሮ እንደ ነበርም ተናግሮለት እኛም ጠቅሰነዋል።

በኩላሊት ህመም ሲሰቃይ የነበረውንና ሀምሌ መጀመሪያ (2001 ዓ.ም) ላይ ከዚህ አለም በሞት የተለየንን ደምሴ እቤቱ ድረስ በመሄድ ጠይቆት የነበረውና የነበረበትን ሁኔታ አዲስ አድማስ ጋዜጣ (መጋቢት 4 ቀን 2002 ዓ.ም) ላይ ያሰፈረው አለማየሁ ገላጋይ እንደሚናገረው ከሆነ ደምሴ ከህመሙ ለመዳን 500ሺህ ብር ያስፈልገው ነበር። ይህን ብር ቢያገኝ ኖሮ በዶክተሮቹ ውሳኔ ውጭ አገር ሄዶ መታከምና ወደ ነበረበት የጤንነት ሁኔታ መመለስ ይችል ነበር። ነገር ግን የደረሰለት ባለመኖሩ ይህ ሳይሆን ቀርቷል።

አለማየሁ ገላጋይ እንደ ነገረን ደምሴ በጠና ታሞ እንኳን ስለሥነ ጽሑፍና ፍልስፍና፤ ደራሲያንና ፈላስፎች ከመናገርና ማዳመጥ ወደ ኋላ አላለም ነበር። እንደውም “አላጫውት አለን እኮ ...” በማለት ቴሌቪዥኑን ሁሉ በመዝጋት ሙሉ ትኩረቱን ወደ ፍልስፍናዊ ጭውውቱ (ወጉ) ያደርግ ነበር። (ዝርዝሩ ብዙ ነውና ጋዜጣውን ይመለከቷል። )

በመጨረሻም፣ ይህ ጽሑፍ እንደ መነሻ ሆኖ፣ ወደ ፊት በስራዎቹ ላይ በምሁራን የተደረጉ በርካታ ጥናቶችን እንመለከታለን ብለን ተስፋ እያደረግን፤ የዛሬውን ስለ ደምሴና ተያያዥ ጉዳዮች ያደረግነውን ምጥን ዳሰሳ በዚሁ እንቋጫለን።

ስም ከመቃብር በላይ ነው!!!



## “ቢልጌትስ በሐብት የሚበልጠኝ አንድ ጥቁር ብቻ ነው” አለ


የአለማችን ቀዳሚ ባለጠጋ በአንድ ኢንተርቪው እንዲህ ተጠየቀ ከአንተ የሚበልጥ ባለጠጋ ማን ነው?

### ከአንተ የሚበልጥህ ባለጠጋ አለ ?

‹‹አዎ የሚበልጠኝ ሰው አለ። የሚበልጠኝ አንድ ሰው ብቻ ነው። ከብዙ ዓመት በፊት ወደ ኒውዮርክ መሄድ ነበረብኝ። ወደ ኒውዮርክ ለመሄድ አየር መንገድ ላይ ሳለሁ የተለያዩ ጋዜጦችን የጋዜጣ አዟሪዎች እጅ ላይ አየሁ። ካየኋቸው ጋዜጦች መካከል አንዱን ወደድኩት ለመግዛት አስቤ ኪሴ ስገባ ዝርዝር ስላጣሁ ሳልገዛው መልሼ ተውኩት። በድንገትም አንድ ጥቁር ጋዜጣ አዟሪ ልጅ መጣና ጋዜጣውን ሰጠኝ። ዝርዝር የለኝም አልወስደውም አልኩት እርሱም ችግር የለውም በነጻ ውሰደው አለኝና በነጻ ሰጠኝ። ከሦስት ወር በኋላ ተመልሼ በዚያው አየር መንገድ ማለፍ ነበረብኝና በዚያ አየር መንገድ ሳልፍ አሁንም አጋጣሚ ሆነና ያንን ጋዜጣ አዟሪ ጥቁር ልጅ አገኘሁት። አሁንም በነፃ ጋዜጣ ሰጠኝ። እኔም በነፃ አልቀበልህም አልኩት እርሱም ግድየለም ከትርፌ ላይ እቀንሳለሁ ውሰድ አለኝና በነጻ ሰጠኝ። ከ19 አመትም በኋላ ባለጠጋ ከሆንኩ በኋላ ያንን ልጅ ፈልጌ ለማግኘት ወሰንኩና ፈለኩት ከአንድ ወር ተኩል ፍለጋም በኋላ አገኘሁት። ከዚያም አወቅከኝ ብዬ ጠየኩት። አዎ አውቅሃለሁ ዝነኛው ቢልጌት አይደለህም አለኝ። ከብዙ አመት በፊት ሁለት ጊዜ ጋዜጣ በነጻ ሰጥተኸኛል። ያንን ውለታህን አካክሼ መመለስ እፈልጋለሁና የፈለከውን የትኛውንም ነገር እሰጥሃለሁ ጠይቀኝ አልኩት። ያም ጥቁር ሰው በምንም መካካሻ ልትሰጠኝ አትችልም አለኝ።

እኔም ለምን አልኩት እኔ የሰጠሁህ ደሃ በነበርኩ ጊዜ ከድህነቴ ነው። አንተ ግን ልትሰጠኝ የመጣኸው ባለጠጋ በሆንክ ጊዜ ነው። እነዚህን ሁለቱን እንዴት አካክሰህ ልትሰጠኝ ትችላለህ። ቢልጌትም ያጥቁር ወጣት በርግጥም ከእኔ የሚበልጥ ባለጠጋ ነው። ለመስጠት ባለጠጋ መሆንህን ወይም ባለጠጋ እስክትሆን ድረስ አትጠብቅ። መስጠት የልብ ጉዳይ ነው እንጂ የአቅም ጉዳይ አይደለም።

# ጠቃሚ አባባሎች



አንተ ጠንክረህ በዝምታ ስትሰራ ፣ ስኬትህ ጮኾ ይናገራል።

**-ፍራንክ ኦሽን**

በሕይወትህ ከዚህ በፊት ያልነበረህ አዲስ ነገር ለማግኘት ከፈለክ፣ አዲስ ሰርተኸው የማታውቀው ስራ ለመስራት መፍቀድ ይኖርብሀል።

**-ቶማስ ጄፈርሰን**

ትክክለኛ ሕይወት የሚጀምረው የምቾት ቀጠና ሲያልቅ። **-ዶናልድ**

አንተን ሁለት ነገሮች ይገልፁሀል። የመጀመሪያው ምንም የሌለህ ጊዜ የምታሳየው ትዕግስት ሲሆን ሁለተኛው ሁሉም ሲሟላልህ የምታሳየው ጠባይ ነው።

**-ኢማም አሊ**

በምድር ላይ ትልቁ አስደሳች ነገር ሰዎች አትችልም ያሉህን ሰርተህ ማሳየትህ ነው። **-ዋልተር ባግሆት**

ወንዝ ድንጋይ ቦርቡሮ የሚገባው ሀይለኛ ስለሆነ ሳይሆን ያለማቋረጥ ስለሚፈስ ነው። **-ጂም ዋትኪንስ**

ህልምህን ለመፈፀም ብዙ ጊዜ በመውሰዱ ተስፋ አትቁረጥ ምክንያቱም ጊዜ ስለሚበር አርቀህ ያየኸው ህልም በፍጥነት መፈፀሙ አይቀርም። **-አርል ኒተንጋል**

ሰዎች በምታቅደው እቅድ ካልሳቁ ወይም ካልተገረሙ እቅድህ ትንሽ ነው ማለት ነው። **-አዚም ፕሪሚጂ**

ለመጀመር ትልቅ መሆን አይጠበቅብህም፤ ነገር ግን ትልቅ ለመሆን መጀመር አለብህ። **-ዚግ ዚግላር**

ደስተኛ የሆነ ሕይወት ለመኖር ከፈለክ ከሁኔታና ከሰዎች ጋር ሳይሆን ከአላማና እቅድህ ጋር ተጣበቅ። **-አልበርት አንስታይን**

አንተ የምርጫህ ውጤት እንጂ በአንተ ላይ የሚደርሱት ነገሮች ውጤት አይደለህም። **-ካርል ጉስታቭ**

ባለትላልቅ አእምሮ ሰዎች በሃሳብ ላይ ይወያያሉ ፣ መካከለኞች በ ድርጊት / ሁኔታዎች ላይ ይወያያሉ ባለትናንሾች ቁጭ ብለው ሰው ያማሉ። **-ሪያኖር ሮዝቬልት**

እስካልቆምክ ድረስ በምንም ዝግታ ብትጓዝ መድረስህ አይቀርም። **-ኮንፊሺየስ**

ችሎታ ያለው ሰው ምንም ስራ እስካልሰራ ድረስ ችሎታ በሌለው ጠንካራ ሰራተኛ ይበለጣል።

**-ቲም ኖትኪ**

ከውድቀት ይልቅ ጥርጣሬ የነገ ህልምን ይገላል።

**-ሱዚ ካስም**

እውቀት ብቻ አይበቃም ተግባራዊ ካልተደረገ በስተቀር ፣ ፍቃደኛነት ብቻ አይበቃም ካልተሰራ በስተቀር። **-ብሩስ ሊ**

የዛሬ አመት በዚህ ሰአት ምናለ ምናለ ከአመት በፊት በጀመርኩ የምትላቸው ብዙ ነገሮች ይኖራሉ።

**-ካረን ላንብ**

ጀማሪዎቹ ለመስራት ከሞከሩት ጊዜ በላይ አለቃቸው ብዙ ጊዜ ወድቋል።

**-ስቴፈን ማክክሬን**

ብዙ ጊዜ ላለመስራት የምትተዋቸው ስራዎች በውስጣቸው ብዙ እድልን የያዙ ናቸው።

**-ሮቢን ሻርማ**

መተንፈስ እንደምትፈልግ ያህል ለስኬታማ ሕይወት ጥልቅ ፍላጎት ካለህ ይሳካልሀል። **-ኤሪክ ቶማስ**

ፊትህን ወደ ፀሀይ ስታዞር ጥላህ ከኋላህ ይወድቃል።

**-የማዎሪ አባባል**

99 በመቶ የሚሆኑ ሰዎች ሀሳብህን ከተጠራጠሩህ፣ እጅጉን ስተሀል አልያም ታሪክ ልትሰራ ነው።

**-ስኮት ቤልስካይ**

ፈፅሞ አትድከም ምክንያቱም አሁን እጅግ ከባድ የሆነብህ ስራ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ለሌላ ስራ መሟሟቂያ ይሆናል።

**-ያልታወቀ ሰው**

# የፀጉር መሳሳት መነሻ ምክንያትና ህክምናው

- ሰዎች በተፈጥሮ በየቀኑ ከ50 እስከ 100 የሚሆን ፀጉራቸውን ያጣሉ ነገርግን በተመሳሳይ ሁኔታ በሌላ አዲስ ፀጉር ስለሚተኩ አይታወቃቸውም። የፀጉር መሳሳት የሚፈጠረውም እንግዲህ ያጣነውን ፀጉር የሚተካ አዲስ ፀጉር መተካት ሳይቻል ሲቀር ነው። ለፀጉር መሳሳት መነሻ ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም ከነዚያ መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው :-
- የሆርሞን ለውጥና የህክምና ሁኔታ :-በእርግዝና ፣ልጅ በመውለድ ፣የወር አበባን በማቆም ወይም በታይሮይድ እጢ ችግር ምክንያት በሚፈጠር የሆርሞን ለውጥ የፀጉር መሳሳት ሊፈጠር ይችላል። እንደ Alopecia Areata ያሉ በሽታን ከመከላከል የሰውነታችን ስርዓት (Immune system) ጋር የሚያያዙ እና የተለያዩ የፀጉር መነቃቀልን የሚያስከትሉ ፣የአናት ኢንፌክሽንን የሚያስከትል የRingworm ኢንፌክሽንን የመሳሰሉ የህክምና ጉዳዮች ለፀጉር መሳሳት ምክንያት ናቸው።
- በቤተሰብ ያለ በዘር የሚተላለፍ የፀጉር መሳሳት :-ይህ ለፀጉር መሳሳት ዋነኛው ምክንያት ሲሆን ከእድሜ መጨመር ጋር የሚከሰት በቤተሰብ ሲወራረስ የሚከሰት የፀጉር መሳሳት ችግር ነው።
- በጭንቅላት የሚሰጥ የጨረር ህክምና የሚወስዱ ሰዎች ፀጉራቸው እንደቀድሞው የመብቀል ሁኔታ በድጋሚ አይኖራቸውም።
- ለበርካታ ግዜያት በከፍተኛ የጭንቀት ሁኔታ ውስጥ ያሳለፉ ሰዎች በሚፈጠርባቸው የሰውነት እና የስሜት ሾክ ምክንያት ለፀጉር መሳሳት ሊጋለጡ ይችላሉ። ይህ አይነቱ የፀጉር መሳሳት በአብዛኛው ጊዜያዊ ነው።
- ፀጉርን በሀይለኛው የሚጎትት የፀጉር ስታይል መከተል ወይም የሞቀ ዘይት ለፀጉራችን መጠቀም ፀጉራችንን ይበታትነዋል።
- ታዲያ ሀኪምዎን መቼ ማየት አለቦት
- ቋሚ የሆነ የፀጉር መቀነስ እየገጠማቸው ያሉና በዚህም የሚሰቃዩ ሰዎች ለመመለጥ ከመዳረጋቸው በፊት ከህክምና ተቋማት የሚሰጡ ህክምናዎችን ከሀኪም ጋር ተመካክረው መከታተል አስፈላጊ ነው።

ፀጉሮን ሲታጠቡ አሊያም ሲያበጥሩ ያልተለመደ አይነት አስደንጋጭ የበዛ የፀጉር መነቃቀል ከገጠሞት ሀኪም ማማከር አስፈላጊ ነው።

**#ምርጥ_መጣጥፎች**